“ባይተዋሩ” እንደ ልቦለድ ችሳ መባሉ
ገፅ 16

# አዲስ ጉዳይ

ጠ/ሚኒስትሩ ከአዳዲስ መረጃዎች ጋር አስተዋወቁን!
ገፅ 11

ቅፅ 13 ቁጥር 780 | ቅዳሜ ታህሳስ 18 ቀን 2007 ዓ.ም | ብር 8.00

# ተቃዋሚዎች የታዛቢዎችን የምርጫ ሂደት ተቃወሙ

## ምርጫው ሳይነገረን ነው የተካሄደው ብለዋል
## ታዛቢዎቹን ህብረተሰቡ ነው የመረጣቸው - ምርጫ ቦርድ

አለማየሁ አንበሴ

በግንቦቱ ምርጫ የሚወዳደሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ባለፈው ሳምንት የተካሄደው የህዝብ ታዛቢዎች ምርጫ ከህግና ደንብ ውጪ፣ የገዢው ፓርቲ አባላት የተመረጡበት ነው በማለት የተቃወሙ ሲሆን ምርጫ ቦርድ በበኩሉ፣ የህዝብ ታዛቢዎችን ህብረተሰቡ ነው የመረጣቸው ብሏል፡፡በዘጠኝ ፓርቲዎች ጥምረት የተመሰረተው የፓርቲዎች ትብብር፣ የታዛቢዎች ምርጫ በተከናወነ ማግስት

ሙሉ ዘገባውን በገፅ 3 ይመልከቱ

# መንግሥት በባህርዳር ተቃውሞ ስተጎዱ ካሳ እንዲከፍል መድረክ ጠየቀ

## መንግሥት የደረሰው ጉዳት እየተጣራ መሆኑን አስታውቋል

ሙሉ ዘገባውን በገፅ 2 ይመልከቱ

# መንግሥት ሔሊኮፕተሯን ለማስመለስ የጀመረው ጥረት የለም ተባለ

ማህሌት ሰለሞን

በዋና አብራሪ ሻምበል ሳሙኤል ግደይ ተጠልፋ ወደ ኤርትራ የገባችውን የኢትዮጵያ አየር ኃይል የሆነች ሩሲያ ሰራሽ ተዋጊ ሔሊኮፕተር ለማስመለስ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል የተጀመረ ምንም አይነት ጥረት እንደሌለ ተገለፀ፡፡ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ፅህፈት ቤት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ እውነቱ ብላታ ለአዲስ አድማስ በሰጡት ምላሽ፣ “የኤርትራ መንግስት ለአካባቢያዊ ህጎችም ሆነ ለዓለም አቀፍ ህጎች ተገዢ የሆነ መንግስት ስላልሆነና ከኤርትራ መንግስት በጎ ምላሽ ይገኛል

ሔሊኮፕተር ወደ ገፅ 2 ዞሯል

# በመንበረ ፓትርያርኩ ቅ/ማርያም ገዳም በሚሊዮኖች የሚገመት ገንዘብ መመዝበሩ ተገለጸ

*የገዳሟ የገንዘብ አያያዝና የንብረት አጠቃቀም በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ታዝዟል*

*የሥራ ዘመኑ ያለፈው ሰበካ ጉባኤ ለገዳሙ ልማትና ለኦዲቱ ዕንቅፋት ኾኗል ተብሏል*


የመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የፓትርያርኮች መንበር (መንበረ ፕትርክና) በኾነችው ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ገዳም፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብና ንብረት በአስተዳደር ሓላፊዎችና ሠራተኞች መመዝበሩን ምንጮች ጠቆሙ፡፡ጥቆማው የቀረበው፣ የገዳሟ ማኅበረ ካህናትና የልማት ኮሚቴ የቤተ ክርስቲያኒቱን የገንዘብና የንብረት አሰባሰብ በተመለከተ ግልጽነትና ተጠያቂነት ያለው አሠራር እንዲዘረጋ የገዳሟ ልማት ኮሚቴ የበላይ ጠባቂ ለኾኑት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ ባቀረቡት ማመልከቻና ሪፖርት ነው፡፡የቤተ ክርስቲያኒቱ መተዳደርያ ቃለ ዐዋዲና ደንቡን መሠረት አድርጎ በሀገረ ስብከቱ የተዘጋጀው የገንዘብ ቆጠራ፣ የንብረት አመዘጋገብና አጠባበቅ መመሪያ የካህናቱን፣ የምእመናኑንና የእያንዳንዱን ሠራተኛ የሥራ ድርሻና ተጠያቂነት በግልጽ ማስቀመጡን የጠቀሱት ማኅበረ ካህናቱ÷ የገዳሟን ገንዘብና ንብረት የመቆጣጠርና የመከታተል መብታቸው በአስተዳደሩ ሓላፊዎች ተነፍጓቸው የሙዳየ ምጽዋት ቆጠራና የንብረት ቁጥጥር ለማድረግ ሳይችሉ መቆየታቸውን ገልጸዋል፡፡ገዳሚቷ በየዕለቱና በየበዓላቱ ከምእመናን በስጦታና በስእለት የምታገኘው ሀብትና ንብረት ከራስዋ አልፎ ለተቸገሩ ገዳማትና አድባራት የሚተርፍ ቢኾንም ግልጽነትና ተጠያቂነት በጎደለው የአስተዳደሩ አሠራርና በሰበካ ጉባኤው የቁጥጥር ማነስ ሳቢያ የገቢ አቅሟን ለማጎልበት ከዓመታት በፊት የወጠነችው ኹለ ገብ ሕንፃ ግንባታ ከመጓተቱም በላይ ለሀገረ ስብከቱ መከፈል ለሚገባው ውዝፍ ዕዳ መዳረጓን ካህናቱ አስታውቀዋል፡፡ በገንዘብ አያያዝና በንብረት አሰባሰብ ረገድ በአስተዳደሩ እየተባባሰ የመጣው ሙስና እንዲወገድና ካለፈው

ገዳም ወደ ገፅ 2 ዞሯል

ምንጩ ያልታወቀ ትኩሳት አለብዎ?
ዩኒቨርሳል ከፍተኛ ክሊኒክ ቁጥር 1
ታይፎይድ፣ ፊቨር መሆኑን ተጠራጥረዋል? ወይስ ወባ? በ3 ደቂቃ በሽታው እንዳለብዎ ወይም እንደሌለብዎ ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡ ሰፊ መመርመሪያ አዘጋጅተናል!!
በኢንተርቼክ ቴስት እና በማሳስካን ስትሪፕ ወዲያውኑ ውጤቱን ያገኛሉ!!
አድራሻ ቸርችል ጎዳና ቴዎድሮስ አደባባይ ከፍ ብሎ ሲልክትፊክ ወርልድ ህንፃ አጠገብ
ዩኒቨርሳል ከፍተኛ ክሊኒክ
ስልክ 011-1-550336

# ኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል በመስተንግዶ ጥራት አለማቀፍ አሸናፊ ሆነ

አለማየሁ አንበሴ

ኢንተርኮንቲኔንታል አዲስ ሆቴል በደቡብ አፍሪካ ደርባን ከተማ በተካሄደውና ከ45 ሀገሮች የተውጣጡ ከ13ሺህ በላይ ሆቴሎች በተሳተፉበት አለማቀፍ የአገልግሎትና አጠቃላይ የሆቴል መስተንግዶ ጥራት አሸናፊ መሆኑ ተገለፀ፡፡ኢንተርኮንትኔንታል አዲስ ሆቴል አለማቀፉን ሽልማት ያገኘባቸው መስፈርቶች የሆቴል መስተንግዶና የአገልግሎት አቅርቦት መሆኑን የጠቆሙት የሆቴሉ ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ ዜናዊ መስፍን፣ ሆቴሎችን ገምግመው ለሽልማት እጩ የሚያደርጉ ባለሙያዎች የግምገማ ስራውን በይፋና በድብቅ ጉብኝት ማከናወናቸውን ጠቁመዋል፡፡ ሆቴሉ ለሽልማት እንዲበቃ የሠራተኞቹና የማናጅመንቱ ተናቦ መስራት በተለይም

ሆቴል ወደ ገፅ 2 ዞሯል

# በሽብር የተከሰሱ የተቃዋሚ አመራሮች፣ በማረሚያ ቤት ንብረት ተወስዶብናል አሉ

## ማረሚያ ቤት ምላሽ እንዲሰጥ ፍ/ቤት አዘዟል

አለማየሁ አንበሴ

"የግንቦት 7 አባል በመሆን በሽብር ድርጊቶች ተሳትፈዋል" በሚል ክስ የተመሰረተባቸው የአንድነት፣ የሰማያዊ እና የአረና ፓርቲ አመራሮች፤ ሌሊት በማረሚያ ቤት በተደረገ ድንገተኛ ፍተሻ ገንዘብን ጨምሮ የተለያዩ ንብረቶች እንደተወሰደባቸው ባለፈው ረቡዕ ለፍ/ቤት አመልክተዋል፡፡ በእነ ዘላለም ወርቅ አገኘው መዝገብ የተከሰሱት የአንድነት ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ሀብታሙ አያሌው፣ የፓርቲው የድርጅት ጉዳይ ም/ኃላፊ አቶ ዳንኤል ሺበሺ፣ የሰማያዊ ፓርቲ አመራር አቶ የሸዋስ አሰፋ እና የአረና ፓርቲ አመራር አባል አቶ አብርሃ ደስታና ሌሎች ተከሳሾች በጠበቃቸው በኩል ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት አቤቱታ፤ ታህሳስ 12 ለ 13 አጥቢያ ከሌሊቱ 8 ሰዓት እስከ ቀኑ 5 ሰዓት በማረሚያ ቤት ድንገተኛ ፍተሻ ተደርጎ፤ የማስታወሻ ደብተራቸው፣ ገንዘብና ሌሎች ሰነዶች እንደተወሰደባቸው ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል፡፡

ፈታሾቹ የማረሚያ ቤቱ ኃላፊዎች ሳይሆኑ በፊት ይመረምሯቸው የነበሩ ፖሊሶችና የደህንነት አባላት እንደሆኑም ጠቁመዋል፡፡ በተለይ የማስታወሻ ደብተራቸው እንደተወሰደባቸው አፅንኦት ሰጥተው የተናገሩት ጠበቃው ተማም አባቡልጋ፤ ተከሳሾቹ ለቀጣይ ክርክር ያዘጋጇቸውን ነጥቦች ያሰፈሩባቸው በመሆኑ በቀረበባቸው ክስ ላይ ለመከራከር እንደሚቸገሩና የስነ ልቦና ጫና እንደሚያሳድርባቸው ለፍ/ቤቱ አስረድተዋል፡ ፡ "ምርመራ የሚፈቀደው ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽት 2 ሰዓት ሆኖ ሳለ በሌሊት መደረጉ ህግ የጣሰ ተግባር ነው፤ ድርጊቱን የፈፀሙ ሰዎች ስልጣናቸውን ያለአግባብ በመጠቀማቸው ህጋዊ እርምጃ ይወሰድልን" በማለት ለፍ/ቤቱ ያመለከቱት ጠበቃው፤ "ደንበኞቼ የማረሚያ ቤት ቆይታቸው አደጋ ላይ የወደቀ በመሆኑ የደህንነት ስጋት አለብኝ፤ በዋስትና ይለቀቁ አሊያም ከወህኒ ቤቱ በተለየ ቦታ እንዲቀመጡ ይደረግ" ሲሉ አጠይቀዋል፡፡

አቃቤ ህግ፤ ለተከሳሾቹ አቤቱታ በሰጠው ምላሽ፤ ጠበቃ ተማም አባቡልጋ የብዙ ታራሚዎችን ደህንነት በማስጠበቅ ኃላፊነቱን እየተወጣ ያለን ማረሚያ ቤት የታራሚዎችን ደህንነት የመጠበቅ ብቃት የለውም ማለታቸው አግባብነት እንደሌለው ጠቁሞ፣ ይህን መነሻ አድርጎ ዋስትና መጠየቁም ተቀባይነት የለውም ሲል ተቃውሟል፡፡ ፖሊስ የብርበራ ትዕዛዝ ይዞ በማረሚያ ቤት ፍተሻ ማካሄድ እንደሚችልም አቃቤ ህግ አስረድቷል፡፡ ፍ/ቤቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ ብይን ለመስጠት በአቤቱታው ላይ የማረሚያ ቤቱ ምላሽ እንደሚያስፈልግ ጠቅሶ፣ በቀጣይ ቀጠሮ የማረሚያ ቤቱ አስተዳደር ጉዳዩ ተፈፅሟል አልተፈፀመም በሚለው ላይ ምላሽ እንዲሰጥ ትዕዛዝ አስተላልፏል፡፡

ፍ/ቤቱ በተጨማሪም ለጠበቃ ተማም አባቡልጋ ማሳሰቢያ ሰጥቷል፡፡ "ተቋምን ብቃት የለውም ብሎ መግለፅ አግባብ አይደለም፣ በማስረጃ አረጋግጡ ቢባሉ ሊከብድት ይችላል" ያለው ፍ/ቤቱ፤ ጠበቃው ከዚህ አይነት አገላለፅ እንዲታረሙ ተግሳፅ ሰጥቷል፡ ፡ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ከሰጠ በኋላ አቶ ሃብታሙ አያሌው "የምናገረው አለኝ" በማለት "በማረሚያ ቤቱ ደህንነት እየተሰማኝ አይደለም፤ ፍ/ቤቱ ደህንነቴን ያስከብር" ሲሉ አቤቱታቸውን በቃል ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም "ድርጊቱ ስለመፈጸሙ በማስረጃ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤ ጉዳዩ በቀጣይ ቀጠሮ ብይን ይሰጥበታል" ሲል መልሷል፡፡ መዝገቡንም ለታህሳስ 24 ቀጥሯል፡፡

ሔሊኮፕተር ከገፅ 1 የዞረ

ተብሎ ስለማይታሰብ፣ ሔሊኮፕተሯን ለማስመለስ በኢትዮጵያ መንግስት በኩል ምንም አይነት ጥረት እየተደረገ አይደለም" ብለዋል፡፡ መንግስት ወደፊት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንደሚሰጥም አክለው ተናግረዋል፡፡ ቀደም ሲል የመከላከያ ሚኒስቴር በሰጠው መግለጫ፣ ረዳት አብራሪውና የሔሊኮፕተሩ ቴክኒሻን በዋና አብራሪው ሻምበል ሳሙኤል አስገዳጅነት ኤርትራ መግባታቸውን የጠቆመ ሲሆን የሔሊኮፕተሯ አብራሪ ለምን ድርጊቱን እንደፈፀመ እስካሁን የታወቀ ነገር የለም፡፡አሶሼትድ ፕሬስ በጉዳዩ ዙሪያ ባቀረበው ዘገባ፤ ብዙ ጊዜ የኤርትራ ወታደሮች በአገራቸው ባለው አስቸጋሪ ሁኔታዎች የተነሳ ወደ ኢትዮጵያ እንደሚገቡ ጠቁሞ "ከኢትዮጵያ ወደ ኤርትራ የሚደረግ ሽሽት ግን ያልተለመደና እንግዳ ጉዳይ ነው" ብሏል፡፡ ባለፈው አርብ ማለዳ 2:35 ላይ ድሬደዋ ከሚገኘው የአየር ኃይል ማዘዣ ጣቢያ የዘወትር የልምምድ በረራ ለማድረግ የተነሳችው ተዋጊ ሔሊኮፕተር፤ በዋና አብራሪ ሻምበል ሳሙኤል ግደይ እየተመራች ረዳት አብራሪ መቶ አለቃ ቢልልኝ ደሳለኝንና ቴክኒሻን ፀጋ ብርሀን ግደይን ይዛ ወደ ኤርትራ መኮብለሏ የሚታወስ ነው፡ ፡ በተመሳሳይ በ1995 ዓ.ም ሻምበል ተሾመ ተንኮሉ በተሰኘ የአየር ኃይል ባልደረባ ኤል 39 የተሰኘ የልምምድና ቀላል የውጊያ አውሮፕላንን ለልምምድ ከመቀሌ የማዘዣ ጣቢያ ይዞ በመነሳት ወደ ኤርትራ መኮብለሉ የሚታወስ ነው፡፡ እስካሁን የኤርትራ መንግስት በጉዳዩ ላይ አንዳችም አስተያየት እንዳልሰጠ ታውቋል

# በእንግሊዛዊው ላይ የተፈፀመው ግድያ ሆን ተብሎ የተደረገ አይደለም ተባለ

አለማየሁ አንበሴ

ሠሞኑን በባህር ዳር ከተማ በእንግሊዛዊው የ50 አመት ጐልማሳ ቱሪስት ላይ የተፈፀመው ግድያ ሆን ተብሎ የተፈፀመ አለመሆኑን መንግስት ገለፀ፡ ፡ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሽመልስ ከማል ጉዳዩን አስመልክቶ ለአዲስ አድማስ እንደገለፁት፤ ቱሪስቱን በመግደል ተጠርጥሮ የተያዘው ግለሰብ ፍቃድ ያለው መሣሪያ ይዞ እንደነበርና ከአንዱ ትከሻው ወደ አንዱ በሚያቀያይርበት ወቅት በድንገት ጥይት ባርቆበት አደጋው መከሰቱን ለፖሊስ ተናግሯል ብለዋል፡፡ በተጠርጣሪነት በቁጥጥር ስር የዋለው ግለሰብ ላይ የሚደረገው ተጨማሪ ምርመራ መቀጠሉንም ሚኒስትር ዴኤታው ገልፀዋል፡፡ ድርጊቱ የተፈፀመው ባለፈው ረቡዕ ከረፋዱ 4 ሰዓት ከ30 ላይ ባህርዳር ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን አካባቢ መሆኑን ፖሊስ ገልፆ፤ ተጠርጣሪውን ወዲያው በቁጥጥር ስር አውሎ የሟች አስከሬን ባህርዳር ሆስፒታል እንዲቆይ ከተደረገ በኋላ ሃሙስ እለት ወደ አዲስ አበባ እንዲላክ ተደርጓል ተብሏል፡፡ የሟች አስከሬን አዲስ አበባ በደረሰበት ወቅትም የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትሩ አቶ አሚን አብዱልቃድርና በኢትዮጵያ የእንግሊዝ አምባሣደር ግሬግ ዶሪ አቀባበል ያደረጉ ሲሆን አስከሬኑ ምርመራ ከተደረገለት በኋላ ወደ ትውልድ ሀገሩ እንደሚሸኝም ለማወቅ ተችሏል፡፡ አዲስ አበባ በተደረገው አቀባበል ላይ፤ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስትሩ አቶ አሚን አብዱልቃድር፤ ግድያው በልዩ አላማ ወይም በሽብር የተፈፀመ አለመሆኑን በመጥቀስ የእንግሊዛዊውን መገደል ተከትሎ የሀገሪቱ የጐብኚዎች ፍሰት አይቀንስም፤ ገጽታንም አያበላሽም ብለዋል፡፡

# መንግሥት በባህርዳር ተቃውሞ ለተጎዱ ካሳ እንዲከፍል መድረክ ጠየቀ

## መንግሥት የደረሰው ጉዳት እየተጣራ መሆኑን አስታውቋል

አለማየሁ አንበሴ

በባህርዳር የተቃውሞ ሰልፍ ላይ ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች መንግስት ካሳ እንዲከፍልና ጥቃቱን የፈፀመውን አካል ለፍርድ እንዲያቀርብ መድረክ የጠየቀ ሲሆን መንግሥት በበኩሉ ጉዳቱ እየተጣራ ነው ብሏል፡፡ "በባህርዳር ከተማ በሰላማዊ አግባብ ተቃውሞ ባሰሙ ዜጎች ላይ የተፈፀመው ጥቃት የአምባገነናዊ አገዛዝ ባህሪ ነፀብራቅ ነው" ያለው ፓርቲው፤ ማንኛውንም የኃይል እርምጃ በጥብቅ እንደሚያወግዝ አስታውቋል፡፡ የከተማዋ ነዋሪ በሆኑ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን እምነት ተከታዮች ላይ የተወሰደው የኃይል እርምጃ በህገ መንግስታዊ የመቃወም መብት ላይ የተፈፀመ ጥሰት ነው ያለው መድረክ፤ ከዚህ ቀደምም የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታይ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ላይ መሰል ተግባር ሲፈፀም መቆየቱን ጠቅሶ፤ "ጥቃቱ ኃላፊነት የጎደለውና ተቀባይነት የሌለው ነው" ሲል አውግዟል፡፡ በሌላ በኩል በደቡብ ክልል የተለያዩ ወረዳዎች የመድረኩ አባላት በማዳበሪያ እዳ ሰበብ እየታሰሩ እንደሆነ የጠቆመው ፓርቲው፤ ድርጊቱ የሚፈጸመው አባላቱን ከግንቦቱ የምርጫ እንቅስቃሴ ለማራቅ በማሰብ ነው ብሏል፡፡ በባህርዳር ከእምነት ቦታ ጥያቄ ጋር በተገናኘ በተደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ጉዳት ስለ መድረሱና ስለ እርምጃው ተገቢነት ከጋዜጠኞች ጥያቄ የቀረበላቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ፤ ጉዳት ስለመድረሱ መረጃው እንዳላቸው ጠቁመው የጉዳቱ ምክንያት ምንድን ነው የሚለው ተጣርቶ እንደሚታወቅ ተናግረዋል፡፡ "በፀጥታ ኃይሎች ነው የተከናወነው ወይስ የተለያየ የራሱ መንገድ አለው የሚለው ተጣርቶ የሚታወቅ ነው" ያሉት ጠ/ሚኒስትሩ ጉዳዩ ተጣርቶ ውጤቱ በሚታወቅ ጊዜ ተገቢው ህጋዊ እርምጃ ይወሰዳል" ብለዋል፡፡

ገዳም ከገፅ 1 የዞረ

ዓመት ነሐሴ ወር ጀምሮ የተስተጓጎለው የልማት ሥራ እንዲቀላጠፍ በኅዳር ወር አጋማሽ ፓትርያርኩን መጠየቃቸውንም አመልክተዋል፡፡ከገዳሚቷ የልማት ኮሚቴ ጋራ በመቀናጀት የቀረበውን የማኅበረ ካህናቱን ማመልከቻ መነሻ በማድረግ ፓትርያርኩ አቡነ ማትያስ በሰጡትና በረዳት ሊቀ ጳጳሱ በኩል ተፈጻሚ በኾነው መመሪያ፤ የገዳሟን የገንዘብና ንብረት አሰባሰብ የሚከታተል አምስት ካህናት ያሉት የሙዳየ ምጽዋት ቆጠራ ኮሚቴ ኅዳር 18 ቀን መቋቋሙ ታውቋል፡፡ ኮሚቴው ከተቋቋመበት ማግሥት አንሥቶ ኅዳር 19 እና 22 ቀናት ባካሔደው የሙዳየ ምጽዋት ቆጠራ የተገኘውን ከብር 826,000 በላይ ገቢ ጨምሮ ከንብረት ሽያጭና በሞዴል 30 የተሰበሰበውን በማካተት ከ1.2 ሚሊዮን ብር በላይ አጠቃላይ ገቢ በአንድ ወር ብቻ መመዝገቡ ተገልጧል፡፡ በካህናቱ አስፈጻሚነት በአንድ ወር የተወሰነ ቆጠራ ብቻ ይህን ያኽል ገቢ መመዝገቡ፣ የገዳሟ ገቢ «የግለሰቦች መደራጃ ኾኖ መኖሩን የሚያሳይ ነው፤» ብለዋል - ማኅበረ ካህናቱ፡፡ አያይዘውም ለሀገረ ስብከቱ መክፈል የሚገባው የኻያ በመቶ ውዝፍ ዕዳ ሳይፈጸም አኹን በካዝና ያለው ብር 129,000 ብቻ እንደኾነ በመጥቀስ ገዳሟ በየዓመቱ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ብር ስትመዘበር እንደኖረችና ጠቅላይ ቤተ ክህነቱም ኾነ ሀገረ ስብከቱ በየደረጃው ማግኘት የነበረባቸውን የፐርሰንት ፈሰስ ማጣታቸውን ስለሚያረጋግጥ «የአስተዳደር ሠራተኞቹን ተጠያቂ የሚያደርግ ነው፤» ብለዋል፡፡ እንደ ማኅበረ ካህናቱ እምነት፣ የገዳሟ ገቢ ለአስተዳደር ሠራተኞቹ ምዝበራ የተጋለጠው የተጠናከረ ሰበካ ጉባኤ ባለመኖሩ ነው፡፡ አኹን ያለው የገዳሙ ሰበካ ጉባኤ በቃለ ዐዋዲው መሠረት፣ የገዳሙን የሥራ ክፍሎች አገልግሎት አፈጻጸም በወቅታዊ የኪንውን መግለጫዎች የመከታተል፣ የሒሳብ አያያዙንና የንብረት እንቅስቃሴውን ጊዜውን ጠብቀውና እንዳስፈላጊነቱ በሚቀርቡ ሪፖርቶች የመቆጣጠር ሓላፊነቱን ካለመወጣቱም በላይ «ገዳሚቷ ችግር ላይ ስትወድቅ ዝም ብሎ የኖረ ተባባሪ» በመኾኑና የሥራ ጊዜውም በማለፉ ጠንካራና ሓላፊነት በሚሰማው ሰበካ ጉባኤ እንዲተካ መመሪያ እንዲሰጥላቸው፣ ተጀምሮ የቆመው ልማት እንዲቀጥል፣ የገዳሟ ገቢና ወጪም በውጭ ኦዲተሮች እንዲጣራ ማኅበረ ካህናቱ ፓትርያርኩን ጠይቀዋል፡፡ ያለማኅበረ ካህናቱና ማኅበረ ምእመናኑ ፈቃድ ጊዜው በሀ/ስብከቱ ውሳኔ ተራዝሟል የተባለው ሰበካ ጉባኤ፣ በቆጠራ ኮሚቴው የተሰበሰበውን ከብር 440,000 በላይ የገዳሚቷን ከፍተኛ ገንዘብ ያለተቆጣጣሪ ወጪ ማድረጉን ካህናቱ ገልጸው፣ ሕጋዊ ሰበካ ጉባኤ ሳይቋቋም ቀጣይ ቆጠራ እንደማይካሔድ አስጠንቅቀዋል፡፡ በገዳሚቷ አስተዳደር ውስጥ ሙስናዊ ጥቅማቸው የተነካባቸው ናቸው ያሏቸው ግለሰቦች፣ የቆጠራ ኮሚቴውን ለማፍረስ÷ «ማኅበረ ቅዱሳንና ግንቦት ሰባት ናችኹ፤ ምርጫውን ለማወክ ትንቀሳቀሳላችኁ፤ ወደ ሌላ ደብር እናዘዋውራችኋለን» በሚል ከሚያደርሱባቸው ዛቻና ማስፈራራት እንዲቆጠቡ አስተዳደራዊ ርምጃ እንዲሰጥላቸው አመልክተዋል፡፡የማኅበረ ካህናቱንና የልማት ኮሚቴውን ጥያቄ ተከትሎ ፓትርያርኩ በሰጡት መመሪያ÷ ሰበካ ጉባኤው የሥራ ክንውን ሪፖርት ካቀረበ በኋላ የአዲስ ሰበካ ጉባኤ ምርጫ እንዲካሔድ፣ የገዳሚቷ ገቢና ወጪ ሒሳብ በአስቸኳይ በውጭ ኦዲተር ተከናውኖ እንዲቀርብ፣ የቆጠራ ኮሚቴው የአስተዳደሩን ዕውቅና አግኝቶ ተጠናክሮ እንዲቀጥል፣ በ48 ሚልዮን ብር ወጪ በኹለት ምዕራፎች የተጀመረውና የተጓተተው የባለስድስት ፎቅ የአገልግሎትና ኹለገብ ሕንፃ ግንባታ የብቃት ማረጋገጫ ባለው አካል ክትትል እንዲፋጠን ማዘዛቸው ታውቋል፡፡

ሆቴል ከገፅ 1 የዞረ

የሠራተኞቹ መልካም የመስተንግዶ ጠባይ መሆኑን ጠቅሰው ሠራተኞቻቸውን በእጅጉ አመስግነዋል፡፡ "ሠራተኞቻችን ሁሉንም እንግዳ በፈገግታ ተቀብለው በእኩል የማስተናገድ ክህሎት ያላቸው" ናቸው ያሉት ዋና ስራ አስኪያጁ፤ "ደንበኞቻችን የዚህ ምስክር ሆነው ለሽልማት በቅተናል" ብለዋል፡፡ ሆቴሉ አለማቀፍ ሽልማት ማግኘቱና ይህ የሽልማት ስነስርዓት በተለያዩ አለማቀፍ የሚዲያ አውታሮች መነገሩ ለሆቴሉ የበለጠ አለማቀፋዊ እውቅና እንደሚያስገኝለት ጠቁመው፤ ለሀገሪቱም በሆቴል መስተንግዶ ዘርፍ መልካም ገፅታ ይፈጥራል ብለዋል፡፡ አክለውም ሆቴሉን በአለማቀፍ ደረጃ ይበልጥ ለማስተዋወቅ ሽልማቱ የፕሮሞሽን አካል ሆኖ እንደሚያገለግል ስራ አስኪያጁ ገልፀዋል፡ ፡ ኢንተርኮንቲኔንታል አዲስ ሆቴል ከግብፅ፣ ከሞሮኮ፣ ከሲሼልስ እና ከናሚቢያ ሆቴሎች ጋር ተወዳድሮ ከአፍሪካ ምርጥ አስር ሆቴሎች ውስጥ መካተቱ ታላቅ ስኬት ነውም ተብሏል፡፡ ተሸከርካሪ ሬስቶራንትና አለማቀፍ ደረጃውን የጠበቀ የስብሰባ አዳራሽ ያለው የማስፋፊያ ፕሮጀክቱ በቅርቡ ሲጠናቀቅ የሆቴሉን አገልግሎት ይበልጥ እንደሚያሣድገው በጋዜጣዊ መግለጫው ተጠቁሟል፡፡

# ታማሚዎችን ለህክምና ወደ ውጭ አገራት የሚልክ ድርጅት ተከፈተ

መታሰቢያ ካሣዬ

ለህክምና ወደ ውጭ አገር ለሚሄዱ ህሙማን ሙያዊ የምክር አገልግሎት በመስጠትና የህክምናውንና የጉዞውን ሁኔታ በማመቻቸት ሥራ ላይ የተሰማራ "ጌትዌል" የተሰኘ ድርጅት ተቋቁሞ አገልግሎት መስጠት ጀመረ፡፡

በተለያዩ የጤና ችግሮች ተይዘው ከፍተኛ ህክምና እንደሚያስፈልጋቸው የተገለፀላቸው በርካታ ህሙማን ህክምናቸውን የትና እንዴት ማግኘት እንደሚገባቸው ባለማወቃቸው እንዲሁም በውጭ አገር ስለሚገኙ የህክምና ተቋማትና ስለሚሰጡት አገልግሎቶች ያላቸው ግንዛቤ አነስተኛ በመሆኑ ከፍተኛ ችግር እንደሚያጋጥማቸው የገለፁት የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ዶ/ር በጋሻው ባይለየኝ፤ ድርጅቱ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ታስቦ መቋቋሙን ተናግረዋል፡፡

በህክምና ባለሙያዎች የተቋቋመው ድርጅቱ፤ እስከ አሁን አምስት ህሙማንን ወደ ውጭ አገር ልኮ እንዲታከሙ ያደረገ ሲሆን ለ15 ህሙማንም ህክምናቸውን የሚያገኙበትን ሁኔታ በማመቻቸት ላይ እንደሆነ ተገልጿል፡፡ "ጌትዌል"ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል የአየር አንቡላንስ አገልግሎት፣ የውጭ ሀገር ህክምናን ማመቻቸትና የከፍተኛ ደረጃ ህክምና የምክር አገልግሎቶች የሚጠቀሱ ሲሆን ከፍተኛ የጤና ችግር ላለባቸው ህሙማን በጉዞ ወቅት አጋዥ ሐኪሞችንና ነርሶችን በመመደብ፣ ህሙማኑ ህክምና ለማግኘት የሚችሉበትን ሁኔታ እንደሚያመቻች ሥራ አስኪያጁ ተናግረዋል፡፡ ድርጅቱ እስከ አሁን ድረስ በህንድ፣ በታይላንድ፣ በሲንጋፖርና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ ውስጥ ካሉ ስምንት ታላላቅ የጤና ተቋማት ጋር በትብብር እየሰራ እንደሚገኝ ሥራ አስኪያጁ ገልፀው፤ እንደየታካሚው ፍላጐት በዓለም ዙሪያ ህክምና ማግኘት የሚቻልበትን መንገድ እናመቻቻለን ብለዋል፡ ፡ ታካሚዎች ህክምናቸውን ጨርሰው ወደ አገራቸው ከተመለሱ በኋላም የህክምና ክትትል እንደሚያደርጉ ዶክተሩ ገልፀዋል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የማይገኙ ወይንም አቅርቦታቸው ዝቅተኛ ለሆኑ የህመም ህክምናዎች በየዓመቱ ወደውጭ አገር የሚሄዱ ዜጐች ቁጥር ሰላሣ ሺ እንደሚደርስ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

# ተቃዋሚዎች የታዛቢዎችን የምርጫ ሂደት ተቃወሙ

## ምርጫው ሳይነገረን ነው የተካሄደው ብለዋል

## ታዛቢዎቹን ህብረተሰቡ ነው የመረጣቸው - ምርጫ ቦርድ

አለማየሁ አንበሴ

በግንቦቱ ምርጫ የሚወዳደሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ባለፈው ሳምንት የተካሄደው የህዝብ ታዛቢዎች ምርጫ ከህግና ደንብ ውጪ፣ የገዢው ፓርቲ አባላት የተመረጡበት ነው በማለት የተቃወሙ ሲሆን ምርጫ ቦርድ በበኩሉ፤ የህዝብ ታዛቢዎችን ህብረተሰቡ ነው የመረጣቸው ብሏል፡፡

በዘጠኝ ፓርቲዎች ጥምረት የተመሰረተው የፓርቲዎች ትብብር፤ የታዛቢዎች ምርጫ በተከናወነ ማግስት "የታዛቢዎች ምርጫ የገዥውን ፓርቲና የምርጫ ቦርድን አንድነት ይበልጡን ያረጋገጠ ነው" በሚል ባወጣው መግለጫ፤ ምርጫው ዋና ዋና ፓርቲዎችን ባገለለ መልኩ የተከናወነ ነው ሲል ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

የህዝብ ታዛቢዎች አመራረጥን በሚደነግገው መመሪያ መሠረት፤ የምርጫ ጣቢያ ሃላፊው ለህዝብ ይፋ የስብሰባ ጥሪ ማድረግ እንዳለበት ተቀምጧል ያለው የትብብሩ መግለጫ፤ ታህሣሥ 12 በተካሄደው ምርጫ ግን የገዥው ፓርቲ ካድሬዎች የመረጧቸው የወጣትና የሴት ሊግ አባላት እንዲመረጡ ተደርጓል ብሏል፡፡ መመሪያው ፓርቲዎች በምርጫው እንዲሳተፉ በደብዳቤ ጥሪ ይደረጋል ቢልም ከኢህአዴግ ተወካዮች ውጪ የትኛውም የተቃዋሚ ፓርቲ በፅሁፍ አልተጋበዘም ብሏል - ትብብሩ፡፡

"ምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ከሂደቱ ባገለለ መልኩ የምርጫ ታዛቢዎችን መርጦ መሠየሙ ለገዥው ፓርቲ መገልገያ ከመሆኑም ባሻገር ባጠቃላይ ምርጫው የኢህአዴግ የማምታቻ ፖለቲካ እንደሆነ ያረጋገጠ ነው" ይላል - መግለጫው፡፡

በ2002 ምርጫ ተመሳሳይ ነገር መፈፀሙን ያስታወሰው ትብብሩ፤ የህዝብ ታዛቢዎች ያለተወዳዳሪ የኢህአዴግ አመራር በሆኑ አስመራጮች መልካም ፈቃድ ብቻ ታዛቢ እንዲሆኑ ተደርጓል ብሏል፡፡

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) ሊቀመንበር ፕ/ር በየነ ጴጥሮስ በበኩላቸው፤ የአመራረጥ መመሪያው ለተሣታፊ ፓርቲዎች በቀጥታ ጥሪ ተደርጐላቸው እንዲታደሙ ይደረጋል እንደሚል ጠቅሰው፤ "በመገናኛ ብዙሃን ከተነገረው ውጭ በምርጫው ላይ እንድንሣተፍ ጥሪ አልቀረበልንም፤ ከዚህ አንፃር አካሄዱ ሚስጥራዊና ስህተት ያለበት ነው" ብለዋል፡፡

ሙሉ ለሙሉ ህገወጥ ተግባር ነው የተከናወነው ያሉት ሊቀመንበሩ፤ ለምርጫ ሂደቱ ወሣኝ የሆነው የህዝብ ታዛቢዎች ምርጫ በዚህ መልኩ መከናወኑ ገዥው ፓርቲ ምርጫውን በቁጥጥሩ ስር ለማስገባት ያስችለዋል ብለዋል፡፡ "ቦርዱ 250ሺ የህዝብ ታዛቢ አስመርጠናል ያለው የገዢውን ፓርቲ ሰዎች በማስመረጥ ነው" ሲሉም ተችተዋል - ፕ/ር በየነ፡፡

የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አባል የሆነው የመላው ኢትዮጵያውያን ብሔራዊ ንቅናቄ (መኢብን) ፕሬዚዳንት አቶ መሣፍንት ሽፈራው በሰጡት አስተያየት፤ ምርጫ ቦርድ በሰሞኑ የታዛቢዎች ምርጫ ላይ ስህተት ሠርቷል ይላሉ፡፡ "ምርጫው እንደሚካሄድ በሚገባ አላስተዋወቁም፤ ለኛም አልነገሩንም" ብለዋል - አቶ መሣፍንት፡፡

ቦርዱ ለፓርቲዎች በደብዳቤ ጥሪ ማቅረብ እንደነበረበት የጠቀሱት ፕሬዚዳንቱ፤ ጥሪው ባለመቅረቡ የህዝብ ታዛቢዎች ምርጫው አሳታፊ ነው ማለት አይቻልም ብለዋል፡፡ በትክክል የህዝብ ታዛቢዎች ናቸው የተመረጡት ብሎ ለመቀበል የፓርቲዎች ውክልና ያስፈልግ ነበር ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ የፓርቲዎቹ ተወካዮች በሌሉበት ታዛቢዎቹ መመረጣቸው ፍትሃዊ አይደለም ሲሉ ተችተዋል፡፡

ከ400 በላይ አባላቱን የታዛቢዎች ምርጫ በተደረጉባቸው የአዲስ አበባ አካባቢዎች ማሰማራቱን የጠቆሙት የመኢአድ ፕሬዚዳንት አቶ ማሙሸት አማረ በበኩላቸው፤ ምርጫ ሳይከናወን በ2002 ታዛቢ የነበሩ ግለሰቦች በዘንድሮ ምርጫም እንዲቀጥሉ መደረጉን ይናገራሉ፡፡

የህዝብ ታዛቢዎች ምርጫ ገና ከጅምሩ እንከን ነበረበት የሚሉት አቶ ማሙሸት፤ ህብረተሰቡ ታዛቢዎቹን እንዲመርጥ በቂ ቅስቀሳ አለመደረጉንና በዚህም የተነሳ በየጣቢያው ከ20 እና 30 የማይበልጡ ሰዎች መገኘታቸውን ይገልፃሉ፡፡ ባለፈው ምርጫ ታዛቢ የነበሩ ግለሰቦች ድምፀ ውሳኔ ሳይሰጥባቸው በታዛቢነት እንዲቀጥሉ ተደርጓል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ከፓርቲው የተወከሉ ግለሰቦች ያሰባሰቡት መረጃ ለህዝብ ይፋ ከተደረገ በኋላ ቅሬታችንን ለምርጫ ቦርድ እናቀርባለን ብለዋል፡፡

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ወረዳ 8 ተገኝተው መታዘባቸውን የተናገሩት፣ የአንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ የውጭ ግንኙነት ኃላፊ አቶ ዳንኤል ተፈራ፤ በአብዛኛው በስብሰባ ቦታው የነበሩት እናቶች መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ መድረክ ላይ የነበሩት ግለሰቦች የህዝብ ታዛቢዎች ምርጫ እንደሚካሄድ አስተዋውቀው የእለቱ ፕሮግራም መጀመሩን የጠቆሙት አቶ ዳንኤል፤ ከተሰባሳቢው መሃል ግለሰቦች እየተጠቆሙ ይመረጣሉ የሚል ግምት የነበረኝ ቢሆንም የተደረገው ግን ከገመትኩት ውጭ ነው ይላሉ፡፡ "መድረክ ላይ የነበረው ሰብሳቢ በቀጠናው ላሉ ጣቢዎች 60 ሰዎች እንደሚስፈልግ አስተዋውቆ ስም ዝርዝራቸውን መጥራት ጀመረ፤ ከተጠሩት 60 ግለሰቦች ውስጥ በእለቱ የተገኙት 22 ያህል ብቻ ነበሩ" ያሉት አቶ ዳንኤል፤ የቀሩት ሰዎች ምን ይሁኑ ሲባል አንዳንዶች እየተነሱ "በቃ እኛ እናውቃቸዋለን፤ ባይመጡም ተቀበሏቸው" ይሉ እንደነበር መታዘዛቸውን ገልፀዋል፡፡ በኋላ ላይ ተቃውሞ በመቅረቡ "ከቤቱ ይመረጡ" ተብሎ 5 ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ሰዎች ወደ መድረኩ እየሄዱ በሹክሹክታ ከጠቆሙ በኋላ "በቃ 60 ሰው ሞልቷል፤ መልካም የምርጫ ጊዜ ይሁንልን" ተብሎ ስብሰባው ተበተነ ሲሉ አቶ ዳንኤል የታዘቡትን ተናግረዋል፡

> "ከዚህ ቀደም በነበሩት ምርጫዎች የተደረገው የኢህአዴግ አባላትን በታዛቢነት የማስመረጥ ልምድ በዚህኛው ምርጫ ላይም ተደግሟል"

"ከዚህ ቀደም በነበሩት ምርጫዎች የተደረገው የኢህአዴግ አባላትን በታዛቢነት የማስመረጥ ልምድ በዚህኛው ምርጫ ላይም ተደግሟል" ያሉት ደግሞ የኢዴፓ አመራር አባል አቶ አዳነ ታደሰ ናቸው፡፡

ኢዴፓ የወከላቸው የምርጫ ታዛቢዎች፤ የኢህአዴግ አባላት የሆኑ ግለሰቦች በታዛቢነት መመረጣቸውን እንደተመለከተ ለፓርቲው ሪፖርት ማድረጋቸውን የተናገሩት አቶ አዳነ፤ በተደጋጋሚ ተመሳሳይ ሰዎች እንዲመረጡ መደረጋቸው የምርጫውን ተአማኒነት የሚያሳጣና በህዝብ ዘንድ ጥርጣሬ የሚፈጥር ነው ብለዋል፡፡

እንዲህ አይነት ችግር እንዳይፈጠር እጩዎች አስቀድሞ ታውቀውና ተገምግመው ለህዝብ ምርጫ ይቅረቡ የሚል ሃሳብ ለምርጫ ቦርድ አቅርበን ነበር ያሉት የፓርቲው አመራር አባል ግን ቦርዱ ሃሳባችንን ውድቅ አድርጎታል ብለዋል፡፡

የምርጫ ቦርድ ፅ/ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ ወንድሙ ጎላ በበኩላቸው፤ የህዝብ ታዛቢዎቹን ህብረተሰቡ ራሱ ነው የመረጠው ብለዋል፡፡ ቦርዱ በሬዲዮና በቴሌቪዥን ስለታዛቢዎች ምርጫ ማስታወቂያ በማስነገሩም በመላ ሃገሪቱ ያሉ ዜጎች ተወካያቸውን በነቂስ ወጥተው እንደመረጡ ም/ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

ቦርዱ ቀደም ብሎ የጊዜ ሰሌዳ አውጥቶ ለሚመለከታቸው ሁሉ ማሰራጨቱን የጠቆሙት ኃላፊው፤ የታዛቢዎች ምርጫን በተመለከተ በሚዲያ በቂ ማስታወቂያ በመነገሩ፣ ፓርቲዎች በደብዳቤ ጥሪ አልደረሰንም ሲሉ የሚያቀርቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም ብለዋል - መድረክ ለቦርዱ በደብዳቤ ቅሬታውን ማቅረቡን በመጠቆም፡፡

በአመራርጥ ሂደቱ ተቃዋሚዎች የጠቀሱትን ችግር በተመለከተም፣ የምርጫ ጣቢያ በትክክል ተጠቅሶ ለሚመጣ አቤቱታ ቦርዱ አጣርቶ እርምጃ እንደሚወስድ አቶ ወንድሙ አስታውቀዋል፡፡

# አዲስ አድማስ

## የግጥምና የአጭር ልብወለድ ውድድር

አዲስ አድማስ ጋዜጣ የተመሰረተበትን የ15ኛ ዓመት በዓል ምክንያት በማድረግ የተለያየ ደረጃ ያላቸው ዘመናዊ የሞባይል ቀፎዎች የሚያሸልም የግጥምና የአጭር ልብወለድ ውድድር ለማካሄድ አቅደናል፡፡ በውድድሩ ለመሳተፍ አቅሙና ፍላጎቱ ያላችሁ በሙሉ በአንዱ ወይም በሁለቱም የስነ-ፅሑፍ ዘርፎች እንድትወዳደሩ ተጋብዛችኋል፡፡

- ግጥሙም ሆነ አጭር ልብወለዱ ያለ ምንም ገደብ በማናቸውም ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የሚያጠነጥን ይሆናል፡፡ ሆኖም በግምገማ ወቅት ለመሰረታዊ የስነ-ፅሁፍ አላባውያን፣ ለሃሳብ ጥልቀትና ምጥቀት እንዲሁም ለቋንቋ አጠቃቀምና ውበት ትኩረት ይሰጣል፡፡
- ለውድድር የቀረቡት ሥራዎች በስነ ፅሁፍ ባለሙያዎች በተዋቀረ ገለልተኛ ኮሚቴ ተገምግመው አሸናፊዎቹ ይለያሉ፡፡
- ከ1-3ኛ የወጡት የሥነ-ፅሁፍ ሥራዎች ለበዓሉ በምናወጣው ልዩ እትም መፅሄትና ጋዜጣ ላይ ይታተማሉ፡፡
- ተወዳዳሪዎች የሚያቀርቧቸው ሥራዎች ከዚህ ቀደም በማናቸውም ሚዲያዎች ያልወጡና አዲስ (ኦሪጂናል) መሆን ይገባቸዋል፡፡ ስራዎቹ በፌስ ቡክ፣ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ወይም በህትመት ውጤቶች የቀረቡ መሆናቸው ከታወቀ ወዲያውኑ ከውድድር ውጭ ይደረጋሉ፡፡
- ሥራዎቻቸውን በአካል ወይም በሃርድ ኮፒ የሚያመጡልን ተወዳዳሪዎች የማይመለስ ኮፒ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
- ለግጥም - ከ4 ገፅ፣ ለአጭር ልብወለድ - ከ8 ገፅ መብለጥ አይኖርበትም፡፡
- በግጥምም ሆነ በአጭር ልብወለድ ከ1-3 የወጡ አሸናፊዎች ስም ዝርዝር በጋዜጣው ላይ ይፋ የሚደረግ ሲሆን የጋዜጣው 15ኛ ዓመት በዓል በሚከበርበት ምሽት የሽልማቱ ሥነ-ስርዓት ይካሄዳል፡፡

ተወዳዳሪዎች ጽሑፎቻቸውን ይሄ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ በአካል ወይም በኢሜይል ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

ለውድድር የሚቀርቡ ስራዎች የፀሃፊውን ትክክለኛ ሙሉ ስም እንዲሁም የስልክና የኢሜይል አድራሻ መያዝ ይገባቸዋል፡፡

መልካም ዕድል!

አድራሻችን፡- ካዛንቺስ፣ ከሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ጀርባ


email addisadmass@ethionet.et

ለተጨማሪ መረጃ፡- በ0911811859 ይደውሉ


SOLUTIONS WORK
BETTER
WHEN OFFERED
TOGETHER
QUALITY SERVICE GUARANTEED
Like us on Facebook
letter mail
door to door service
parcel mail
transport service
express mail service
financial solutions
ETHIOPIAN POSTAL SERVICE ENTERPRISE
Head office: P.O.Box 5555, Tel: 251 11 5515011
የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት
ETHIOPIAN POSTAL SERVICE ENTERPRISE

# INTERCONTINENTALADDIS HOTEL

Addis Ababa







Merry Christmas and Happy New Year

The World Luxury Awards is described as the Oscars of the hospitality industry is known as the highest accolade that properties can receive.The nominees are judged for service excellence and best leadership quality or excellent management performance. The winners are voted by tourism industry leaders and top hotel professionals as well as guests who stay at the properties.

So Intercontinental Addis is selected as the best Hotel in Ethiopia and Top ten in Africa being shown in the world record.

This great news would be magnificent not only for the hotel. It will be very significant for the country as to put the representation to attract potential tourists being set in mind that we have hotels recognized in the region by the World Luxury hotel award being shown in the world record.

Intercontinentaladdis Hotel|Kazanchis Area| Guinea Conakry Street| P.O.BOX 5907|AddisAbaba|Ethiopia|
Tel: - +251-115-180444|+251-911-402695 Fax: - +251-115-540090 www.intercontinentaladdis.com

ርዕሰ አንቀፅ

# መሰላል ያላንሸራተተው ሁሌ ጫፍ የሚወጣ ይመስለዋል

## የህንዶች አባባል

ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት የውሃ ኤሊ የመውለጃዋ ጊዜ ደርሶ ኖሮ ከውሃው ወጥታ ወደ ባህሩ ዳርቻ ትሄዳለች፡፡ይቺ ኤሊ ቀስ እያለች በረጅሙ የአሸዋ መንገዷ ስታዘግም ሁለት ጓደኛሞች ያዩዋታል፡፡

አንደኛው ፤ "ይቺ ዔሊ ወዴት ነው የምትሄደው?" ይላል፡፡

ሁለተኛው፤ "የመውለጃ ጊዜዋ ደርሶ ይሆናል"

አንደኛው፤ "የመውለጃዋ ጊዜ ቢደርስ ወደ አሸዋው ምን ያስኬዳታል? መኖሪያዋ ውሃ ውስጥ ነው፡፡ እዚያው ወልዳ ተገላግላ እርፍ አትልም እንዴ?"

ሁለተኛው፤ "ለምን ውሃ ውስጥ እንደማትገላገል አላውቅም፤ የማውቀውና ሰዎች ሲሉ የሰማሁት ግን፤ ኤሊ የመውለጃዋ ጊዜ ሲደርስ ወደ ባሕሩ ቅርብ ዳርቻ አይደለም የምትጓዘው፡፡ ከውሃው እጅግ እርቃ ወደማይታይ አቅጣጫ ነው የምትሄደው"

"ልጆችዋን እሩቅ ቦታ ሄዳ የምትገላገል ከሆነ፤ በኋላ እንዴት አድርገው ልጆችዋ ከሷ ጋር ይገናኛሉ? እናታቸው በባሕሩ ውስጥ መሆኗንስ እንዴት ያውቃሉ?"

ይህ ጥያቄ በጣም ውስብስብና በቀላሉ የሚፈታ ስላልሆነላቸው በአቅራቢያው ወደሚገኝ አንድ ጠቢብ ዘንድ ሄደው ሊጠይቁ ይስማማሉ፡፡

ጠቢቡ ቤት ሄደውም፤ "ጠቢብ ሆይ! አንዲት የውሃ ኤሊ አየን፤ ከውሃው ወጥታ ወደ አሸዋው ዘልቃ እርቃ ሄደች፡፡ በኛ ግምት የመውለጃዋ ቀን ደርሶ ይሆናል ተባባልን፡፡ ግን አንድ ጥያቄ አነሳን፡ ፡ ወልዳ ወደ ባሕር ስትመለስ ልጆችዋን ማን ያመጣላታል? መቼም ህፃናት ናቸውና አውቀው ወደ ባሕሩ አይመጡም፡፡ ደግሞስ ያን ያህል ሰፊ ባሕር ውስጥ እናታቸው የት ትኑር የት እንደምን ያውቃሉ " ሲሉ ጠየቁት፡፡ ጠቢቡም "የአምላክን ተአምር የምታደንቁት እነዚህን አይነት ጉዳዮችን ለመመርመር ስትችሉ ነው፡፡ ኤሊዋ ልጆችዋን የምትወልደው እንዳላቻሁት ከባሕሩ ራቅ ያለ ቦታ ሄዳ ነው፡፡ እንዳላችሁትም ከተገላገለች በኋላ የባሕሩ ዳርቻ አሸዋ እንዲሞቃቸው እዚያው ትታቸው ነው ወደ ባሕሩ የምትመለሰው፡፡ ልጆችዋ እስኪጠነክሩ ድረስ እዚያው አሸዋው ላይ ይቆዩና ሰፊውን አሸዋ አቋርጠው ወደ እናታቸው ይመለሳሉ፡፡ የተፈጥሮ ህግ ስለሆነ ያለ ጥርጥር በባሕሩ ውስጥ እናታቸው የቱ ጋ እንዳለች ያውቃሉ፡፡ ዋና አስገራሚ ነገር ግን ወደ ባሕሩ በሚመጡ ጊዜ መንገድ ላይ አደጋ መኖሩ ነው፡፡ በባሕሩ ዳርቻ ላይ የኤሊ ጫጩት እየተመገቡ የሚኖሩ ወፎች አሉ፡፡ ከጫጩቶቹ መካከል በወፎቹ ከመበላት ተርፈው እናታቸው እቅፍ ውስጥ ለመግባት የሚችሉት ጥቂቶቹ የታደሉቱ ናቸው፡፡ ይህ የአምላክ ስርዓተ ተፈጥሮ ነው፡፡ ትላንት እንደዚያ ነበረ፤ ዛሬም አለ፤ ነገም በአግባቡ ይቀጥላል፡፡" አላቸው፡፡

የፍጥረታትን ተዓምር እያደነቁ ወደመጡበት ተመለሱ፡፡

***

በዓለም ላይ በዚህም ቢሉት በዚያም ከመሆን የማይቀር ነገር አለ፡፡ መንግስታት ይለወጣሉ፤ አገሮች ባሉበት ይቆያሉ፡፡ የሚሠሩ ያገኛሉ፡፡ ዳተኞች ባዶ እጃቸውን ይቀራሉ፡፡ የሚጥሩ ዳር ይደርሳሉ፡፡ የተኙ ወደ ኋላ ይሄዳሉ፡፡ ይሄ ተፈጥሮአዊ የሆነው ነገር አይቀሬ ነው፡፡ ከኤሊ ጫጩቶች መካከል ተርፈው ለእናታቸው የሚኖሩ ጥቂቶቹ ይሁኑ እንጂ ይኖሩ ዘንድ የተፈቀደላቸው የታደሉ ናቸው፡፡ ያልታደሉት ባጭር ይቀጫሉ፡፡ ይህ ህግ ሁሌም የሚኖር ነው፡፡ ሰው የሚሰራው ነገር ተጨማሪ ነው፡፡ ያም ሆኖ

"አለ አንዳንድ ነገር

በዚህ ቢሉት በዚያ ከመሆን የማይቀር" ይላሉ ደራሲ ከበደ ሚካኤል፡፡ በዚህ ውስጥ የተቃራኒዎች አንድነትና ትግል ሁሌም አይቀሬ ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ መግዛቱን ለመቀጠል ተገዢዎች የኛም ፓርቲ የገዢነት ቦታ ሊኖረው ይገባል በማለት እስኪሸናነፉና እስኪለይላቸው ጉዞአቸውን ይቀጥላሉ፡፡

"ልምድን ከሩቅ ሆነህ አታየውም፤ ሲከሰት ግን መኖሩን ታውቃለህ" ይላሉ ፈረንጆች፡፡ ለመማር ዝግጁ የሆነ ባወቀው ይጠቀማል፡፡ አትማር ያለው ባወቀውም ይደነቁራል፡፡ በሀገራችን ብዙ ፓርቲዎች ተወልደዋል፡፡ ብዙዎች ሞተዋል፡፡ አንዳንዶች ቀንቷቸዋል፡፡ አንዳንዶች በአጭር ተቀጭተዋል፡፡ የሁሉም የጋራ ሀብት ግን ከኖሩት አለመማር ሆኖ ታዝበነዋል፡፡ አሸናፊው ድሉን ከማሸብረቅ በቀር የሄደበትን መንገድ ዳግመኛ ለመመርመር አይቃጣውም፡፡ ተሸናፊው ቂም በቀሉን ከማመንዠክ እና ጊዜ ከመጠበቅ በቀር ያለፈውን ሁኔታ አጥንቶ በወጉ ለነገ ለመዘጋጀት ከቶም ልቦና የለውም፡፡ ይህ ሀቅ ሁሌም ምርጫ በመጣ ቁጥር የሚያጋጥመው እውነታ ነው፡፡ ትላንት በምርጫው አሸናፊ ነኝ የሚለው ወገን ለአሸናፊነት ሁሌም የታጨሁና ሁሌም የሚሳካልኝ ነኝ የሚለውን አስተሳሰብ የማይለወጥ እውነታ አድርጐ መውሰዱን አይን ካለን እናያለን፡፡ በአንፃሩ ትላንት በምርጫው ተሸናፊ የሆነው ወገን ደግሞ በመጭበርበር ተሸነፍኩ እንጂ ልክ ነበርኩ የሚለውን ሃሳቡን ሳይለውጥ አምስት አመት ይኖራል፡፡ በኢትዮጵያ ሥርጉ ካልደረሰ በርበሬ አይቀነጠስም ይባላል፡፡ አድፍጦ፣ አሳቻ ጊዜ መርጦ ለማነቅ ጀግና መባል አንዱና ዋነኛው የትግል ዘዴ በሆነበት ሀገር፣ የዲሞክራሲ እውንነት ሁሌም ጥያቄ ውስጥ ነው፡፡

ያለ ዲሞክራሲያዊ መስተጋብር ህይወት የአዘቦት መንገዷን እንጂ የተለወጠ ጐዳና ወይም እግረ መንገድ እንኳ ልትቀዳጅ አይቀናትም፡፡ የትግሉን ሂደት ከማየት ይልቅ ስወለድም እንዲህ ነበርኩ ማለትም አጉል መመካት ነው ይሉናል አበው ጠበብት፡፡ እኛ ብቻ ነን ለዚህ ስልጣን የተቀባን የሚለው ሃሳብ ግዘፍ ነስቶ የምናየው ለዚህ ነው፡፡ ከዚህ ይሰውረን ብለን እናማትብ፡፡ አንድ የፖለቲካ ድርጅት በእውነትም ሆነ በውሸት ምርጫ ሲያሸንፍ "ፍፁም ስለሆንኩ አሸነፍኩ" የሚል አስተሳሰብ ውስጥ መዋኘቱ አይገርሜ ነው! ግቡን መምታቱ ያላጋጠሙትን አሊያም አጋጥመውት ያልዘገባቸውን መንሸራተቶችና መሰናክሎች ወይም ሰንካላ እድሎች እንዲረሳ የደረሰበት ወንበር ክፉ ንቀት ይሰጠዋል! ዛሬ እዚህ የደረስከው በሠራኸው ጥሩም፣ መጥፎም ነገር ነው፡፡ የሚለውን ልብ አይልም፡፡ "መሠላል ያላንሸራተተው ሁሌ ጫፍ የሚወጣ ይመስለዋል" የሚለው ተረት ከላይ የተጠቀሰውን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡

"ጥሩው ብቻ አይደለም እዚህ ያደረሰህ

መጥፎም ነው እኮ ያንተ ማንነትህ" እንደማለት ነው በግጥም ሲለገጥ፡፡




ሥራ አስኪያጅ፡- ገነት ጎሳዬ
(ልደታ ክ/ከ ቀበሌ 04/06 የቤ.ቁ.581) ስልክ 0911-936787
ዋና አዘጋጅ፡- ነቢይ መኮንን
(ቂ/ክ/ከ ቀበሌ 08/09 የቤት.ቁ.213)
ም/ዋና አዘጋጅ፡- ኢዮብ ካሣ
ከፍተኛ አዘጋጅ፡- ሰለሞን ገ/እግዚአብሔር
አዘጋጅ፡- ኤልሳቤት ዕቁባይ
ታኅሣሥ 29 ቀን 1992 ዓ.ም ተመሰረተ፡፡ ዘወትር ቅዳሜ የሚታተም ሳምንታዊ ጋዜጣ
አሣታሚ ፡- አድማስ አድቨርታይዚንግ ኃ.የተ.የግ.ማ.
አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 17 / የቤት ቁ.984
ከፍተኛ ሪፖርተሮች፡- መንግስቱ አበበ፣ ግሩም ሠይፉ፣
አበባየሁ ገበያው ፣ መታሰቢያ ካሳዬ፣ናፍቆት ዮሴፍ፣ አለማየሁ አንበሴ
ሌይ አውት ዲዛይነር ፡- ኮከ አሰፋ፣ ንግሥት ብርሃነ
አርቲስት ፡- ሥርፀድንግል ጣሰው
ሽያጭና ስርጭት ፡- ሰለሞን ካሣ
ፎቶግራፈር ፡- አንተነህ አክሊሉ
ዌብፔጅ ፡- አስቴር ጎሳዬ
ኮምፒውተር ጽሑፍ ፡- የወብዳር ካሣ፣ ሃና ገ/ሚካኤል
አድራሻ፡- ካዛንችስ፤ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር ገባ ብሎ፣ ከጤና ጣቢያው ጀርባ
ቂርቆስ ክ/ከ ቀበሌ 31 ፤ የቤት ቁ.376
ስልክ፡- 0115-155-222/ 0115-153-660 ሞባይል፡- 0921-622-040/
0911-201-357 / 0935-98-74-44 / 0118699024
ፋክስ፡- 0115-547373 ፖ.ሳ.ቁ 12324
E-mail :- admassadvert@gmail.com/ addisadmass@ethionet.et
website www.addisadmassnews.com



# “የበጎቹ ጠባቂ ሆይ፣‘ወየት’ ነህ!”

ኤፍሬም እንዳለ




እንዴት ሰነበታችሁሳ!

ሰውየው አእምሮ ሀኪም ዘንድ ይሄድና... “ዶክተር፣ መጥፎ ተግባራት እየፈጸምኩ ህሊናዬ እየረበሸኝ ነው...” ይለዋል፡፡

ዶክተሩም... “እና መጥፎ ድርጊት ከመፈጸም የሚከላከል ህክምና እንዳደርግልህ ነው የምትፈልገው?” ይለዋል፡፡ ሰውየውም... “አይደለም...” ይላል፡፡

ዶክተሩም... “ታዲያ ምን ፈልገህ መጣህ?” ይለዋል፡፡

ሰውየው ምን ቢል ጥሩ ነው...“ህሊናዬን ከሥሩ ነቅለህ አውጣልኝ!”

‘አልሰሜን ግባ በለው’ አሉ...እኛ ዘንድ ቢመጣ ህሊና እያለም እንዴት ‘ህሊናቢስ’ መሆን እንደሚቻል ‘በስምንተኛ ዲግሪ’ ደረጃ እናሰለጥነው ነበር፡፡ የምር ግን የህሊና ነገር እኮ እኛ አገር የሆነች ተረስታ ከአሮጌ አንሶላ ጋር የተጠቀለለች ነው የምትመስለው፡፡

እናላችሁ...“ትንሽ ህሊና እንኳን የለህም!” ብሎ አማረኛ ቀረ፡፡ ህሊና የሰው ስም ብቻ የሚመስለን እየበዛን ነዋ! (“ህሊና ቢኖረኝ እዚህ አገር ታገኙኝ ነበር ወይ...” ያልከን ወዳጃችን በእግርህ አስነካኸው እንዴ!)

እኔ የምለው...እንግዲህ ጨዋታን ጨዋታ ያነሳው የለ...ነገርየው እንዴት ነው...‘ጉልቤ’ ነገሮች በዙብና! ልክ ነዋ...ጉልቤነት ማለት እኮ የግድ ‘አገጭ ማጣመም’፣ ጥርስን ‘በመሀረብ ማስቋጠር’ ምናምን ማለት ብቻ አይደለም፡፡ የዘንድሮ ‘ጉልቤነት’... አለ አይደል...መአት መልክ አለው፡፡

እንግዲህ ጨዋታም አይደል...ይቺን ስሙኝማ... የሆነ ሚኒባስ ታክሲ ላይ ያየነው ‘ጥቅስ’ ነው... ‘ጥቅሱ’ ምን ይል መሰላችሁ... (ምንም ደስ ባይልም መነገር አለበት፣) “አፍህን ከምትከፍት ሱቅ ክፈት” ይላል፡፡

እናላችሁ...እንዲህ አይነት በህዝብ መገልገያ ላይ ከእግር ጥፍር እስከ ራስ ጸጉር ‘ሙልጭ’ የምንደረግበት ዘመን ላይ ደርሰንላችኋል፡፡ የምር ግን... እንደዚህ አይነት ነገር መጀመሪያ ስናይ ፈገግ እንደ ማለት ይቃጣናል፡፡ ግን... እኛም ተሰዳቢዎች መሆናችን ሲገባን...

“የበጎቹ ጠባቂ ሆይ፣ ‘ወየት’ ነህ!” እንላለን፡፡

ምን መሰላችሁ...‘የቤትሽን ዓመል እዛው’ ‘አትንጣጪ’ ምናምን ሲባል ዝም ተብሎ ተከረመና አሁን ደግሞ “አፍህን አትክፈት...” ወደ መባል ደርሰናል፡፡

የምር እኮ...ነገርየው በዚሁ ከቀጠለ ...ቀስ ብሎ...በአንድ ወቅት እዚች ዋና ከተማችን ጎራ ያለ የገጠሩ ሰውዬ... “አዲስ አበባ ገዳይ ጠፋ እንጂ ሟች ብዙ ነበር!” ያለበት አይነት ስድብ ነገ ተነገ ወዲያ የማይለጠፍበት ምክንያት የለም፡፡ እነማ...እንደዚህ አይነት ነገር ሲበዛብን፣

“የበጎቹ ጠባቂ ሆይ፣ ‘ወየት’ ነህ!” እንላለን፡፡

የምር አስቸጋሪ ጊዜ ነው፡ የደንብ ልብስ የለበሱ በከተማው ጎዳናዎች በበዙበት ጊዜ፣ ማስቲካና መፋቂያ ሻጮች ሲሯሯጡ በምናይበት ጊዜ... አንዳንድ አካባቢ ተረጋግቶ መገበያየት እንኳን እያስቸገረ ነው፡፡ እኔ የምለው... እግረ መንገዴን... የገበያተኛ መዋከብ ‘የደንብ ጥሰት’ ለመሆን ያንሳል እንዴ!

በቀደም መርካቶ ዕቃ ቢጤ ለማየት ወጣ ብለን... “አይ መርካቶ!” ብለን ተመለስን እላችኋለሁ፡፡ የምር እኮ... የምንጣፍ ሱቆች በበዙበት አካባቢ መራመድ እስኪያቅታችሁ ድረስ ትከበባላችሁ፡፡ ‘የደላላው’ ብዛት! የሆነ ሱቅ ውስጥ ለመግባት ስታስቡ ወጣት ደላሎች እየተከተሉ... “መጋዘኑ እዛ’ጋ ነው፣ ቅናሽ አለው...” “እዛ ሱቅ ያለው አሪፍ ነው...” ምናምን እየተባለ እስኪሰለቻችሁ ድረስ የሚቀባበሏችሁ ወጣቶች ብዛታቸው... አለ አይደል... ያበሳጫል ብቻ ሳይሆን ‘ያስፈራል’ ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡

እንግዲህ ይህ ሁሉ ሲሆን በአካባቢው የደንብ ልብስ የለበሱ ሰዎች ውር፣ ውር ይታያሉ— የሚያስጥል የለም እንጂ፡፡ እናላችሁ... ገበያተኛ ሲጉላላ፣ ደንብ አስከባሪውም ዝም፣ ነጋዴውም ዝም፣ ሁሉም ዝም ሲሆን... አለ አይደል...

“የበጎቹ ጠባቂ ሆይ፣ ‘ወየት’ ነህ!” እንላለን፡፡

ስሙኝማ...እንግዲህ ጨዋታም አይደል...እዚህ አገር መድረክ ላይም ‘ሙልጭ’ ተደርጎ መሰደብ እየተለመደ ነው፡፡ መጀመሪያ ሰብሳቢው...“መሀላችን የተሰገሰጉ የራሳቸው ዓላማ ያላቸው...” ምናምን እያለ ‘ሆረር’ ምናምን ነገር ይለቅባችኋል፡፡

‘አስተያየት ሰጪው’ ተነስቶ... “በተባለው ላይ የምጨምረው የለኝም...” ይልና “ዕድገታችንን ለመግታት የሚፍጨረጨሩ አንዳንድ የስብሰባው ተካፋዮች ላይ እርምጃ ለምን እንደማይወሰድ...” በቁጭት ይጠይቃል፡፡ ይህ ሁሉ ሲሆን እከሌ፣ እከሌ ተብሎ እስካልተጠቀሰ ድረስ አንዳንድ “...የስብሰባው ተካፋዮች...” የሚለው ሁላችንንም ስለሚመለከት...አለ አይደል...

“የበጎቹ ጠባቂ ሆይ፣ ‘ወየት’ ነህ!” እንድንል ያደርገናል፡፡

አሀ... ማን በበላው ማን ‘ራዳር’ ውስጥ ይገባል! ልጄ ዘንድሮ ‘...ሁሉም እንደ የሥራው...” ምናምን የሚል አባባል፣ ‘ጥቅስ’...ነገር አይሠራም፡ ፡ ልጄ...ዘንድሮ ሰው ‘ባልሠራው’ የሚበላበት፣ ‘ባልሠራውም’ የሚበላውን የሚያጣበት ዘመን ነው፡ ፡

ይቺን ስሙኝማ...የመንገድ ግንባታ ሥራ ላይ ነው አሉ፡፡ እናላችሁ...አንዱ ሠራተኛ አካፋ አልነበረውም፡፡ ታዲያ...አለቃውን፣ “አካፋ የለኝም...” ይለዋል፡፡ አለቅየውም...“ታዲያ ምን ያነጫንጭሀል! አካፋ ከሌለህ ሥራ አትሠራ!” ይለዋል፡፡ ሰውየው ምን ብሎ ቢመልስ ጥሩ ነው... “ታዲያ እንደ ሌሎቹ ሠራተኞች ምን ተደግፌ ልቁም?” ብሎ አረፈላችሁ፡፡

እናማ...በየቢሮው፣ በየሥራ ቦታው ‘አካፋ ተደግፈን’ የምንቆም መአት ነን፡፡

ይቺን አሪፍ ነገር ስሙኝማ...ሰውየው ለጓደኛው ሲደውል ከጀርባ ድምጽ ይሰማል፡፡ “የምን ጫጫታ ነው የምሰማው?” ይለዋል፡፡ ጓደኛየውም... “የእህቴን ልደት ዓመታዊ በዓል እያከበርን ነው...” ይለዋል፡ ፡ ሰውየውም ግራ ይገባዋል፡፡ “የእህቴን ልደት ዓመታዊ በዓል ብሎ ነገር ምንድነው? ወይ ልደት ታከብራለህ፣ ወይ ዓመታዊ በዓል ታከብራለህ፡፡ ሁለቱ የሚገናኙ አይደሉም...” ይለዋል፡፡

ጓደኛየው ምን ብሎ ቢመልስ ጥሩ ነው...“አይ ሞኞ...የእህቴን አሥራ ስምንተኛ ዓመት ልደት አሥራ አምስተኛ ዓመታዊ በዓል እያከበርን ነው...” ብሎት አረፈ፡፡ አሪፍ አይደል!

የዕድሜ ነገር ከተነሳ... ይቺን ስሙኝማ...“በቀደም ሀያ ዘጠነኛ ዓመቴን ሳከብር ለምንድነው ስጦታ ያልሰጠኸኝ?” ብትለው እሱዬው... “ረሳሽው እንዴ! የዛሬ አምስት ዓመት ሀያ ዘጠነኛ ልደትሽን ስታከብሪ ሸቶ አልሰጠሁሽም?” ብሏት አረፈ፡፡

እናላችሁ...ጉልቤነት መልኩን እየለዋወጠ መከራችንን እያበላን ነው፡፡ ቤት አከራይ በቀን ሁለት ባሊ ውሀ ብቻ እየፈቀደ፣ መብራት በሦስት ሰዓት ላይ እያጠፋ፣ “ከአንድ ሰዓት በኋላ ማምሸት ክልክል ነው...” አይነት ክፉ ሚስት እንኳን የማታስበው ‘ህግ እያረቀቀ’ ይቆይና አንድ ቀን ማታ በር ይንኳኳል፡ ፡ እናንተም ስትከፍቱ አከራያችሁ ተኮሳትረው ቆመዋል፡፡ እናንተም...“ደህና አመሹ፣ ምነው ደህና?” ስትሉ ምን ትባሉ መሰላችሁ...“ኪራይ ላይ ከሰኞ

ጠባቂ ወደ ገፅ 22 ዞሯል

## ተሸሳሚው

የአዳራሹ ስፋት ለጉድ ነው፡፡ ወደ አምስት ሺህ የሚደርሱ መጻሕፍትን በውስጡ የያዘ አይመስልም፤ ከሃያ እስከ ሰላሣ የሚደርሱ ተጠቃሚዎች መጻሕፍታቸው ላይ ተደፍተው በጥሞና እያነበቡ ነው፡፡ ፅዳቱ፣ በቂ አየር መኖሩ፣ ፀጥታው፣ በመጻሕፍት መደርደሪያዎች መካከል ያለው ሰፊ ክፍተት ሁሉ የጥሩ ቤተ መጻሕፍት ወግ እንዲኖረው አድርጓል፡፡

‹‹ቤተ መጻሕፍት ለአንድ አገር ወሳኝ ነገር እንደሆነ ማንም ያውቃል፡፡ ይህንን የመሰለ ከዚህ በፊት ያልተለመደ ዘመናዊ አሠራር በማየቴ እጅግ በጣም ተደስቻለሁ፡፡ ይህንን ቤተ መጻሕፍት ለዚህ ያበቃው አካል ምስጋና ይገባዋል›› ይላል ይርጋ ክብረት የተባሉ ተጠቃሚ በቤተ መጽሐፍቱ አስተያየት መስጫ ደብተር ላይ ያሰፈሩት ጽሑፍ፡፡ እኛም በመጀመሪያ እይታችን የተሰማን ስሜት ይህ ነው፡፡

ከመገናኛ አልታድ ሚካኤል የሚወስደውን መንገድ ይዘው ሲሄዱ ልክ የሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ መግቢያ በርን ጥቂት አለፍ እንዳሉ ወደ ቀኝ የሚታጠፍ መንገድ ያገኛሉ፡፡ እንደታጠፉ ከቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች አለፍ ብሎ ከሚታይ የወጣት ማዕከል ህንፃ ጀርባ ዛሬ የምናወራለት ቤተ መጻሕፍት መገኛ ነው፡፡ የቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ ስምንት የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የህዝብ ቤተ መጻሕፍት፡፡

በ2003 ዓ.ም የተመሰረተው ይህ ቤተ መጻሕፍት በቀን ሁለት መቶ ለሚደርሱ ተጠቃሚዎች የንባብ እና የውሰት አገልግሎት ይሰጣል፡፡ የውሰት አገልግሎት በዋናነት የሚሰጠው ግን በስሩ ላቋቋማቸው ወደ መቶ ሃምሳ ለሚደርሱ የቤተ መጻሕፍቱ ክበብ አባላት ነው፡፡ ‹‹የክበብ አባላቱ ለሚያገኙት አገልግሎት ተገቢውን መዋጮ ያዋጣሉ›› የሚሉት የቤተ መጻሕፍቱ ሠራተኛ የሆኑት ወ/ሮ ቤተልሔም ዘነበ እና ወ/ሪት ወይንዬ ዘነበ ናቸው፡፡

‹‹አንድ ተጠቃሚ የክበቡ አባል ለመሆን በወር አምስት ብር መክፈል ይኖርበታል፡፡ ክበቡ የሚመራው አባላቱ ባቋቋሙት ኮሚቴ ነው፡፡ መዋጮውንም የሚሰበስቡት ራሳቸው ናቸው፡፡ ብሩ ተሰባስቦ መጻሕፍት መገዛት አለበት ሲሉ ከእኛ አንድ ሰው አብሮ ይሄድና ግዢ ይፈፀማል፡፡ በቅርቡ በክበቡ ወደ አምስት መቶ የሚጠጉ መጻሕፍት ተገዝተዋል፡፡››

ይህ ቤተ መጻሕፍት በቦሌ ክፍለ ከተማ ሥር ከሚገኙ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት አብያተ መጻሕፍት መካከል የተሻለ የሥራ አፈፃፀም ካሳዩ ሦስት አብያተ መጻሕፍት ውስጥ አንዱ ነው ተብሎ ባለፈው አመት የዋንጫ ሽልማቱን ወስዷል፡፡

‹‹አራት ሠራተኞች ነን ያለነው፡፡ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ አገልግሎት እንሰጣለን፡፡ በሥራችን በጣም ደስተኞች ነን፡፡ አንድ ሰው የሚፈልገውን መጽሐፍ ጠይቆን ሰጥተነው፤ አንብቦ እውቀት ገብይቶ ሲሄድ እንደማየት የሚያስደስት ነገር የለም›› ይላሉ ቤተልሔም እና ወይንዬ ፈገግ ብለው፡፡የቤተ መጻሕፍቱን ስኬት ያዩ የሌላ ክፍለ ከተማ ሰዎች መጥተው ተሞክሮ ወስደዋል፡ ፡ ‹‹ከእነዚህ መካከል የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳዎች ይጠቀሳሉ›› ትለናለች ወይንዬ፤ ‹‹አዎ! ለመጡት ሰዎች ስለአገልግሎት አሰጣጣችን፤ ስለመጻሕፍት አያያዛችን እና ስለሪፖርት አቀራረብ ያለንን ልምድ አካፍለናል፡፡››

ቤተ መጻሕፍቱ ለህፃናትም ተገቢውን ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ከማቅረብ ጀምሮ ማንበቢያ ሥፍራ ለይቶ እስከማዘጋጀት ድረስ ያደረገውን ጥረት ለማየት ችለናል፡፡

ይሁን እንጂ አገልግሎት አሰጣጣቸው እንዲህ ያማረ ቢሆንም ብዙ ችግሮች አሉበት፡፡ ቤተ መጻሕፍቱ ውሃ የለውም፤ መፀዳጃ ቤት የለውም፡፡ አጥር የለውም፡፡ እንዲያው ዝም ተብሎ አውላላ ሜዳ ላይ የተቀመጠ ነው፡፡

‹‹ለመሆኑ ይህ አዳራሽ ለቤተ መጻሕፍት ተብሎ የተሠራ ነውን?››

‹‹አዎን!›› የእነቤተልሔም መልስ ነው፡፡

‹‹ታዲያ እንዴት እንዲህ አምሮ ከተሠራ በኋላ ውሃና መፀዳጃ ቤት እንዲሁም አጥር ተዘነጋ?››

‹‹የእኛም ጥያቄ ነው!›› ሁለቱም በአንድ ላይ የመለሱት መልስ ነው፤ ‹‹እንዲሟላልን እየጠየቅን ነው፡፡ ቤተ መጻሕፍቱ አጥር የሌለው ከመሆኑም በላይ የሌሊት ጥበቃ የለውም፡፡ የሌሊት ጥበቃ እንዲኖር ደግሞ የጠባቂ ቤት ያስፈልጋል ተባለ፡፡ ይሄንን ሁሉ በየጊዜው አቤት እያልን መልስ በመጠባበቅ ላይ ነን፡፡››

‹‹ከዚህም የከፋ ችግር አለ!›› ትላለች ቤተልሔም፤ ‹‹ቤተ መጻሕፍቱ እንዲህ አምሮ የሚታየው በጋ ላይ ነው፡፡ ክረምት ላይ ጣራው በጣም ያፈሳል፡፡ እኛም ዝናብ በጣለ ቁጥር መጻሕፍቱንና መደርደሪያዎቹን ስናንቀሳቅስ ነው የምንውለው፡፡ ይሄንንም አሳውቀናል፡፡ መልስ ግን አላገኘንም፡፡››

የቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ ስምንት የባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት የሕዝብ ቤተ መጻሕፍት የሚተዳደረው በወረዳው ሥር ነው፡ ፡ ነገር ግን ወረዳው ምንም ዓይነት ድጋፍ የማያደርግ ከመሆኑም በላይ ለቤተ መጻሕፍቱ ችግር ጆሮ ያለው አይመስልም፡፡

‹‹እኛን የሚጠሩን ለሪፖርት ወይም አዳራሹን ለስብሰባ ሲፈልጉት ነው፡፡ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ደክመን እየሠራን አዳራሹን ለስብሰባ ስለሚፈልገው እሁድ ግቡልን ይሉናል፡፡ ከዚህ ውጪ እኛን አይፈልጉንም፡፡ ሽሪ ሥራም እየሠራን አይመስላቸውም››

‹‹ለምን? እኮ ለምን?›› ይህን ጥያቄ የምንወረውረው ለቦሌ ክፍለ ከተማ የወረዳ ስምንት ሰዎች ነው፡፡ ዛሬም እንደከዚሁ ቀደሙ እንዲህ እንላለን፤ ‹‹በየት በኩል አለፋችሁና የቤተ መጻሕፍት ጥቅም ጠፋባችሁ!?››

*የጀርመን ባህል ተቋም ከብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት እና ቤተ መዛግብት ኤጀንሲ ጋር በመተባበር የቀረበ*

# ጣቢያውን የማይመጥን ፕሮግራም!

## “One’s in a Life”

አንዱአለም ናስር
andualemnassir@gmail.com

የቴሌቪዥን ስርጭቶች የሚተላለፉበት አንዱ መንገድ በጠፈር ላይ የሚገኙ ሳተላይቶችን በመጠቀም ነው፡፡ በዚህ መንገድ ለኢትዮጵውያን እንደ አማራጭ ሆኖ የቀረበ የቴሌቪዥን ጣቢያ ነው - ኢቢኤስ፡፡ ጣቢያው ከተመሰረተ ጀምሮ አስተማሪና አዝናኝ ፕሮግራሞችን በማቅረብ ከአማራጭም በላይ ለመሆን ችሏል፡፡ ለዚህም ምስክሩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ተቀባይነትን ማግኘቱ ነው፡፡

በቅርቡ በጀመረውና ምንም ኢትዮጵያዊ መልክ በሌለው ከውጭ በተቀዳ ፕሮግራሙ ምክንያት ግን ለትችት ተጋልጧል፡፡ በግል ምልከታዬ፣ ይህ ፕሮግራም ኢቢኤስን የሚመጥን አይደለም፡፡ እስቲ ፕሮግራሙ ለኔ የሰጠኝን ስሜት ላጋራችሁ፡፡ ቅዳሜ ህዳር 27 ቀን 2006 ዓ.ም 12፡00 የተጀመረውና 35 ደቂቃ የወሰደው ሙሉ ፕሮግራም የሚከተለውን ይመስላል፡፡

ፕሮግራሙ ሲጀምር አንድ የ17 ዓመት ልጃገረድ (ተረኛ ባለ ልደት ነች) በሚያምር ሰፊ አልጋ ላይ ተኝታ ያሳያል፡፡ ይህች ተረኛ ባለ ልደት ከተኛችበት ምቹ አልጋ እየተንጠራራች ተነስታ፣ በረጅም መስታወት ፊት በመቆም ጸጉራን በጣቶቿ በተን በተን ታደርግና፣ ቻፒስቲኳን ከመደርደርያው አንስታ ከንፈሯን ትቀባለች፡፡ ከዚያም ጓደኞቿ እቤቷ ድረስ በመኪናቸው መጥተው ይወስዷታል፡ ፡ (የዚህች ባለ ልደት ኑሮ እንኳን ለመኖር ለማሰብም ይከብዳል'ኮ! በቁጥርም ቢሰላ እንደሷ ባማረ አልጋ ላይ በምቾት የሚተኙ ኢትዮጵውያን ከመቶ አምስት መሙላታቸውን እንጃ፡፡ የቤታችን መስታወት'ኮ ግማሽ ፊታችንን ብቻ የሚያሳይ ነው፤ አለባበሳችንን እንኳ እድሜ ለከተማችን ባለመስታወት ፎቆች! ወደ ግራ ወደ ቀኝ እያልን አስተካክለን እንውላለን፡፡ እኛ 95 በመቶ ኢትዮጵያውያኖች እንግዲህ እንዲህ ነው ኑሮአችን!)

ከዚያም በሚያምረው የመኖሪያ አካባቢያቸው ለመዝናኛ ተብሎ በተከለለው ስፍራ ውስጥ ለምለም ሳር ላይ ከጓደኞቿ ጋር ሩጫ ሲወዳደሩ፣ በጀርባቸው ሲንደባለሉና የቅርጫት ኳስ ሲጫወቱ ይቆዩና፣ ተመልሰው በመጡበት መኪና ወደ ቤታቸው ይሄዳሉ፡፡ (እኛ 95 በመቶ ኢትዮጵያውያኖችስ? ...ሆ! እኛ'ኮ እንኳን ተከልሎልን ለምለም ሳር ላይ ልንጫወት በራሳችን ተነሳሽነት ሜዳ ብለን በሃሳብ መስመር የከለልነው አቧራማና ድንጋያማ ሜዳ ለልማት ተብሎ የታጠረብን ምስኪኖች ነን!)

ወደ ቤታቸው ከገቡም በኋላ ተጣጥበው፣ ለልደቷ ቁሳቁሶች ለመግዛት ተሰባስበው በመኪናቸው ይወጣሉ፡፡ ከዚያም በመሃል ከተማ ከሚገኙት ስመ ገናና ውድ ሱቆች ውስጥ ይገቡና እንኳን ከኪስ አውጥቶ ለመክፈል፣ ለማሰብ እንኳ በሚከብድ ዋጋ የሚፈልጉትን ገዝተው ይመለሳሉ፡ ፡ (እኛስ?... እኛ'ኮ አዲስ ልብስ የምንለብሰው አዲስ አመትን ጠብቀን ነው - እሱም ከሞላልን ነው፡፡ ታዲያ የ5 በመቶ ኢትዮ-አሜሪካኖችን ኑሮ እያየን መሳቀቅ አለብን እንዴ ጎበዝ!)

በመቀጠል ያቺ የታደለች ባለልደት ከጓደኛዋ ጋር ሆና ወደ ውበት ሳሎን በማምራት፣ ይህ ቀረሽ በማይባል ደረጃ ትዋብና መጥቶ የሚወስዳትን መኪና ትጠባበቃለች፡፡ መኪናው ሲያዩት ያምራል፤ ዋጋው ግን ያስፈራል! በሚሊዮን ብር የሚገመት ነው በተባለለት በዚህ መኪና፤ በግራና በቀኝ በጥቋቁር ሞተር ሳይክሎች በመታጀብ፣ ወደተዘጋጀላት የልደት አዳራሽ ትከንፋለች፡፡ ባለሚሊዮን ብሩ መኪና መንገዱን ዚግዛግ እየመታ፣ የሃን መብራቶቹን ብልጭ ድርግም እያደረገ፣ በጥሩምባው ከተማውን እያበጠበጠ ከአዳራሹ ደረሰ፡፡ ለልደቷ የተጋበዙ ጓደኞቿ በራፍ ላይ ተኮልኩለው ጠብቀው፣ አላሳፈሯትም፡፡ ገና ያልቾበትን መኪና ሲመለከቱ

ፕሮግራም ወደ ገፅ 22 ዞሯል

# የደርግ ዘመን የፈጠራቸው ቃል ግጥሞች

ባዩልኝ አያሌው

ስነቃል (Oral literature) የሰው ልጅ ራሱን ከሚገልጥባቸው፣ ስሜቱን ከሚነግርባቸውና ማንነቱን ከሚቀርስባቸው ባህላዊ እሴቶች አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ማህበረሰብና ስነቃል ያላቸው ቁርኝት እጅጉን ጥብቅ ነው፡፡ ለዚህም ነው የአንድን ማህበረሰብ ባህላዊ እሴቶች ማጥናትና መረዳት ማህበረሰቡን ማወቅ ነው የሚባለው፡፡ አይነቱና መጠኑ ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ቢለያይም ስነቃል የሌለው ማህበረሰብ የለም፡፡

የጽሑፌ ማጠንጠኛ ስነቃል፣ ከስነቃልም (በቅርጽ ግጥማዊ የሆነው) ቃል ግጥም (Oral poetry) ነው፡፡ ትኩረቴም በደርግ ዘመን በስርዓቱ ላይ በተቃውሞ የተነገሩት (በድጋፍ ከተነገሩት ይበዛሉና) ቃል ግጥሞች ናቸው፡፡ በዚህም በሰፊው የተነገሩ ጥቂት ቃል ግጥሞችን "የዘመኑን እውነት" (ግጥሞቹ የተነገሩባቸው ግፊቶች ዘመኑ ውስጥ አሉና) እማኝ አድርጌ እቃኛለሁ፡፡ ምክንያቴም በአንድ የአገዛዝ ዘመን የተነገሩ ስነቃሎች የአገዛዙን መንፈስ፣ የወቅቱን ማህበረሰብ አስተሳሰብና ስነልቡና እንዲሁም ለአገዛዙ የነበረውን ምላሽ በጉልህ ያሳያሉ ብዬ ማመኔ ነው፡፡ ነገሬን እንዲህ አስረድቼ "ይለፍ" አልነፈገምና ልቀጥል፡፡

ወታደራዊው የደርግ መንግስት የንጉሡን ስርዓት "አስወግዶ" ስልጣን በመያዝ ይህቺን ሀገር ለ17 ዓመታት ማለትም ከ1966 እስከ 1983 ዓ.ም አስተዳድሮአል፡፡ በእነዚህ ዓመታትም በሀገሪቱ የተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡ ከለውጦቹና ክንዋኔዎቹ መካከል ስርዓቱ ቀድሞ ያቀነቀነው የመሬት ለአራሹ አዋጅ፣ የእድገት በህብረት ዘመቻ፣ የሠፈራ ፕሮግራም፣ ቀይ ሽብር፣ ብሔራዊ ውትድርና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡

በዘመኑ የነበረው ማህበረሰብም እንደቀደሙት ዘመናት አባቶቹ ሁሉ እነዚህና ሌሎች ከስርዓቱ መለወጥ ጋር ተያይዘው የመጡ ክስተቶች ያሳደሩበትን የአዎንታም ይሁን የአሉታ፣ የድጋፍም ይሁን የተቃውሞ ስሜት በስነቃል፣ ከስነቃልም በቃል ግጥም ሲገልጽ ኖሮአል፡፡ በደርግ ዘመን የተነገሩት ቃል ግጥሞች በወቅቱ በመንግስት የተከወኑ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ለውጦችን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡ ትኩረቴ በተቃውሞ የተነገሩት ላይ መሆኑን ቀድሜ አትቻለሁና ወደነሱ ልለፍ፡፡ ከእነሱም በዘመኑ "ጉልህ" ክስተቶች በነበሩት ማለትም "ቀይ ሽብር"፣ "ሠፈራ" እና ጦርነት ላይ የተነገሩትን ላንሳ፡፡

በደርግ ዘመን በነበረው የ"ቀይ ሽብር ዘመቻ" ሳቢያ የበርካታ ዜጎች (በተለይ የወጣቶች) ህይወት አልፎአል፡፡ ይህ "ዘመቻ" በመላው ሀገሪቱ ሊባል በሚችል መልኩ የተካሄደ ሲሆን በዘመቻውም የጠፋው የሰው ሕይወት እጅግ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ነው፡፡ በዘመኑ የነበረው ማህበረሰብም "ዘመቻው" ያደረሰውን ጉዳትና ጉዳቱም የፈጠረበትን ሀዘንና ስሜት በተለያዩ የስነቃል አይነቶች በተለይም በቃል ግጥም ገልጾአል፡፡ በ"ቀይ ሽብር" ላይ ከተነገሩ ቃል ግጥሞች መካከል በጎንደር ከተማ የተነገሩትን ሁለት ቃል ግጥሞች እንመልከት፡፡

*መላኩ ተፈራ የእግዜር ታናሽ ወንድም*
*የዛሬን ማርልኝ የነገን አልወልድም*
*(ይህንን ማርልኝ ከእንግዲህ አልወልድም)*

ግጥሙ መላኩ ተፈራ ጎንደርን "ያስተዳድር" በነበረበት ዘመን የተነገረ ነው፡፡ መላኩ በጎንደር በርካታ የ"ኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ" (ኢህአፓ) አባላት የሆኑ ወጣቶች "እንዲገደሉ" እንዳደረገና "የፈለገውን የመግደልና የፈለገውን የማዳን" ስልጣን እንደነበረው ይነገራል፡፡ በዚህ ወቅት ነው አንዲት ልጇ ሊገደልባት የነበረች እናት ይህንን ግጥም የተናገረችው ይባላል፡፡ (ይባላል ነው!)

በግጥሙ ሴቲቱ "ማንም ከልካይ የሌለበትንና የፈለገውን የሚያደርገውን" መላኩን "የእግዜር ታናሽ ወንድም" አድርጋዋለች፡፡ ከዚህም ሌላ "ይህንን ማርልኝ" እንጂ "ከእንግዲህ አልወልድም" በማለት ሌላ ልጅ ላለመውለድ ቃሏን እስከመስጠት ደርሳለች፡፡ ይህ ግጥም የዘመኑ ማህበረሰብ በዘመቻው የደረሰበትን ጉዳትና ሰቀቀን በሚገባ ማሳየት የሚችል ነው፡፡ በዚያው በጎንደር (ቀይ ሽብር ከፍተኛ ጉዳት ካደረሰባቸው ከተሞች አንዷ ጎንደር መሆኗን ልብ ይሏል፡፡) የተነገረ አንድ ሌላ እንጨምር፡፡

*የ<u>ማራኪ</u> ጎመን አልበላም እርሜ ነው*
*ያ<u>ባሳሜል</u> ጎመን አልበላም እርሜ ነው*
*እሱ የበቀለው በወጣቶች ደም ነው፡፡*

ሁለቱ (የተሰመረባቸው) በጎንደር በ"ቀይ ሽብር" የተገደሉ ወጣቶች በጅምላ ይቀበሩባቸው የነበሩ ቦታዎች ናቸው፡፡ ይህንን የሚያውቀው ሀገሬው በሁኔታው የተሰማውን የመረረ ሀዘን ፊት ለፊት ሳይሆን አዙሮና አጠይሞ በግጥሙ ገልጾአል፡፡ የሀገሬው ጉዳይ ወይንም ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት ስለሚበላው ጎመን አይደለም፡፡ እሱን ያስቆጨውና ያስመረረው በሁለቱ ቦታዎች ላይ የፈሰሰው የወጣቶቹ (የልጆቹ) ደም ነው፡፡ ሆኖም ይህንን ድርጊት በግልጽ ለመቃወምና ለመውቀስ ፍርሀት ስለነበረበት ጎመንን ጠርቶ ቁጭቱን ገልጾአል፡፡

ግጥሞቹ በዘመኑ የነበረው ማህበረሰብ በቀይ ሽብር የደረሰበትን ፍራት፣ ጉዳትና ሰቀቀን እንዲሁም ለክስተቱ የነበረውን ምላሽ የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ግጥሞቹ የተነገሩት በጎንደር በነበረው ሁኔታ መነሻነት ነው ቢባልም የዘመቻው ጉዳት በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎችም የነበረ በመሆኑ የምንደርስበት መደምደሚያ የተለየ አይሆንም፡፡

"ሠፈራ" ላይ የተነገሩ ቃል ግጥሞችን እንመልከት፡፡ "የሠፈራ ፕሮግራም" በደርግ ዘመነ መንግስት በተለያዩ ጊዜያት ተካሂዶአል፡፡ በዚህም በሀገሪቱ ልዩ ልዩ ቦታዎች በተፈጠረ "የተፈጥሮ ችግርና ድርቅ" ምክንያት መንግስት የአንዳንድ አካባቢ ነዋሪዎችን ከነበሩበት ቦታ አንስቶ የተሻለ ነው ወደአለው ቦታ እንዲሠፍሩ አድርጎአል፡፡ የሠፈራው ተገቢነት አከራካሪ ቢሆንም ማህበረሰቡ "እትብቴ ተቀብሮበታል!" ከሚለውና ተኩሎና ተድሮ ልጆች ካፈራበት ርስቱ ጋር ያለው ቁርኝት እጅጉን የጠበቀ በመሆኑ፣ ተነስተህ ወደ ሌላ ቦታ ሥፈር ሲባል የደረሰበት የስነልቡና እና

ግጥሞች ወደ ገፅ 19 ዞሯል


# የ2015 እ.ኤ.አ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) የሥራ ፈጠራ (ኢንተርፕሪነር ሺፕ) ሽልማቶች

የተበባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም ለ2015 ኢንተርፕረነርሽፕ ሽልማት እንዲወዳደሩ ተጋበዘዋል፡፡ ሽልማቱ በኢኮኖሚ፤በአካባቢ ልማት፣በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ፣ በህብረተሰብ ዘርፎች ተጽእኖ ፈጣሪና ስኬታማ ኢንተርፕረነሮችን ለማበረታታት የታለመ ነው፡፡ በዚህ ሽልማት መወዳደር የሚችሉት ግለሰብ ኢንተርፕረነሮች ናቸው፡፡

መወዳደር የሚፈሌጉ ሁሉ በ http://goo.gl/iwM7d4
የተቀመጠውን መስፈርት መሰረት የማመልከቻ ቅጹን ሞልተው
በተጠቀሰው ግዜ ውስጥ ብቻ መላክ ይችላሉ ፡፡
በተጨማሪም ለዚህ ውድድር ብቁ ናቸው የሚልዋቸው እጩ
ተወዳዳሪዎች ካሉ ለውድድሩ ብቁ ናቸው ያሉበትን ምክንያት ባጭሩ
በመዘርዘር በፅሁፍ ይላኩልን ፡፡

UNDP
Empowered lives.
Resilient nations.

# SAMSUNG

For your daily life

## Quick and easy printing meets big savings

### Hassle free Business PrintingSolution



Samsung Monochrome Laser Printer ML-5015ND

- ✓High Monthly duty cycle up to 200,000 Sheets
- ✓Unique anti-jam technology that saves printing paper
- ✓Eco printing mode saves up to 30% of toner and paper

And more ...

### The Small printer that packs A mighty punch



Samsung Monochrome Laser Printer ML-2160

- ✓Compact Printer but powerful with 150 sheet paper capacity
- ✓Print what you see on screen quivery And easily with one Touch screen Print Button
- ✓ast Print within compact size up to 20 pages per minute print speed for A4

And more ...

Ctrl P

### Quick and easy printing meets big savings



Samsung Monochrome Laser Multi-function Printer SCX-3405FW

- ✓4 in 1 Fax/Print/Scan/Copy multifunction device Eco mode printing that Saves 20% of toner and paper
- ✓Unique anti-jam technology that saves printing paper
- ✓Wireless printing solution with one button

And more ...

### High Productivity Save Time and Money



Samsung Printer ProXpress SL-M3820ND

- ✓Prints out professional quality including certificates (220 gsm)
- ✓Faster & Powerful
- ✓Eco mode Printing Saves up to 20% toner & Paper

And more ...

**Manufactured By:**

TANA Communication

Tel +251582180406
Fax +251918718501
+251582180408
Bahirdar

With 2 Years in country Warranty!

**Distributed By:**


Glotar Trading & Alta Computec PLC

| Glotar Trading | Alta Computec PLC |
|---|---|
| Tel +251116670165 | Tel +251115519546 |
| +251930033218 | +251115531874 |
| Fax +251116670160 | Fax +251115514753 |
| Addis Ababa | Addis Ababa |

# በሲጋራ ላይ የወጣው ህግ በቅርቡ ይተገበራል

## *ታዳጊዎች ለማጨስ እንዳይበረታቱ ከፍተኛ ቀረጥ ሊጣል ነው*

## *በፓኬት እንጂ በነጠላ መሸጥ ሊከለከል ነው*




መታሰቢያ ካሣዬ

የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን ሰሞኑን በቢሾፍቱ ከተማ ለመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ባዘጋጀው የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራም ላይ በአገሪቱ የሲጋራ አጫሹ ቁጥር እየጨመረ እንደሆነ የተገለፀ ሲሆን በሲጋራ ምርት ላይ ከፍተኛ ቀረጥ እንደሚመጣል ተጠቆመ፡፡

በ2003 ዓ.ም የተደረገውን የሥነ ህዝብና ጤና ጥናት (DHS) ዋቢ በማድረግ በቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች እንደተመለከተው፤ የአጫሾች ቁጥር ወደ ስድስት ሚሊዮን ገደማ ይሆናል፡፡ ከአጫሾቹ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ወንዶች ቢሆኑም የሴት አጫሾች ቁጥርም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ የአገሪቱ አጠቃላይ አመታዊ የሲጋራ ፍላጐትም ወደ 5 ቢሊዮን ፍሬ ደርሷል ተብሏል፡፡

ከአገሪቱ አጠቃላይ የሲጋራ ፍላጐት 53 በመቶ ያህሉ የሚሸፈነው በብሔራዊ ትምባሆ ሞኖፖል ሲሆን 4.6 በመቶ ከውጪ በማስገባት፣ 38 በመቶ ደግሞ በኮንትሮባንድ (ህገወጥ) ንግድ ነው፡፡ ትምባሆ፤ ሱስ አስያዥ የሆነውን ኒኮቲን የተባለ ንጥረ ነገር ጨምሮ ከአራት ሺህ በላይ ኬሚካሎችን በውስጡ ይይዛል፡፡ ከእነዚህ ውስጥም 250 ያህሉ እጅግ አደገኛ ኬሚካሎች ሲሆኑ 50 የሚደርሱት ደግሞ ካንሰር አምጪ ኬሚካሎች መሆናቸውን የአለም ጤና ድርጅት ተወካዩ አቶ ዋሲሁን መላኩ ተናግረዋል፡፡



አዕምሮአችን የተስተካከለ ጤና እንዳይኖረው ከሚያደርጉ ጉዳዮች አንዱ ሱሰኝነት ነው ያሉት ዶክተር ሙሴ ገብረሚካኤል፤ በትምባሆ ውስጥ የሚገኘውና ኒኮቲን የተባለው ንጥረ ነገር አንጐላችን ውስጥ የተለያዩ ለውጦችን በመፍጠር አንጐላችንን የኒኮቲን ጥገኛ ያደርገዋል ብለዋል፡፡ ትንባሆ ውስጥ የሚገኘው ሱስ አስያዥ ኒኮቲን መጠኑ እየጨመረ በመጣ ቁጥር ለአዕምሮ ህመም እንዲሁም ለሞት የመጋለጥ እድል እንደሚጨምር ገልፀዋል፡፡

መከላከል እየተቻለ ለሞት መንስኤ ከሚሆኑ የአለማችን የጤና ጠንቆች ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው ትምባሆ፤ ለከፍተኛ የደም ግፊት፣ ለልብ ህመም፣ ለተለያዩ ካንሰር ህመሞች፣ ለአይን ሞራ ግርዶሽ፣ ለጥርስ መበስበስ፣ ለጨጓራ ቁስለት፣ ለአንጐል በሽታ፣ ለጋንግሪንና ለስንፈተ ወሲብ እንደሚያጋልጥም የአለም ጤና ድርጅት መረጃ ያመለክታል፡፡

በ2013 የተደረገና በአለም ጤና ድርጅት ይፋ የሆነ የጥናት ውጤት እንደሚጠቁመውም፤ በአለማችን በትምባሆ ሣቢያ በሚከሰቱ የጤና ችግሮች ህይወታቸውን የሚያጡ ሰዎች ቁጥር በኤድስ፣ በትራፊክ አደጋ፣ በአደንዛዥ እፅ፣ በግድያ ወንጀልና ራስን በማጥፋት ከሚሞቱት ሰዎች አጠቃላይ ድምር ይበልጣል፡፡ በአሁኑ ወቅት በዓለማችን 1.3 ቢሊዮን የትምባሆ ተጠቃሚዎች የሚገኙ ሲሆን በየዓመቱም 5 ሚሊዮን የሚሆኑት በትምባሆ ምክንያት ህይወታቸውን ያጣሉ፡፡ የሟቾቹ ቁጥር ካደጉት አገራት ይልቅ ገና በማደግ ላይ ባሉት አገራት ይጨምራል፡፡

በአገራችን ትምባሆ በተለያዩ መንገዶች በጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን ማጨስ፣ ማኘክ፣ መታጠንና ማሽተት ዋንኞቹ የትምባሆ ተጠቃሚዎች የሚያዘወትሯቸው መንገዶች ናቸው፡፡ በተለይ ከከተማ ወጣ ባሉ አካባቢዎች በማኘክና በማሽተት የትምባሆ ተጠቃሚ መሆን የተለመደ ነው፡፡

በከተሞች አካባቢ በፋብሪካ የሚዘጋጁ የትምባሆ ምርቶች የሚዘወተሩ ሲሆን በብሔራዊ ትምባሆ ሞኖፖል የሚመረቱት ግስላ፣ ኒያላ፣ ኢሌኒና ዲላይት የተባሉት የሲጋራ አይነቶች ገበያውን በከፍተኛ ደረጃ ተቆጣጥረውታል፡፡

ማልቦሮ፣ ዊንስተን፣ ሮዝማን፣ ኤል ኤንድ ኤም እና ኬንት የተባሉት የሲጋራ አይነቶች ደግሞ በህጋዊ መንገድና በኮንትሮባንድ ከውጪ አገር እየገቡ ለአገራችን ገበያ የሚቀርቡ የሲጋራ አይነቶች ናቸው፡፡

የትምባሆ ኢንዱስትሪ ከፍተኛ የሥራ ዕድል በመፍጠርና የታክስ ገቢ በማስገኘት ለአገሪቱ የሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ ከፍተኛ ቢሆንም የሚያስከትለው ችግርና የሚፈጥረው ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ከፍተኛ በመሆኑ፣ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ፣ በትምባሆ ሣቢያ የሚሞቱ ዜጐችን መታደግ አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሆኖ በመገኘቱ፣ ህግ አውጥቶ፣ አሠራሩን መቆጣጠር እንዳስፈለገ በኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን አማካሪ አቶ መንግስተአብ ወልደአረጋይ ተናግረዋል፡፡ በተለይም ማጨስ በሚጀመርበት የወጣትነት ዕድሜ ውስጥ የሚገኙ ዜጐች ሲጋራ በቀላሉ ለማግኘት እንዳይችሉ በትምባሆ ላይ የሚጣለውን ታክስ ከፍ በማድረግ፣ የሲጋራ መሸጫ ዋጋን ለመጨመር የሚያስችል ስትራቴጂ ተነድፎና ረቂቅ ህግ ወጥቶ በገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስትር ጥናት እየተደረገበት እንደሆነ አማካሪው ጠቁመዋል፡፡ ህጉ በቅርቡ ፀድቆ ተግባራዊ ይደረጋል ተብሎ እንደሚጠበቅም ገልፀዋል፡፡

ባለፈው ዓመት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፀደቀውን የትምባሆ ቁጥጥር አዋጅ ለማስፈፀም ሥልጣንና ኃላፊነት የተሰጠው የኢትዮጵያ የምግብ፣ መድኀኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን፤ ህዳር 22 ቀን 2007 ዓ.ም የትምባሆ ቁጥጥር መመሪያ በማውጣት አፅድቋል፡፡ በቅርቡም ተግባራዊ እንቅስቃሴ የሚጀመር ሲሆን በትምባሆ ምርቶች ሽያጭ፣ ዝውውርና አጠቃቀም ላይ ቁጥጥርና ክትትል እንደሚደረግ ተገልጿል፡፡

በአዲሱ አዋጅና መመሪያ መሰረትም፣ ማንኛውም የኤሌክትሮኒክስ ኒኮቲን መስጫ መሳሪያ ማምረት ወደ ሀገር ውስጥ ማምጣት፣ ማከፋፈል፣ መሸጥ ወይም በማንኛውም መንገድ ገበያ ውስጥ ማስገባት የተከለከለ ነው፡፡

የትምባሆ ምርቱ ለጤና አደገኛ መሆኑን የሚገልፅ የማስጠንቀቂያ ፅሁፍ የሲጋራ ባኮውን 30 በመቶው ያላነሰ ቦታ በሚሸፍን መልኩ መገለፅ ይኖርበታል፡፡ የትምባሆ ምርትን በችርቻሮ የመሸጥ ፍቃድ የተሰጣቸው ሰዎች ምርቱን ለአይን በሚታይ መልኩ መደርደርና ገዥን መሳብ አይችሉም፡፡ የትምባሆ ምርት የሚሸጠው ባልተከፈተ ፓኬት ወይም ማሸጊያ ሲሆን ሲጋራን በነጠላ መሸጥ የተከለከለ መሆኑን አዲሱ አዋጅና መመሪያ ያዛል፡፡

ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ታዳጊዎች በትምባሆ ምርት ግዥም ሆነ ሽያጭ ላይ ተሳታፊ መሆን እንደማይችሉ የደነገገው አዲሱ መመሪያ፤ የትምባሆ ምርት በችርቻሮ በሚሸጥበት ወቅት ሻጩ የገዥውን ዕድሜ ከተጠራጠረ ህጋዊ ፓስፖርት፣ የመንጃ ፈቃድ ወይም የነዋሪነት መታወቂያ ካርድ አይቶ ማረጋገጥ አለበት ይላል፡፡ አዲሱ መመሪያ ሲጋራ ማጨስ የማይፈቅድባቸውን ቦታዎች በዝርዝር የገለጸ ሲሆን፤ ሆቴሎች፣ የመጠጥ ቤቶች፣ የምሽት ክለቦች፣ መዝናኛ ክበቦች፣ ካፌዎች፣ ምግብ ቤቶች፣ የመንግስትና የግል መስሪያ ቤቶች፣ ሊፍቶች፣ መታጠቢያ ቤቶች፣ ፋብሪካዎችና የንግድ መደብሮች፣ ሲኒማ፣ ቲያትርና ቪዲዮ ቤቶች፣ ሙዚቃ ማጫያ አዳራሾች፣ የህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች፣ የህዝብ ትራንስፖርቶች፣ እንዲሁም ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች በሚገኙባቸው ሥፍራዎች ሁሉ ማጨስ የተከለከለ ነው፡፡

አዲሱ ህግና መመሪያ በቅርቡ ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን ደንብና መመሪያውን በማይተገብሩ አካላት ላይም ህጋዊ እርምጃ እንደሚወሰድ ተገልጿል፡፡ ከሶስት ወራት በኋላ በሚወጡ ፊልሞች ላይ ሲጋራ እንዳይጨስና የሚጨስባቸው አጋጣሚዎች ካሉም በፊልሙ ላይ የሲጋራን ጎጂነት የሚገልፁ ፅሁፎች በስክሪኑ ላይ እንዲጻፉ የሚያስገድድ አሰራርም እንደሚጀመር ተገልጿል፡፡

# ጭውውት 12፤ማርጀት፣ መሞት፣ ወዘተ

**ሂሳብ**፣ የዛሬው የመጨረሻው ጭውውታችን ነው፣ ማርጀትና መሞትን የሚመለከት፡፡ ጥናቱን የሚያቀርብልን ጓድ አስተዳደር ነው፡፡ መድረኩ ይኸውልህ!

**ኬሚስትሪ**፣ ጓድ ሰብሳቢ፣ ይህ አርእስት ስጋት ላይ ጥሎኛል፣ ማለቴ ጡረተኛ ስለሞት ማውራት አለበት እንዴ? እንደኔ ከዚህ አርእስት መራቅ ይሻላል!

**ምህንድስና**፣ አቤት ፍርሃት! አይዞህ ጭውውቱን እስከንጨርስ አትሞትም፣ ለማናቸውም ብትሞትም አንዴ ነው፣ ደግመህ ትሞትም፡፡ ስለዚህ ፍርሃትህን ወደ ጎን አድርገው፡፡

**አስተዳደር**፣ ጓዶች፣ አርእስቱን እንተወው ለማለት ትንሽ የዘገየ ይመስለኛል፡፡ እኔም እኮ የማይናቅ ጊዜ መሰናዶው ላይ አጥፍቻለሁ፡፡

**ሂሳብ**፣ መልካም፣ በል ጥናትህን አቅርብልን፡፡

**አስተዳደር**፣ በመጀመሪያ ሦስታችሁንም ለማመስገን እፈልጋለሁ፣ የሚነበቡ ፅሁፎች ባትሰጡኝ ኖሮ በፍፁም ልወጣው ባልቻልኩ ነበር፡፡

በእርግጠኝነት መናገር እችላለሁ፣ ስለ ፕሮቶን፣ ኤሌክትሮን ባላወራሁም ነበር፡፡ እስቲ ከመሰረቱ ልጀምር፡፡ ሳይንስ ሲያስተምረን ሁሉ ነገር፣ ማለትም ከድንጋይ እስከ ሰው ያለው ሁሉ የተገነባው ከአቶሞች እንደሆነ ነው፡፡

አቶሞች በተራቸው ከፕሮቶኖችና ኤሌክትሮኖች የተነቡ ሲሆን፣ ፕሮቶኖች ከኳርክ ዝርያዎች ተቀነባብረው የተሰሩ ናቸው፣ ኤሌክትሮን ግን እራሷን የቻለች ናት፡፡ ጓዶች፣ ከወር በፊት "ኳርክ" ምንድነው ብትሉኝ ኖሮ፣ እንቁራሪት የሚያሰማው ድምፅ ነዋ! እል ነበር፡፡ እንደምታዩት እኔም መጠነኛ ትምህርት ቀስሜያለሁ!

የሚነሳው ጥያቄ የአቶሞች ዕድሜ ስንት ነው? ያረጃሉ ወይ? የሚል ነው፡፡ የፊዚክስ ባለሙያዎች ሲያስረዱ፣ የፕሮቶን እድሜ $10^{31}$ ዓመታት (ማለትም 10 ሚሊዮን፣ ሚሊዮን፣ ሚሊዮን፣ ሚሊዮን፣ ሚሊዮን) ሲሆን ኤሌክትሮን ግን ጨርሶ የማትለወጥ ናት፡፡

ታዲያ ይኸ እንዲህ ከሆነ በአቶሞች የተገነቡት ህዋሳ፣ ብሎም ተክሎችና እንስሳት እንዴትና ለምን ማርጀት ቻሉ? አንዳንዶች ሲያስረዱ፣ ህዋስ ከአቶም የበለጠ ውስብስብ፣ እንቁራሪት (የህዋሳት ስብስብ) ከአንድ ህዋስ የበለጠ ውስብስብ ናቸው፡፡ እነኚህ ምሁራን እንደሚሉት ውስብስብነት (ኮምፕሌክሲቲ) ወደ ህይወት ያመራል፣ አይቀሬ ነው፡፡ ህይወት ወደ ሞት! ይህ አባባል ወደ ፍልስፍናው የሚያደላ ስለሚመስል ባንገፋበት ይሻላል፡፡

ባለአንድ ህዋስ ባክቴሪያም እኮ ታረጃለች፣ ማለትም ውስብስብነት በይፋ የማይታይበት፣ ለምን? እርጅናን የሚቆጣጠሩ ጂኖች አሉ? አንዳንድ ሰዎች እስከ 130 ዓመት እንደሚኖሩ የታወቀ ነው፣ ባካባቢያቸው ምክንያት ይሆን? ብዙ ጊዜ እነኚህ ሰዎች ዳገትማ ስፍራ፣ ንፁህ አየርና ውሃ በሚገኝበት የሚኖሩ ናቸው፡፡ ለምግባቸውም ከስጋ ይልቅስ ተክሎችን ያዘወትራሉ ይባላል፡፡ ተክሎችን ስንመለከት፣ በአሁኑ ወቅት በሰሜን አሜሪካ፣ ካሊፎርኒያ ግዛት ውስጥ "ሴኮያ" የተባለ ዛፍ እስከ 3,800 ዓመት እንዲኖር በተደረገ ምርምር በ C-14 እና ከግንዱ ቀለበቶች ቁጥር ተረጋግጧል፡፡

የዚህ ዓይነት ዛፍ፣ ትልቅና ረጅም ዕድሜ ያለው የግንዱ ግማሽ - ወገብ ስፋት (ሬዲየስ) 4,85 ሜትር፣ ዙሪያ ርቀት (ሰርከምፈረንስ) 30 ሜትር፣ የቅርፊት ውፍረት 61 ሴንቲሜትር መሆኑ ታውቋል፡፡ እርግጥ፣ ሴኮያ በንግዱ መወፈርና በቅርፊቱ ደንዳና መሆን ምስጥ፣ ዝናብ፣ በረዶ ሊያጠቁት የቻሉ አይመስልም፡፡ ሌላው የዛፉ ከፍታ ቦታ በማደግ ከእንስሳት መራቁ ነው፡፡ ከሴኮያ ህዋሳት የምንማረው ይኖራል?

["ከዚህም ከዚያም" (የ4 ጡረተኞች ጭውውት) ከተሰኘው የፕሮፌሰር ግርማ ሙልኢሳ መፅሃፍ የተቀነጨበ]

# ጠ/ሚኒስትሩ ከአዳዲስ መረጃዎች ጋር አስተዋወቁን!

## አውሮፓ ህብረት ምርጫውን የማይታዘበው በገንዘብ ችግር ነው
## ተቃዋሚዎች ባይነግሩንም ከጠ/ሚኒስትሩ ጋር ተወያይተው ነበር
## እነ "ኤፈርት" ከአውራው ፓርቲ ጋር የሚያገናኛቸው ነገር የለም ተባለ

ባለፈው ማክሰኞ በቀድሞው ኢቴቪ (በአዲሱ EBC) በምርጫ ዙሪያ የቀረበው ዘገባ አስደምሞኛል (ሌላ ምርጫ የለኝማ!) ለነገሩ ዘገባ ከማለት ይልቅ ያፈጠጠ የምርጫ ቅስቀሳ ቢባል ይቀላል (መተቸቴ እኮ አይደለም?!) ቢያንስ ግን በEBC ጋዜጠኛ ባይሰራ ይመረጥ ነበር (ልማታዊ ጋዜጠኛ መሆኑ አልጠፋኝም!)

እኔ የምለው ግን... EBC በቢቢሲ ሞዴል ይዋቀራል የተባለው ቀረ እንዴ? (ኧረ እንኳንም ቀረ!)፡፡ ለምን አትሉም? ለልማታዊ መንግስት አይመችማ! (ኒዮሊበራሎች እጅ ጠምዛዦች "arm twister" ናቸው!)

እናላችሁ... የEBC ጋዜጠኛ ስላለፉት ነፃ፣ ዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ምርጫዎች በቃሉ የፃፈውን ስክሪፕት ትንሽ ካነበነበ በኋላ "በግንቦቱ ምርጫ ዙሪያ ያሰባሰብኩትን የነዋሪዎች አስተያየት ተከታተሉኝ" አለ፡፡ (አስተያየት ሰጪዎቹ "አንዳንድ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች"ን አስታወሱኝ!) አይገርማችሁም... እነዚህ "ነዋሪዎች" ሁሌም ምርጫ ሲደርስ ከተፍ ይላሉ፡፡ እናም "ይሆነኛል... ይበጀኛል... የምለውን ..."፣ "ልማቱን ያስቀጥልልኛል ያልኩትን ..."፣ "ልማታዊ መንግስት የምለውን --" ወዘተ-- እንመርጣለን እያሉ አስተያየት ሰጡ፡፡ አንዳንዶቹም "ህዝቡ በምርጫው እንዲሳተፍ በመቀስቀስ የዜግነት ግዴታዬን እወጣለሁ" አሉ፡፡ (ግዴታና ውዴታ ተምታታብን እኮ!) እኔ የምላችሁ ... EBC የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ግንባታ ላይ እንደሆንን አልሰማም እንዴ? (የነፃ ገበያ አቀንቃኞች ሃሳብ አልተስተናገደም ብዬ እኮ ነው!)

በነገራችን ላይ--ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ፤ "የመድብለ ፓርቲ ሥርዓት ከሌለ፣ ዕጣ ፈንታችን የሶማሊያ ዓይነት ነው" ሲሉ አስጠንቅቀዋል፡፡ (የEBC ጋዜጠኞችን ይመለከታል!) ለማንኛውም ግን የምርጫ ቅስቀሳው ተጀምሯል፡፡ የጀመረው ግን ኢህአዴግ አይደለም፤ EBC ነው፡፡ ("ያለ ዕዳው ዘማች" አሉ!)

ሰሞኑን ጠ/ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ ለአገር ውስጥና ለውጭ ጋዜጠኞች በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ምን እንደታዘብኩ ልንገራችሁ? ከስልጣናቸው ጋር በደንብ መለማመዳቸውን፡፡ (ፈጣን ተማሪ ናቸው ማለት ነው!) ቢሆኑማ ነው--- ሰሞኑን "የዓለማችን ምሁር መሪዎች" በሚል ከእነ አባማ ተርታ መሰለፍ የቻሉት፡፡ (ለአገር ገፅ ግንባታ ማለፊያ ግብዓት አገኘን!)

እናላችሁ ... የማይለመድ የለም-- ሥልጣኑን በደንብ ተለማምደውታል፡፡ ለዚህ እኮ ነው በሰሞኑ መግለጫ ከሌላው ጊዜ በተለየ ተረጋግተው... በልበሙሉነት... ቁጣና ፍረጃ ሳያበዙ... ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ ያየነው፡፡ (አሁን ተረብ ብቻ ነው የቀራቸው!) በተለይ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን በተመለከተ የተናገሩት ያልተጠበቀ ነው (ተቃዋሚዎች ራሳቸው መገረማቸው አይቀርም!) ጋዜጣዊ መግለጫቸውን የቋጩት፤ "ለጋራ አገራችን በጋራ እንወያይ የሚል ጥሪ ማቅረብ እፈልጋለሁ" በሚል መልዕክት ነው፡፡ ("ባንዳፍ" ብለናቸዋል!)

ብዙዎች ግን አንድ ጥያቄ አላቸው፡፡ "ይሄ አቋም የግላቸው ነው የፓርቲያቸው? ወይስ የመንግስታቸው?" የሚል፡፡ ለእኔ ግን ለውጥ የለውም፡፡ ዋናው ከአንጀታቸው መሆኑ ነው፡፡ ከባለፈው ምርጫ የዞረው የፈረደበት "የሥነምግባር ደንብ" ግን አሁንም አልቀረም፡፡ (ፊርማ ከሌለ፤ ውይይት የለም!) እኔ ተቃዋሚዎችን ብሆን ግን --- የአበሽነት እልሄን ዋጥ አድርጌ፣ የተባለውን ግጥም አድርጌ እፈርም ነበር ("ኩራት እራት አይሆንም" አለ አበሻ!)በሰሞኑ ጋዜጣዊ መግለጫ፣ ጠ/ሚኒስትሩ ከአዳዲስ መረጃዎች ጋር አስተዋውቀውናል፡፡ ከአንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ጋር በግል የመወያየት ዕድል እንደገጠማቸው አስታውሰው፤ አመራሮቹ የሥነምግባር ኮዱን ፈርመው የፓርቲዎች የጋራ ም/ቤትን እንዲቀላቀሉ አሳምነው ከላኳቸው በኋላ ሌሎቹ አልተስማሙም ብለው እንደቀሩ ተናግረዋል፡፡ (ተቃዋሚዎች ውይይቱን ምስጢር ማድረጋቸው ግን ያስተዛዝባል!) ስንቱን ነገር ሲነግሩን ከርመው ... እንዴት ይሄን ይደብቁናል?! ለነገሩ አይፈረድባቸውም፡፡ (ከ"ኢህአዴግ ጋር ተሞዳሞዱ" የሚል ውግዘት ፈርተው ይሆናል!)

ጠ/ሚኒስትሩ ሌላም የነገሩን መረጃ አለ፡፡ አንዳንድ ተቃዋሚዎች ለውይይት ሲጋበዙ "እነ እገሌ ካሉ (እነ እገሌ እኮ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ናቸው!) አንሳተፍም" እንደሚሉ ጠቁመው፤ ከዚህ አቋማቸው ወጥተው በጋራ ለመወያየት መዘጋጀት እንዳለባቸው መክረዋቸዋል (ተቃዋሚዎች የባህርይ ለውጥ ያስፈልጋቸዋል!) እኔ የምለው ... ኢህአዴግ ለየብቻችን ካላነጋገረን የሚሉት በልማት መወጠሩን ዘንግተውት ነው ወይስ ልማቱን ለማደናቀፍ? (መቼም ልማቱን ትቶ ሲወያይ አይከርምም!)

እንዲያም ሆኖ... የደቡብ ሱዳን ፓርቲዎችን ለማደራደር እሳቸውና ፓርቲያቸው ካሳዩት ጥረትና ትዕግስት አንጻር ለአገራቸው ፓርቲዎች ገና ብዙ ጥረትና ትዕግስት ይቀራቸዋል፡፡ ጠ/ሚኒስትሩ፤ አሁንም በደቡብ ሱዳን ጉዳይ ተስፋ እንደማይቆርጡም ተናግረዋል፡፡ እርግጠኛ ነኝ ---- በአገራቸው ተቃዋሚዎችም ተስፋ አይቆርጡም፡፡

ከጠ/ሚኒስትሩ የሰማነው ሌላ አዲስ መረጃ ምን መሰላችሁ? ... የኢህአዴግ ናቸው ሲባሉ የነበሩት የንግድ ድርጅቶች - ኢንዶውመንትስ- (እነ ኤፈርትን ለማለት ነው!) ከኢህአዴግ ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌላቸው ነግረውናል፡፡ ይሄ ትንሽ ግራ ያጋባል፡፡ የኢህአዴግ ካልሆኑ የማን ናቸው? (የተቃዋሚዎች እንዳይሆኑና እንዳይገርመኝ!) ከመጪው የግንቦት አገራዊ ምርጫ ጋር የተያያዙ አንዳንድ ውዥንብሮችንም ጠ/ሚኒስትሩ አጥርተዋል፡፡ የአውሮፓ ህብረት በምርጫው በታዛቢነት የማይሳተፈው መንግስት ሳይጋብዘው ቀርቶ ሳይሆን በራሱ የገንዘብ ችግር እንደሆነ ነግረውናል፡፡ አንዳንድ ወገኖች ግን ለአውሮፓ ህብረት ግብዣው የቀረበለት ባለቀ ሰዓት ነው ይላሉ፡፡ ("እንዳያማህ ጥራው---" ሆኗል ለማለት እኮ ነው!) የሆኖ ሆኖ ግን ጠ/ሚኒስትሩ እንዳሉት፤ "ምርጫው በእጃችን ነው፡፡" ሰናይ ሰንበት!


# የስብሰባ ጥሪ

## ለአያት አክስዮን ማኅበር ባለአክስዮኖች በሙሉ

አያት አክስዮን ማኅበር በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 9 ንጽስ አንቀጽ 9.1 መሠረት 8ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ስለሚያካሂድ የማኅበሩ ባለ አክስዮኖች የሆናችሁ ሁሉ በጉባኤው ላይ እንድትገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

የስብሰባ ቀን -------------------- ታህሳስ 26 ቀን 2007 ዓ.ም

የስብሰባ ቦታ -------------------- በራስ ሆቴል አዳራሽ

የስብሰባ ሰዓት ------------------- ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት

የስብሰባው አጀንዳዎች፣

1. የዳይሬክተሮች ቦርድን ሪፖርት ማድመጥ
2. የውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት ማድመጥ
3. በዳይሬክተሮች ቦርድና በውጭ ኦዲተሮች ሪፖርት ላይ ተወያይቶ መወሰን
4. የትርፍ ክፍፍልን አስመልክቶ ከዳይሬክተሮች ቦርድ በቀረበው ሀሳብ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
5. የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን አበልና የትርፍ ድርሻ መወሰን፣

ማሳሰቢያ፡- ባለአክሲዮኖች በጉባኤው ዕለት አክስዮን የገዛችሁበትን ማስረጃ ይዛችሁ መቅረብ ይጠበቅባችኋል፡፡ በስብሰባው ላይ ራሳችሁ መገኘት የማትችሉ ባለአክሲዮኖች ለገሃር በሚገኘው የአያት አክሲዮን ሽያጭ ቢሮ በመቅረብ የእንደራሴ ውክልና ፎርም እስከ ታህሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ መሙላት ይኖርባችኋል፡፡

እንደራሴዎች የውክልና ደብዳቤ፣ መታወቂያና እንዲሁም አክስዮን የተገዛበት ማስረጃ በስብሰባው ዕለት ይዘው መቅረብ ይኖርባችኋል፡፡ በጣምራ አክሲዮን የገዛችሁ ባለ አክሲዮኖች በጋራ ጉባኤው አንድ ሰው መወከል ይጠበቅባችኋል፡፡ ወኪሎችም የውክልና ደብዳቤና መታወቂያ እንዲሁም አክስዮን የተገዛበትን ማስረጃ ይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

አያት አክስዮን ማኅበር

የዳይሬክተሮች ቦርድ


# ያለፈው ሥርዓት "አስማተኛ" ሳይሆን አይቀርም!

እኔ የምላችሁ ግን ... ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ ስንት ዓመቱ ነው? ይሄንን ቀላል ጥያቄ የምጠይቃችሁ ወድጄ እንዳይመስላችሁ፡፡ ግራ ቢገባኝ ነው፡፡ ሌላም ጥያቄ አለኝ - ያለፈው ሥርዓት ከተገረሰሰ ምን ያህል ጊዜ ሆነው? (ውዥንብሩ መጥራት አለበት!) አንዳንዴ ያለፈው ሥርዓት "አስማተኛ" ይመስለኛል፡፡ ለምን መሰላችሁ? አንዳንድ ሰዎች አሁንም ከ24 ዓመት በኋላ እንኳን ስለሱ ማውራት አልተዉም፡፡ ለሁሉ ነገር ያለፈውን ሥርዓት ካልጠሩ አይሆንላቸውም - በተለይ የኢህአዴግ ካድሬዎች፡፡ (ፍሬሾቹን ማለቴ ነው!)

ሰሞኑን EBC ባቀረበው የዜና ዘገባ ላይ "...የሴቶች ጥቃት ያለፈው ሥርዓት ችግር ስለሆነ እንታገለዋለን..." (really?!) የሚል ነገር የሰማሁ መሰለኝ፡፡ እውነቱን ልንገራችሁ አይደል ... ራሱ ኢህአዴግም እንኳን የሴቶች ጥቃት "ያለፈው ሥርዓት" ችግር ነው አይልም፡፡ እንዲያ ካለማ--- ያለፈው ሥርዓት አልተገረሰሰም ማለት ነው፡፡ ወይም ደግሞ እንዳልኩት "አስተማኛ" ነው፡፡ (መቃብር እየፈነቀለ የሚወጣ!)

ይሄውላችሁ --- በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በዓይነትም በመጠንም እየጨመሩ ለመምጣታቸው ከፖሊስ ፕሮግራም የበለጠ ማስረጃ የለም፡፡ (የሴቶች መብት ተሟጋቾችም ምስክር ናቸው!) አስገድዶ መድፈር፣ አሲድ መድፋት፣ ከባድ ድብደባና የአካል ማጉደል እንዲሁም አሰቃቂ ግድያዎች...በእጅጉ በርክተዋል፡፡ (ሰብዓዊ ልማት ተዘንግቷል!)

እናም--- የሰሞኑ የEBC ዘገባ blame shifting ("የእምዬን ወደ አብዬ") እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም፡፡ ሃቁን እንነጋገር ከተባለ --- የሴቶች ጥቃት "ያለፈው ሥርዓት" ችግር ሳይሆን የእኛው የራሳችን ችግር ነው፡፡ (የኋላ ቀርነት፣ የትምህርት አለመስፋፋት፣ የግንዛቤ ማነስ፣ የአመለካከት ችግር ወዘተ...) ነገርዬው እምብዛም ከስርዓት ጋር የሚያያዝ አልመሰለኝም (ፖለቲካ እኮ አይደለም!) የግድ የሥርዓት ችግር ነው ከተባለም ባለቤቱ የአሁኑ ሥርዓት ነው፡፡ እናሳ? ... እናማ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ወዳለፈው ሥርዓት ለማሻገር ከመታተር ይልቅ እውነታውን ተቀብሎ ለመፍትሄ መትጋት ይሻላል፡፡ (ያለፈው ሥርዓት ከበቂ በላይ የራሱ ኃጢያቶች እንዳሉት አንዘንጋ!!)

ይሄውላችሁ ----- እንኳንስ በቅርብ ዓመታት እየተባባሰ የመጣው "የሴቶች ጥቃት" ይቅርና በእርግጥም ካለፈው ሥርዓት የተወረሱ ናቸው የሚባሉት (እነ ድህነት፣ ሙስና፣ የስልጣን ጥመኝነት፣ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት፣ የነፃነት አፈና፣ የፍትህ መጓደል ወዘተ...) ቢሆኑም እንኳ --- 20 ዓመት ስላለፋቸው ውርስነታቸው አብቅቷል፡፡ (ከአባት የተወረሰ ንብረትም እኮ ለዘላለም በውርስነት አይጠራም!) ከምሬ እኮ ነው... ከአሁን በኋላ ችግሮችን ባለፈው ሥርዓት ማሳበብ ራስን ለትዝብት ማጋለጥ ነው፡፡

በመጨረሻ አንድ ሃሳብ ላቅርብ፡ ከዖታዊ ጥቃቶች አንዱ የሆነው አስገድዶ መድፈር፣ ለምን በፀረ ሽብር ህጉ ውስጥ አይካተትም? ይሄ እኮ... ሥርዓቱን ወይም ህገመንግስቱን በኃይል ለመናድ ከመሞከር ፈፅሞ አይተናነስም፡፡ ሴቶች ላይ ጥቃት መፈጸም - ቤተሰብን --- ህዝብን --- መንግስትን ---- አገርን --- ማሸበር ነው!!

Flintstone Homes
for you®

Leading by example

Trust Flintstone...



...Be happy

Click: www.flintstonehomes.com
E-mail: flintstonehomes@gmail.com


ይቆጥቡ! ይሸለሙ!
በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንድ ሺህ ብር እና ከዚያ በላይ በመቆጠብ ለሽልማት ዕጣ ብቁ
የሚያደርግዎትን ኩፖን ይውሰዱ
ቆጥበን ተሸልመናል እናንተስ?
MOBILE
ከታህሳስ 23 እስከ ሰኔ 23, ቀን 2007 ዓ.ም
(January 1 – June 30,2015)
4ኛ ዙር
ይሸለሙ!
ይቆጥቡ!
ይቆጥቡ!
Design & Print Yekatit Paper Converting Plc
የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ
Commercial Bank of Ethiopia
Gambia Street, P.O.Box 255,Addis Ababa, Ethiopia
ስልክ: +251-115-51-50-04,+251-115-51-24-52/551-21-66
Telegram: ethiobank SWIFT Code: CBETETAA ፋክስ: +251-115-51-21-66
ኢሜይል: cbecomu@combanketh.et
ድረገጽ: www.combanketh.et

# አማርኛ የራሱ ፊደል አለውን?

ጌታቸው አበበ አየለ

## ክፍል ፪

በክፍል ፩ ፅሑፌ፤ የአማርኛ ፊደሎች (ሆሄያት) በዝተዋልና ይቀነሱ (ይሻሻሉ) በሚሉ የቋንቋ ምሁራን የተሰነዘሩትንና እየተሰነዘሩም ያሉትን ሀሳቦች ከብዙው በጣም በጥቂቱ እንደገለጽኩ ይታወሳል፡፡

በማጠናቀቂያዬም "ለመኾኑ አማርኛ የራሱ የኾነ ብቸኛ ፊደል (የፊደል ገበታ) አለውን?" የሚል ጥያቄ አቅርቤ ነበር፡፡ እናም በቀጠሮዬ መሰረት ይኸው የያዝኩትን ይዤ ብቅ ብያለሁ፡፡ መልካም ንባብ፡፡

"ነገርን ነገር ያነሳዋል" ይባል የለ፡፡ እናም ወደ ዋናው ጉዳይ ከመሔዴ በፊት "ፊደል" የሚለውን ቃል በተመለከተ አንድ ሐሳብ ላነሣ ፈለግሁ፡፡ ያለምክንያት አይደለም፡፡ ፊደል የሚለው ቃል ሆሄ ከሚለው ቃል ጋር በተምታታ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሲውሉ በማየቴ ነው፡፡

በእርግጥ እንደ ልምድ ሆኖ ይመስላል ሆሄ በማለት ፈንታ ፊደል እያልን ስንጠቀም ቆይተናል፤ እየተጠቀምንም እንገኛለን፡፡ ያም ሆኖ ግን መግባባታችን አልቀረም፡፡ "ቋንቋ መግባቢያ አይደል እንዴ! እኛ ከተግባባንበት ቢባል ምን ችግር አለው?" የምትሉኝ ትኖሩ ይሆናል፡፡ ተሳስታችኋል ከሚል ድምዳሜ ፈጥኜ አልገባም፡፡

ይሁን እንጂ በሥነ ጽሑፍ ውስጥ አንድ ቃል ሊገልጸው የሚፈልገውን ነገር በትክክል ሊያስረዳ ካልቻለ ጳያፍ ከመሆን አያልፍም፡፡ "እንጀራ እየጋገርሁ ነው" ለማለት "ምጣድ እየጋገርሁ ነው፡፡" አይነት ይሆናል፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ስለ ፊደልና ሆሄ ልዩነትና አጠቃቀም ብንሳሳት ወይም ባናውቅ አይፈረድብንም፡፡ ምክንያቱም ስለ ሁለቱ ቃላት ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያብራራ መዝገበ ቃላት አልተዘጋጀምና፡፡ አንዳንዶቹ መዛግብተ ቃላትማ ፊደልን ጠቅሰው ሆሄ የሚለውን ዘልለውት እናገኛቸዋለን፡፡

ወደ እንግሊዝኛው መዝገበ ቃላት መለስ ብለን እስቲ "አልፋቤት" እና "ሌተር" የሚሉትን ቃላት ትርጉም እንመልከት፡፡

Alphabet: The set of letters used in writing any language, esp. when arranged in order, eg. Greek alphabet, Russian alphabet. Letter: any of the sign in writing or printing that represent a speech sound. "B is a capital letter "b" is a small letter. (Longman Dictionary of Cont. English)

እዚህ ላይ እንደምንመለከተው በእንግሊዝኛው መዝገበ ቃላት alphabet (ፊደል) እና letter (ሆሄ) ግልጽ ትርጉም ይዘው እናገኛቸዋለን፡፡ ወደ አገራችን ስንመጣ፣ ካሉት መዛግብተ ቃላት መካከል ቀረብ ያለ አተረጓጎም የያዘው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታተመው የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር አማርኛ መዝገበ ቃላት ፊደል የሚለውን ቃል፡-

"ፊደል፡- ንግግርን በጽሑፍ ለማስፈር የሚያስችልና ድምጽን ወክሎ የሚቆም ምልክት (ለምሳሌ ሀ፣ ለ ...) በማለት ተርጎሞታል፡፡ ሆሄ ለሚለው ቃል ደግሞ "ሆሄ (ብዙ ሆህያት) ስ. ከግእዝ እስከ ሳብዕ (ለምሳሌ ከሀ-ሆ ወይም ከሀ-ፐ) ያለው የፊደላት ስምና መልክ ወይም ቅርፅ" የሚል ትርጉም ሰጥቶታል፡፡

ለማንኛውም ፊደል ንግግርን በጽሑፍ ለማስፈር የሚያስችሉና ድምፅን ወክለው የሚቆሙ ምልክቶች (ሆሄያት) ስብስብ ሲሆን ሆሄ ግን ለአንድ ድምፅ የሚወክል ምልክት ነው የሚለውን ትርጉም በመያዝ ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳይ ልመልሳችሁ፡፡

እዚህ ዝርዝር ውስጥ የገባሁት ወደፊት ባለው ጽሑፌ የሁለቱ ቃላት አገባብ አንባቢዎችን ግር እንዳያሰኝ በማሰብ ነው፡፡ እናም "አማርኛ የራሱ የሆነ ፊደል አለውን?" የሚለውን እንመልከት፡፡

አማርኛ የራሱ የሆነ ፊደል አለው ወይም የለውም የሚል ብያኔ ከመስጠታችን በፊት ግን የት መጣነቱን ማየት ወይም ማወቁ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ይህንንም ለመረዳት ከኢትዮጵያዊው ፊደል ማለትም ከግዕዝ ታሪካዊ አመጣጥ መነሣቱ ለግንዛቤ ይጠቅማል፡፡

ስለ ግዕዝ ፊደል አመጣጥ ሁለት ዓይነት አመለካከቶች መኖራቸው የታወቀ ነው፡፡ እነዚህም ሃይማኖታዊና ሳይንሳዊ አመለካከቶች ናቸው፡፡ የሃይማኖት ሊቃውንት ስለ ፊደል አመጣጥ ሲገልጹ፣ ፊደል ከአዳም ሦስተኛ ትውልድ በሆነው በሄኖስ አማካይነት ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠ ነው፡፡ በልሳን ተውጦና ተሰውሮ የነበረው አካሉ በሰማይ ገበታነት ተጥፎ፣ ተቀርጦ የተገለጠ ነው በማለት፤ (ኩፋሌ 5፥18)ን በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ ፊደሉም ግዕዝ ነው ይላሉ፡፡

የፊደሉም ሆሄያት መደበኛ ቁጥራቸው ከእሁድ እስከ ዐርብ በተፈጠሩት ፍጥረታት ልክ 22 ናቸው፡፡ በእነሱ ላይ ደግሞ በመጥበቅና በመመሳሰል ምክንያት ተደራራቢ ሆሄያት (ሰ፣ኃ፣ዐ፣ፀ) ሲጨመሩ ኻያ ስድስት ይሆናሉ በማለት ይገልጻሉ፡፡

በሳይንሳዊ አመለካከት በኩል የሚቀርበው የግዕዝ ፊደል አመጣጥ ታሪክ ግን ከሃይማኖት ሊቃውንት አባባል የተለየ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

እንደ ሳይንሳዊ ጥናት አድራጊ ምሁራን አባባል፤ የሰው ልጅ ፊደልን በሚሊዮኖች ዓመታት የዕድገት ደረጃዎች ለውጡ ቋንቋውን ከሥልጣኔ ዕድገቱ ጋር አብሮ እያራመደ ሲመጣ ያገኘው ውጤቱ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

በዚህም መሰረት አስቀድሞ ሸክላ፣ ቆዳ፣ ብረት፣ እንጨትና የመሳሰሉት ልዩ ልዩ ቅርፃቅርፆችንና ምልክቶችን በመጠቀም መልእክት ለማስተላለፍ ቻለ፡፡ በእነዚህ ሥዕላዊ ምልክቶች (Pictographic Symbols) ከመጠቀም አልፎም ወደ ጽሑፍ ቋንቋ (Writing Language) በቅቷል የሚል ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡

የሳይንሳዊ ጥናት ተመራማሪዎች ከላይ እንደተገለጸው፤ የሰው ልጅ ለንግግሩ ጽሑፋዊ መግለጫ የሆነውን ፊደል መፍጠር እንደቻለ አረጋግጠዋል፡፡ እዚህ ላይ ግን አንድ ልንገነዘበው የሚገባን ነገር ይኖራል፡፡ ሃይማኖታዊም ሆነ ሳይንሳዊ አመለካከት ያላቸው ሁለት ክፍሎች፤ በፊደል ታሪካዊ አመጣጥ ላይ የተለያየ አቀራረብ ቢኖራቸውም በአጠባበቅና በአጠቃቀም በኩል ግን በአብዛኛው አንድነት ያላቸው መኾኑን ልንረዳ ይገባል፡፡

ከላይ እንደተመለከትነው፤ የሰው ልጅ ፊደልን ከማግኘቱ በፊት ለፊደል መፈልሰፍ መሰረት የሆኑት ሥዕላዊ ምልክቶችን ይጠቀም እንደነበረ ተገንዝበናል፡፡ እነዚህ ሥዕላዊ ምልክቶች የግብፅ ሂሮግሊፊክ እና የመሶጶታሚያው ኩኒፎርም በመባል የሚታወቁ ናቸው፡፡ በዓለም ውስጥ ያሉት ፊደሎችም በሙሉ ከእነዚህ ሥዕላዊ ምልክቶች የተገኙ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡

የግብፅን ሂሮግሊፍክ (ሥዕላዊ ጽሑፍ) መሠረት በማድረግ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት 1800-1500 በሴማውያን ከተፈለሰፈው ጥንት ሲናዊ (Proto - sinaific) ፊደል፣ በርካታ ሌሎች ፊደላት መገኘት ችለዋል፡፡ ከተፈለሰፉት መካከል ግን እንደ ዐረብኛ፣ ዕብራይስጥኛና ኢትዮጵያዊኛ ያሉት እናት ፊደላቸውን መምሰል እየተውና እየራቁ በመሔድ የተገኙ ናቸው፡፡

ፊደል ወደ ገፅ 22 ዞሯል

## የግጥም ጥግ

### ዛሬም ይዞረኛል

ሄደ ... አለፈ ብዬ ትንሽ ፋታ ሳገኝ፣
የተጫነኝ ችግር የጠፋ ሲመስለኝ፣
ተመልሶ መጥቶ ጎንተል ያደርገኛል፣
የራቀ ሲመስለኝ ዳግም ይቀርበኛል፣
ከጋለው ሊጥደኝ መልሶ ይዞረኛል፡፡
እኔ ቀርቤው ነው? ወይ እሱ እየመጣ፣
የማንለያየው - የማንተጣጣ፡፡
አንዴ እየራቀ፣ ዳግም እየመጣ ...
ይሽከረከረኛል፣
ቁራኛዬ ሆኖ አልለቅህም ብሎ ...
ያንገበገበኛል፡፡
ከዚህ ችግር ዕዳ - ከእንቶ ፈንቶ ጣጣ፣
ሊያድነኝ ከሁሉም ከማጡ ሊያወጣ፣
ዳግም ወደ መሬት ክርስቶስ አይመጣ፣
ታዲያ እንዴት ልሁነው?
እንዲሁ እንዳለሁ ፍግም ልበለው!?
... ኸረ አሳዝናለሁ፣
... አፈር እከብዳለሁ፡፡
ይህ መንገራገጩ ጠቅልሎ አልሄድ ያለው፣
እንዴት ቢያፈቅረኝ ነው ከኔ የማይለየው!?
ፊትም፣ አምና፣ ዛሬ አልተውህ ብሎኛል፣
ነገሩ ምንድነው? - ዛሬም ይዞረኛል፡፡

ከአምሳሉ ጌታሁን ደርሰህ
ታህሣሥ 2007 ዓ.ም

# የእብዶች ሸንጎ

ምናባዊ ታሪክ

ደረጀ ይመር

አፈጉባኤው የጫት ገረዊናውን እያነሳ የንግግር ማድረጊያውን ጉብታ መሬት እየደጋገመ ያጎነዋል፡፡ ለፓርላማው አባላቱ ስለ ስብሰባው ፍሬ ነገር ሹክ ለማለት በእጅጉ እየተጣደፈ ነው፡፡ ጉሮሮውን በልቅላቂ የሀይላንድ ውሀ እያጠበ የመከፈቻውን ንግግር ጀመረ፤

"ከጊዜ ግሳንግስ ውስጥ ይህቺን ቅጽበት ብቻ ተውሰን እብዳታችንን ፊት መንሳት እንጀምራለን፡፡ ከእብደታችን ጋር ለመፋታት ስንዳዳ ማንገራገሩ ሊከፋብን ይችል ይሆናል፡፡ ማንገራገሩ ግን ግፋ ቢል አፍታን ነው የሚሻገረው፡፡ ጉባኤውን ከእብድ ጉባኤነት ልንታደገው ይገባል፤ ከተተመነለት የሰዓት ኮታ ውጭ ውልፊት የሚል ተሰብሳቢ ካለ ጫንቃችን ሊሸከመው ዝግጁ አይደለም፡፡" አለ ጭንቅላቷ ከጣቱ መሀል የደረሰችን ኒያላ ሲጋራን በፍቅር እየማገ፡፡

ስብሰባው ከጅመሩ ያልተዋጠለት እብድ፤ የንግግሩን ቅድሚያ በጉልበት ወሰደ፤፡፡ በሱስ ካበደው ወገን ነው፡፡ ይህ ወገን የሸንጎውን ሲሶ ክፍል ይሸፍናል፡፡ እብዱ የያዘውን የብረት ቁርጥራጭ እያንኳኳ ልፍለፋውን ተያያዘው፤

"ገደብ፣ ክልከላህን ፊት ንሳና ፍሬነገርህን ሹክ በለን፡፡ ቆይ ... ቆይ ... ዘንግቼው ... እንደውም ... ስብሰባውን ለምን በህሊና ጸሎት አንጀምረውም......"

"የህሊና ጸሎት ከእዚህ ምን ዶለው?" አፈጉባኤው በሀይለ ቃል እያበሻቀጠ የመልስ ምት ሰጠው

"ክቡር-አፈጉባኤ.......ይህንን ማዕረግ ተሸክመህ ለህሊና ጸሎት....እንግዳ መሆንህ ...ደንቆኛል፤ ለማንኛውም... የአብራካችን ክፋይ የሆኑ ...በተከርቸም አባዜ የሚናውዙ... የእግረ-ሙቅ...ሲሳዮችን.... ለማሰብ ሁላችንም ከተንጋለልንበት እንነሳ" አለ በስሜት ወዲህ ወዲያ እየተወዛወዘ፡፡

ከተንጋለለበት የተነሳ እብድ ግን ማየት አልቻለም፡፡ በተሰብሳቢው ልግምተኝነት የተነሳ እብደቱ ሊያገረሽበት ከአፋፍ ላይ ደርሶ ተናነቀው ፤ከውስጥ ሱሪው ውስጥ የተጎመደች ሲጋራውን አውጥቶ አየር ላይ ለመለኮስ ይጣጣር ጀመረ፤ መለፍለፉን ሳያቋርጥ፡፡

"እናንተ ብሎ እብድ ፤ይሄኔ ለቀፈታችሁ ውትወታ ጥሞና ስጡ ቢሏችሁ በአደባባይ ላይ ትበዙ ነበር፤ ዝንተአለም ጎብጣችሁ ብታዘግሙ ግድ አይሰጠኝም፤ እኔ እንደሁ.. አንድ ለራሴ አላንስም" በንዴት ስብሰባውን እረግጦ ተፈተለከ፤ግድ ያለው እብድ አልነበረም፡፡

የጉባኤው አየር ሊረግብ አልቻለም፡፡ አየሩም የተሰብሳቢው መንፈስ ተጋብቶበት በላይ በላይ እያበደ ነው፡፡ የሚንሸዋሸው የፌስታል ድምጽ ከርቀት እየሰነጠቀ መጣ፡፡ የሚታይ ሰው የለም፡፡ ድምጹ ግን እየቀረበ ነው፡፡ ትንሽ ሰከንድ ፈቀቅ እንዳለ ከድምጹ አቅጣጫ የተበጠሰ ኤርጌንዶ ነጠላ ጫማ ውስጥ የተቸረቸፉ የእግር ጣቶች ብቅ አሉ፡፡ ለጥቆ ቀርፋፋ ቀውላላ ሰው እንደ ጅብራ ተገተረ፡፡ ጅብራው በቀጣጠለው የላዉንደሪ ላስቲክ ውስጥ የጫት ገረባ፣'የመከኑ ሲጋራዎችና ከዳን አልባ የሀይላንድ ላስቲኮችን ሰብስቧል፡፡ ያዘለውን ኮተት ለፓርላማው ታዳሚዎች ከፈተላቸው፡፡ በሙሉ ሰፈሩበት፡፡ ከቅራቅንቦው ብፌ የየፍላጎታቸውን ለመቃረም እጃቸውን ሰደዱ፡፡ ጅብራው በፌስታሉ ውስጥ ያሉት ኮተቶች የእብዶቹ ሲሳይ ሲሆኑ ደንታ ባይሰጠውም፣ በማሳረጊያው ላይ ግን ለአንድ ነገር ስስት ያዘው፡፡ የገነፈለ ብዕር ነበር፡፡ ብዕሩን ሊያጋፍፍ እጁን የዘረጋውን እብድ አፈፍ አደረገው፡፡ ጅብራው ለወረቀትና ለብዕር ነክ ነገሮች በሚሰጠው ክብር ከዘመኑ እብዶች ለየት ይላል፡፡ "ምሁር እብድ ነኝ" ብሎ ስለሚያስብ ሌሎችን በንቀት ነው የሚመለከተው፡፡ በፈረንጅ አፍ ሲያወራ አላፊ አግዳሚው ሳይወድ በግዱ ቀልቡን ሰብስቦ ጆሮውን ያውሰዋል፡፡ ዛሬ እነዚህን የዘመኑ እብዶች ምን እንዳሰባሰባቸው ግር ተሰኝቷል፡፡ የገነፈለውን ብዕር ከደረቱ ላይ እንደለጠፈ ባለበት ተቸንክሮ ሁኔታውን ለመከታተል ወሰነ፡፡

ብቸኛዋ የሴት እብድ ተወካይ እጇ ላይ የሚያንኮራፉ ጨቅላ እንደታቀፈች ብድግ አለች፡፡ የተኛውን ጨቅላ ላለመቀስቀስ በጣም በዝግታ ታንሾካሹካለች፡፡ ለጨቅላዋ ምቾት እብደቷም አንዳንዴ ታጋሽ ይሆናል፡፡ የተነሳችበትን ፍሬ ሀሳብ በሹክሹክታ ድምጽ እየሰነዘረች ነው፡፡ ንግግሯ ለእብዶቹ ሊሰማቸው ስላልቻለ ባለ በሌለ ሀይላቸው ጆሯቸውን አስግገው ወደ ሹክሹክታው አዘነበሉ፡፡

"የጾታ እኩልነት ለምን በእብድ አለም አይሰራም፡፡ ጤነኛ ሆናችሁ የተጠናወታችሁ ንቀት አብዳችሁ እንኳ አይለቃችሁም፤ እብደት ማለት የጾታና የዘር አጥር የሌለው ልቅና ዝርግ ህይወት ነው፤ እናንተ እብድ አይደላችሁም፡፡ አውቆ አበድ ናችሁ፡፡ ማበዳችሁን ያወቃችሁ፡፡ ለእብደታችሁ ጤነኞች እውቅና እንዲሰጧችሁ የምትንገበገቡ የታይታ እብዶች፡፡ ጉስቁላናችሁን እንደ ቀብድ አሲዛችሁ ትርፍ ለማጋበዝ የምትታትሩ ከንቱዎች፤ከንፈር እንዲመጠጥላችሁ ላይ ታች የምትሉ አስመሳይ ቀውሶች!" ብላ በበለዘ ሻሿ ፊቷን አበሰችው፡፡

ቀውሶች የሚለውን ቃል ስታወጣ እልህ ቢጤ ስለተናነቃት፣ ድምጿ ከተኛው ጨቅላ ጆሮ ሰርስሮ ገባ፡፡ ጨቅላው በጩኸቱ አካባቢውን እውነተኛ የእብድ ሰፈር

ሸንጎ ወደ ገፅ 19 ዞሯል

# ባስ ቆዳ ካልሲው

ሌሊሣ ግርማ

## አጭር ልብወለድ

ድሮ ሰፈሩ እንደዚህ አልነበረም፡፡ ድሮ፤ ከአስር አመት በፊት ሊሆን ይችላል፡፡ እልም ያለን አራዶች ነን የሚሉ ሁሉ የሚያዘወትሩት ስፍራ ነበር፡፡ አሁን አራዳ በሙሉ ተሰፋ ቆርጧል፡፡ የአራዳ ልጅ ጊዜ አልፎበታል፡፡ የአዲስ አበባ ልጅ መሆንም የሚያሳፍር የድሮ ዘመን ሰውነት ነፀብራቅ ተደርጐ ተወስዷል፡፡

አራዳ ነን የሚሉ ብዙዎች ተሰደዋል፡፡ ያልተሰደዱት በከፍተኛ ሱስ ተጠምደዋል፡፡ አራዳ ለመስራትም ሆነ ለመስረቅ አቅም የለውም፡፡ አራድነት በምላስ ይታወቅ ነበር መጀመሪያ ላይ፡፡ ምላስም ግን በመጤዎቹ ተበለጠ፡፡

ድሮ ሰፈሩ እንደዚህ አልነበረም፡፡ ድሮ፤ ከአስር አመት በፊት ሊሆን ይችላል፡፡ እዚሁ ሰፈር ውስጥ ተቀምጠው ሲቅሙ በሚውሉበት አንድ ትንሽ ጫት ቤት ውስጥ አንድ እንግዳ ሰውዬ በሩን ከፍቶ ከእለታት አንድ ቀን ገባ፡፡

የሰፈሩ ነባር የሆኑት መጤን አይወዱም፡፡ አያምኑም፡፡ መጤ ሁሉ ወራሽ ነው የሚመስላቸው፡ ፡ የሚወረስ ነገር ባይኖራቸውም እንኳን መጤን ይፈራሉ፡፡ መጤ በሙሉ ገጠሬ ነው፡፡ ይሄንንም ጐልማሳ ገና ከመግባቱ ፊት ነሱት፡፡ ጢጋ ብለው ሊያስቀምጡትም አልፈቀዱም፡፡ ጫት ሻጩ ራሱ ከሚያውቀው ሰው በስተቀር ማስተናገድ የሚፈልግ አይደለም፡፡ ጐልማሳው ቢጫው ጀሪካን ላይ ተቀመጠ፡፡

"ምን አይነት?"

"እነሱ የያዙትን አይነት"

"የምትፈልገውን ሳታውቅ ነው እንዴ ልትቅም የመጣኸው!?"

"ቅሜ አላውቅም..ቅሜ አለማወቄ ወንጀል ነው"

ጫት ቤቱ ውስጥ የተኮለኮሉት አድፍጠው እያጠኑት ነው፡፡ ገጠሬ አለማወቁን ማሳወቅ አይፈልግም፡፡ ከድቁናው ቀድሞ ቄስ መምሰል ይፈልጋል፡፡ አጉል አራዳ በመሆን ነው ፋርነቱን በራሱ እጅ የሚያጋልጠው፡፡ ይሄኛው ለምን ራሱን በማጋለጥ እንደጀመረ አልገባቸውም፡፡

"ወንጀል አይደለም..የሚጣፍጠውን ስጠው... የተቀቀለውን ይስጥህ ወይንስ የታጠበውን?" ተሰፋ ከቆረጡት አራዶች አንዱ ጠየቀው፡፡

"የትኛው ይሻለኛል?" እያዝናት በመሆኑ ተደስቷል፡፡ አዲስ የቆዳ ጫማ ነው ያደረገው ግን ጫማው ጠቦታል፡፡ የገበሬ እግሩ ጫማውን አፈንድቶ ራሱን ነፃ ለማውጣት እየታገለ ይመስላል፡፡ ካልሲ አላደረገም፡፡ በሱሪው ያልሸፈነው የእግሩ ቆዳ እንደ አውራሪስ ቆዳ ወፍራም እና ግራጫ ነው፡፡

አራዳው ሊያማርጠው ተነሳ፡፡ ከጆንበ ውስጥ ጫት እያወጣ ገለፃ መስጠት ጀመረ፡፡

"ይኼኛው የሚያዘፍን ነው...ይኼኛው የሚያሳስብ...ይኸውልህ ይሄ ደግሞ ፍቅር የሚያስይዝ ጫት ነው...ፎቅ እና መኪና የምትፈልግ ከሆነ ደግሞ እቺኛዋን ቃም..."

"የሚያዘፍነውን ስጠኝ - ዘፈን እወዳለሁ"

"ዝህ!" ትልቁን እስር ሰጠው፡፡

የተሰጠውን ይዞ ቀረ፡፡ አራዳው ተመልሶ ተቀመጠ፡፡ በአራድነት የሚበልጠውን በማግኘቱ ደስ ብሎታል፡፡ ግን የተበለጠ መስሎ ለመብለጥ እንደመጣ አውቋል፡፡ ባላወቀ ሙድ መሀላቸው ሊገባ ነው፡፡

የተሰጠውን እስር እንደያዘ ቀረ፡፡ ወደ አራዶቹ ተመለከተ፡፡ እነሱ እንደሚያደርጉት ጫቱን ከፊት ለፊቱ አስቀመጠ፡፡ የጫት እግር መዘው ሲያወጡ አወጣ፡፡ ቀንበጥ ቀንበጡን ሲቀነጥሱ እሱም በጠሰ፡ ፡ ሲጐርሱ ጐረሰ፡፡በፊቱ ላይ በሚያሳየው ገፅታ ጫቱ በጣም እንደመረረው ያስታውቃል፡፡ ኮካ ይምጣልህ? ተባለ፡፡

አዎ እንደማለት ተውዘወዘ፡፡ ኮካው ሲመጣ በአንድ ትንፋሽ ግጥም አድርጐ ጨረሰው፡፡ "ጨምርልኝ" አለው ባለ ጫቱን፡፡ የትንሿ ጫት ቤት ብዙ ጭንቅላቶች በጐልማሳው ላይ ተነጣጥረዋል፡፡ ሁለተኛ ኮካ ተከፈተለት፡፡

ቅድም ጫት ያማረጠው አራዳ "ማንም አይጠጣብህም እኮ ቀስ ብለህ ተጐንጭ" አለው፡፡ ጐልማሳው እሺ አለ፡፡

ትንሽ ሲያመነዥግ ከቆየ በኋላ፤

"ልዋጠው ወይንስ ልትፋው?" አለው ለመካሪው አራዳ

"ከዋጥከው የሆድ ቁርጠት ይይዝሃል... ከተፋኸው ደግሞ የሉሉ ትከፍላለህ" አለው ያኛው ቀልጠፍ ብሎ፡፡

ጐልማሳው ማመንዠጉን ቀጠለ፡፡ ኮካውን ቀስ ብሎ ጠጣ፡፡ የጐረሰውን ጫት ሳይተፋም ሳይውጥም ማኘኩን ገፋበት፡፡

ሬዲዮው ከፍ ተደረገ፡፡ የአራዶቹ ሳቅ እና ቀልድ እሱ ላይ መሆኑ አልተሰማውም ወይንም አልገባውም፡፡ አንድ ሰአት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተሰጠውን ጫት ግጦ ጨረሰው፡፡ ሲውጥም ሆነ ሲተፋ አልታየም፡፡ አይኑ ፈጠጠ፡፡ የት እንዳለ የሚያውቅ አይመስልም፡፡ እጁን አሻሸ፡፡

"አሁን በጣም ደስ አለኝ" አለ፡፡ አራዶቹ "እንኳን ደስ ያለህ" አሉት፡፡ "ይድፋህ" ከማለት በተስተካከለ ቅላፄ፡፡

"እስክስታ ልውረድ?" ብሎ አስፈቀዳቸው፡፡ ውረድ አሉት፡፡ ተነስቶ በጠባቧ ጫት ቤት ውስጥ እየተሽከረከረ እስክስታ መታ፡፡ ጉንጩ ውስጥ የያዘው ተከዚና ፊቱ በየትኛው ጉን እንዳለ ያምታታል፡፡ እስክስታ ሲወርድ አጨበጨቡለት፡፡ ሲጨርስ ሌላ ዘፈን ጀመረ፡፡ ልቀጥል? ብሎ አስፈቀዳቸው፡፡ ቀጥል አሉት፡፡ ላቡ ጠብ እስኪል ትከሻውን ሰበቀ፡፡

ጫት ሻጩ ተቆጣ፡፡ "ይሄ ጭፈራ ቤት...ናይት ክለብ አይደለም! አርፈህ ቁጭ በል ወይ ውጣ!" አለው፡፡ እሺ ብሎ ተቀመጠ፡፡

አራዶቹ ለሻጩ አስረዱት "ጫት ቅሞ ስለማያውቅ ምርቃና እንደ ስካር መስሎት ነው... ተጠጥቶ እንደሚደነሰው ተቅሞ የሚደነስ መስሎት ነው" አሉት፡፡ እነሱን እንዳሳቃቸው እሱን አላሳቀውም፡፡

ተቀመጠ፤ ላቡን እየጠረገ፡፡ ዘፈኑ ተቀነሰ፡፡ "ሌላ ጫት ይጨመርልኝ" አለ፡፡

"ቅድም ያደቀቅሕውን መጀመሪያ ክፈል" ተባለ፡፡ የሱሪ ኪሱ ውስጥ ሲገባ ብዙ መቶ ብሮች ይዞ ወጣ፡፡ ለራሱም ለሌሎችም አዘዘ፡፡ አንድ ዙርባ ጫትን እንደ አንድ ጠርሙስ ቢራ ነው የቆጠረው፡፡ ሩብ ጫት የጠረረበት የሰፈር አውደልዳይ፤ አንድ ሙሉ ጫት ሲሰጠው እየተቀበለ ጥጉን ያዘ፡፡

"በጣም ደስብሎኛል" አላቸው ጐልማሳው

"ለምን?" አሉት፡፡

"ሎተሪ ስለደረሰኝ" አላቸው፡፡

"ስንት ደረሰህ?" ሎተሪውን አውጥቶ አሳያቸው፡ ፡ ሎተሪ የደረሰው ሰው በዝቅተኛ ገንዘብ (በሁለት ሺ ብር) የአንድ ሚሊዮን ብሩን ሎተሪ እጣ እንደሸጠለት ነገራቸው፡፡

"እንኳን ደስ አለህ" ብለው ጨበጡት...የደስ ደስ ሁሉንም ሊጋብዝ እንደሚፈልግ ነገራቸው፡፡ አብሽር አሉት፡፡

በቃመ ቁጥር ደስታው እየናረ በመምጣቱ፤ ምን ማድረግ እንዳለበት ጨነቀው፡፡

"ጨመቅ አድርገህ ቃም፤ ውህም አብዝተህ ጠጣ" አሉት፡፡

"አብዝቼ ካልጠጣሁስ?"

"አልወጣ ይልሀና...በኋላ በሺኖ መክፈቻ ካልሆነ ሰገራህ አይወጣም"

ሳቁበት፡፡ ሳቀላቸው፡፡

ካልሲ ከሚያዞር ሱቅ በደረቱ በጫት ቤቱ መስኮት ነጭ ካልሲ ገዛ፡፡ "ካልሲ ምን ያደርግልሃል... አንተ እኮ ምርጡን ካልሲ ነው የለበስከው"

"እውነታችሁን ነው...አዲስ ጫማ በአዲስ ካልሲ ካልተደረገ ይሸታል ብለውኝ እኮ ነው"

"የሚናገሩትን አያውቁም ይቅር በላቸው... የአንተ ካልሲ በአለም ዙሪያ ተፈልጐ አይገኝም፡፡ አንተ እኮ የማያረጅ፣ የማይሰፋ፣ የማይቆሸሽ ካልሲ ነው ያደረግኸው...የጨርቅ ካልሲ ጣጣው ብዙ ነው፡ ፡ አንተ የሌዘር ካልሲ ነው ያደረከው" ጐንበስ ብሎ እግሩን አየ፡፡ በተፈጥሮ ካልሲው ተኩራራ፡፡

"ይልቅስ በነገነት መደነስ ከፈለክ፤ በባንድ የሚቃምበት ቤት ስላለ እዛ ይዘንህ እንሄድ

...በብራስ ኦርኬስትራ ሌሊቱን ሙሉ እየተቃመ የሚጨፈርበት ቤት ነው"

"አሁኑኑ እንሂድ" ብሎ ተፈናጥሮ ተነሳ፡፡

"ቆይ ተረጋጋ እንጂ በባንድ የሚቃምበት ቤት ሌሊት ነው የሚከፈተው... በዚያ ላይ ሴቶች ይኖራሉ፡ ፡ ስለዚህ ሴቶቹ እንዲወዱህ ፍቅር የሚያሲዘውን ጫት እየቃምክ ቆይ፡፡ ፍቅር የሚያሲዘውን ጫት ስትጨርስ ፎቅና መኪና የሚያስገዛውንም ብትሞክር አይጐዳህም..."

"ልክ ነው...መኪና መግዛት አለብኝ፡፡ የሎተሪውን ብር ተቀብዬ ስመለስ ሚስትም ገዝቼ ወደ ሀገሬ ብገባ ማለፊያ ነው"

"ሴቶች ደግሞ መኪና ይወዳሉ ታውቃለህ አይደል...የእኛ የወንዶች አይን የተሰራው ከሴቶች ዳሌ እንደሆነው ሁሉ...የሴቶች አይን ደግሞ የተሰራው ከመኪና እቃ ነው...ለዚህ ነው መኪና ሲያልፍ አይናቸውን መንቀል የማይችሉት...እኛም ወንዶች ሴቶች ሲያልፉ አይናችንን ከዳሌያቸው ላይ መንቀል አንችልም አይደል?"

"ልክ ነህ...በደንብ ነው ነገሮችን የገለፅክልኝ... ስለዚህ መኪና መግዛት ይቀድማል ማለት ነው?"

"እንደ ምርጫህ ነው...በባንድ የሚቃምበት ቤት መዝናናት...ወይንስ ሴቶችን ማዝናናት ወይንስ መኪና?"

"መኪና ስንት ነው ዋጋው? አንድ ሚሊዮን ብር ነው የደረሰኝ"

"አንድ ሚሊዮን ብር ... አንድ ሚሊዮን መኪና መግዛት ይችል ነበር...ችግሩ ጐማው ነው፡፡ መኪና ያለ ጐማ አይሽከረከርም... ጐማ በጣም ውድ ነው፡ ፡ ጐማው ለምን መሰለህ ውድ የሆነው? ባዝሊን ስለሚያስፈልገው ነው፡፡ ባዝሊን ሀገር ውስጥ አይመረትም፤ የሚመጣው ከአውስትራሊያ ብቻ ነው፡፡ ባዝሊን ካልተቀባ ጐማ አይሽከረከርም፤ ስለዚህ ዋናው ጉዳይ መኪና ሳይሆን ባዝሊን ነው..." አለው አራዳው፡፡

"ስለዚህ ምን እንዳደርግ ትመክረኛለህ?" አለ ባለ ሌዘር ካልሲው፡፡

"እኔ እንዳጋጣሚ ባዝሊን በርካሽ ዋጋ የሚሸጥ ሰው አውቃለሁ፡፡ ሰውየው ሀገር ጥሎ ሊሄድ ስለሆነ የባዝሊን በርሜሎቹን የሚገዛው ሰው ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ በደንብ አስብበትና ባዝሊን ንግዱን ተረክቤ ልስራ የምትል ከሆነም ትችላለህ...አይ ተዝናንቼ ወደ ሀገሬ የሎተሪ ሽልማቴን ይዤ ልግባ ካልክም ያንተ ምርጫ ነው፡፡ ለማንኛውም ግን በደንብ አስቦ ለመወሰን እንዲረዳህ...ከዚህ ቤት ከመውጣትህ በፊት የማስላሰያ ጫቱን አንተም እኔም ብንቅም ጥሩ ነው...ከዛ ማታ ተያይዘን በባንድ ወደሚቃምበት ቤት እንሄዳለን"

"በጣም ነው ደስ ያለኝ ዛሬ...ስለተዋወቅኳችሁ ደስ ብሎኛል...ሁላችሁንም፡፡ በተለይ አንተ ስምህ ማነው?"

"ስሜን አስይዘህ ትበደርበታለህ አልነግርህም" ሌሎቹ ሳቁ፡፡

"ስምህ ራሱ የገንዘብ እውቀት ባለው ሰው የወጣ እንደሆነ ያስታውቃል...አቶ አስይዘህ ትበደርበታለህ... የአያትህ ስምስ?"

"ፊት አውራሪ አልነግርህም...የአንተስ?"

"የእኔ ኮንስታብል ዘረ ያዕቀብ ነው...በባንድ ስለሚጨፈርበት ጫት ቤት እዚያው ፖሊስ ጣቢያ ትነግሩኛላችሁ...መኪና ይምጣና አንድ ላይ እንሄዳለን..." መታወቂያውን አውጥቶ አሳያቸው፡፡ እውነትም ፖሊስ ነው፡፡

ፖሊስ ሲሆን ታዲያ ድንገት ቁጡ ሆነ፡፡ ፊቱ ጠበበ፤ ጫማው ሰፋ ያለ መሰለ፡፡


## ኪነጥበባዊ ዜና

### "የሶሻሊስቱ ጠንቋይ ጉዳይ እና ሌሎችም" መፅሀፍ ለንባብ በቃ




በደራሲ ሐማቱማ "The case of the Socialist witchdoctor" በሚል ርዕስ ተፅፎ በህይወት ታደሰ "የሶሻሊስቱ ጠንቋይ ጉዳይ" በሚል ወደ አማርኛ የተመለሰው መፅሃፍ ለንባብ በቅቷል፡፡ የተለያዩ በርካታ ታሪኮች ስብስብ የሆነው ይሄው መፅሃፍ፤ በአንድ ሶሻሊስት ጠንቋይ ላይ ያተኮረ ታሪክ የያዘ ሲሆን ሌሎችም አስገራሚ ፖለቲካዊ ታሪኮችን አካትቷል፡፡ መፅሃፉ በ307 ገፆች የተቀነበበ ሲሆን በ50 ብር ከ65 ሳንቲም ለገበያ ቀርቧል፡፡

### "የዘንድሮ ትዳሮች" መፅሀፍ ለንባብ በቃ




"የዘንድሮ ትዳሮች" በሚል ርዕስ በመቅደስ በቀለ (ማክዳ) ተፅፎ በእርከን ቢዝነስ ዲቨሎፕመንት አሳታሚ የታተመው መፅሐፍ በገበያ ላይ ውሏል፡፡ በቅርቡም ይመረቃል ተብሏል፡፡

በመፅሀፉ የዘንድሮ ትዳሮችን ጨምሮ ሌሎች እውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሰረቱ ከ15 በላይ አጫጭር ልቦለዶች እንደተካተቱበትና በ200 ገፆች ተሰናድቶ በ60 ብር ለገበያ እንደቀረበ ለማወቅ ተችሏል፡፡


የመፅሃፉ ደራሲ መቅደስ በቀለ (ማክዳ) የበርካታ ፊልሞች ደራሲና ዳይሬክተር ስትሆን "የዘንድሮ ትዳሮችና ሌሎች" ሁለተኛ መፅሃፏ መሆኑ ታውቋል፡፡ ደራሲዋ ከዚህ ቀደም "የፍቅር መስዋዕት" የተሰኘ መፅሃፍ አሳትማለች፡፡

### "እመሻሽ" የግጥም መድበል ለገባ ቀረበ

የገጣሚ የሺመቤት ካሳ "እመሻሽ" የግጥም መድበል ሰሞኑን በ25 ብር ለገበያ ቀርቧል፡፡

የግጥም መድበሉ 62 አጫጭርና ረጃጅም ግጥሞች የተካተቱበት ሲሆን ገጣሚዋ ማስታወሻነቱን ለቀደምት ደራሲያንና ለነገው ደራሲያን ማድረጓን አስታውቃለች፡፡

### "ኤል-ማጐት" መፅሃፍ ለንባብ በቃ





የደራሲ ስንዱ አካልነህ "ኤል-ማጐት" የተሰኘ የረዥም ልቦለድ መፅሃፍ እየተነበበ ነው፡፡

በጐንደር ማተሚያ ድርጅት ታትሞ ለገበያ የቀረበው መፅሃፉ መቼቱን በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ያደረገ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ መፅሃፉ በ75 ብር ለገበያ ቀርቧል፡፡

# “ባይተዋሩ” እንደ ልቦለድ ችሳ መባሉ

አብደላ ዕዝራ




ሲነበብ፥ እንደተገባደደም አእምሮ ዉስጥ የሚንገዋለል ልቦለድ ብርቅ ነዉ። በአንፃሩ ስሜት ለጥጦ ትረካዉ ሲደመደም የሚደበዝዝ የምንዘነጋዉ ያመዝናል። የአልበርት ካሙ “The Stranger” ወይም ሚፍታ ዘለቀ እንደተረጎመው፤ “ባይተዋሩ” ወደ ብዙ ቋንቋዎች የተመለሰና ከጥቂት የዓለም ምርጥ ልቦለዶች ጐራ የተመደበ ዘመናዊ ልጨኛ (classical) ነዉ። በመቶ ሃያ ሰባት ገፆች ተቀንብቦ 25 ብር የሚሸጠው ልቦለድ፤ አምና ታትሞ፣ ክብሩ መጻሕፍት መደብር አሁንም ያከፋፍለዋል። ዛሬ አንባቢ ተነፍጐ በ40 በመቶ ቅናሽ፣ ገዢ እያባበለ ለመፍዘዙ ምክንያቱ ምን ይሆን? አንድም ተርጓሚው ስለ ካሙ ልቦለድ ጥልቀትና ኪነውበት እንደ መግቢያ ያተተው፥ ደራሲውንም ለማስተዋወቅ የፃፈው አለመኖሩ ነዉ፤ አንድም አከፋፋዩ እስከ ዛሬ አያሌ ምሁራንን ያወያየና ያላተመ ልቦለድ መሆኑን ለማስተዋወቅ መትጋት እንዳለበት መዘንጋቱ ይሆናል። አልበርት ካሙ በሚመጥነው በጥሩ አማርኛ ለኛ አንባቢ ሲቀርብ፣ የፈረንሳይ ወይን ጠጅን የአበሻ አረቄ ስለተካው ተቆረፋፍዶ ተገለለ ብሎ ማፌዝ አይበጅም። በብዙ አልባሌ ትርጉም ስራዎች መጋረዱ ይቆጫል። ከዚህ በፊት መስፍን ዓለማየሁ የሄሚንግዌይን “ሽማግሌዉና ባህሩ”፣ ሣህለሥላሴ ብርሃነ ማርያም የራልፍ ኤሊሰንን “የሀገር ልጅ”፣ ቴዎድሮስ አጥላዉ “አልኬሚስት” … የመሳሰሉትን ድንቅ ልቦለዶች ቢተረጐሙም ትኩረት ሳይሰጣቸዉ፥ አንባቢ በጥሞና ሳይወያይባቸዉ ተጋርደዋል። ለመሆኑ Albert Camus ማን ነዉ?

ካሙ በሥነፅሁፍ የኖቤል ሽልማት የተበረከተለት ፈረንሳዊ ደራሲ ነዉ። እንደ የልቦለድ ደራሲ፥ ወግ ፀሐፊ፥ ጋዜጠኛና ፀሐፌ-ተዉኔት ስሙ የገነነ ነዉ። የብዕር ውጤቱ የህይወት ዘበትነት (the absurdity of life) የጠነነበት ቢሆንም ግለሰብ ለኑሮ ትርጉም ለመፍተል ሲጣጣርና ሲያቃስት ተተርኮበታል። ከሳርተር ጋር በህልውናነት ፍልስፍናና በማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም መጣጣምም መፋለስም ካሙ በአጭር እድሜው የኖረበት የተነፈሰበት ዐውድ ነዉ። ከሆነ ስፍራ በባቡር ለመሳፈር ሲጣደፍ ጓደኛዉ በሚኩና ካላደረስኩህ ብሎት እያሽከረከር ሲጓዝ በሌላ መኪና ይገጫሉ። ጓደኛዉ ሲተርፍ፥ ካሙ ግን በአደጋው ይሞታል። ልክ እንደ ፅሁፎቹ አሟሟቱም ፍልስፍናዉን -የሕይወት ዘበትነትን- አደመቀዉ። አያሌ ድንቅ ልቦለዶችና ተዉኔቶች ደርሷል። ከአንድ ሁለት ዐሰርት በፊት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር፣ጌታቸዉ ታረቀኝ፤ የካሙን እውቅ ተውኔት “Caligula” በውርስ ትርጉም ለመድረክ አብቅቶት ነበር፤ ዛሬ ሚፍታ ዘለቀ ከተረጐመው ልቦለድ “ባይተዋሩ” የተሻለ ተቀባይነት ነበረው። በተቀራራቢ ጊዜ ነበር ካሙ “ካሊጉላ” ተውኔት፣ “ባይተዋሩ” ልቦለድና እነዚህን ሁለቱን የፈጠራ ሥራዎቹን የደመቀበት ያጐላበት ዝነኛ ፍልስፍናዊ መጽሐፉን “የሲሲፈስ ሥነተረት” (The Myth of Sisyphus) ያሳተመው። በመጣጥፉ የኑሮን ዘበትነትና ሰው ለፖለቲካ፥ ለሃይማኖትና ለማህበራዊ እሴቶች ማጐብደድ ሣይሆን -nihilism- ግለሰባዊነትን መምረጡን ተንትኗል። ቀስ እያለ አልበርት ካሙ ከሁለተኛ ዓለም ጦርነት በኋላ የትውልዱ አፈቀላጤ፥ የነገውን የፈረንሣይ፥ የአዉሮፓ ብሎም የዓለም አስተሳሰብና አዝማሚያ ጠቋሚ ሊሆን በቅቷል። ካሙ በስራዎቹ የክርስርትናና የማርክሲዝምን ቀኖናዊ አስተምህሮ እየተጋፈጠ፥ የዘመንተኞቹን በማህበራዊ እሴቶች የማመፅ -nihilism- አደጋ ቢያጣጥምም ለዕውነት፥ ለሀቅና ለሰከነ አቋም ከመሚገት አላፈገፈገም።

በግሪኮች ሥነተረት (ሚት) ሲሲፈስ ከሞተ በኋላ በሰማይ ቤት ሆኖ ምድር እጅጉን እየናፈቀው ለመንደሩ በቋጠረው ፍቅር ተንከራተተ፤ ልቡ ቃተተ። ለአንድ ቀን ብቻ አስፈቅዶ ከቀዬው ይመለሳል። ደስታ አብከነከነው፤ የኑሮ ጣዕሙ አልከስም አለ። የገባዉን ቃል አፍርሶ ከምድር ይቀራል። አማልክት በንዴት ይበግናሉ። እንደገና እስኪሞት ለአመታት ጠበቁት፤ ከመዳፋቸዉ ሲገባ እንዴት እንደሚቀጡት ካብሰለሰሉ በኋላ ይበየንበታል። አንድ ትልቅ አለት ከተራራ ሥር ሽቅብ እየገፋ ከተራራው ቋፍ እንዲያደርስ፥ ዝንተዓለም ይህን እንዲፈፅም ይፈረድበታል። ችግሩ አለቱን ገና ከተራራው ጫፍ እንዳዘለቀዉ ተንከባሎ ከነበረበት ሥፍራ ይመለሳል። ሲሲፈስ ረጅም መንገድ ተመልሶ እንደገና አለቱን መግፋት አለበት- ዝንተዓለም። Camus ሲሲፈስ ማለት የዘመናችን ሰው ነው፤ ዘመነኛ ሰው ዘወትር ይማስናል፥ ግን አያልፍለትም ባይ ነዉ። እንደ ሲሲፈስ ሽቅብ ሲባዝን፥ ቁልቁል ሲያዘቀዝቅ ይኖራል ከሚል ርዕዩት በመነሳት፣ ስለ ህይወት ዘበትነት -absurdity- በጥልቅ አውጠንጥኗል። ከሐያስያንና ምሁራን የሚበዙት፣ “ባይተዋሩ” ልቦለዱን የደረሰው ለሰው ህይወት ዘበትነት መግለጫ ነው ይላሉ። በእርግጥ ካሙ የግሪኩን የሲሲፈስን አፈ-ታሪክ፣ ግለሰብ የኑሮ ከንቱነቱ በእልህ ሲፋለም እንደ ተለዋጭ ዘይቤ -metaphor- ተጠቅሞበታል። እንደ ካሙ እምነት ከሆነ፣ የአንድ ግለሰብ የመጀመሪያ እርምጃ መሆን ያለበት የዚህን ዘበትነት እውነታ መቀበል ነው። ለሲሲፈስ -ለዘመነኛ ሰውም- የራስን ህይወት ማጥፋት መፍትሄ አይደለም፤ ብቸኛ ምርጫ ደስ እያለው አለቱን ሽቅብ በመግፋት ዘበትነት ላይ ማመፅ ነው ባይ ነው። የካሙ ተጨማሪ ክርክር ግለሰብ እየፈነደቀ ይህን የአለመሸነፍ ትግሉን እልሁን ሲወጣ እንደ ሰው ትርጉምና ማንነት ይጐናፀፋል። ሌሎች ደግሞ የሲሲፈስ -የዘመነኛ ሰው- ረብ ቢስ የሆነውን የአለት ሽቅብ መግፋት ከንቱ ድካም ሳይሆን የሚያሳስባቸዉ፥ አለቱ ተንከባሎ ረጅም ርቀት ከወረደ ባኋላ ዘመነኛ ሰው ቁልቁለቱን ሲወርድ ብቻውን ከራሱ ጋር በየዕለቱ የሚያውጠነጥነዉ ጉዳይ ነዉ፤ ምን እያብሰለሰለ ያዘግማል ? የመሰለ ጥያቄ እጅጉን አወያይቷል።

“ባይተዋሩ” ልቦለድ በሁለት ክፍሎች ተዋቅሯል። ዋናው ገፀባህሪና ተራኪው መርሶ -meursault- በክፍል አንድ፣ ነፃ ሰው እያለ በሥራ ተጠምዶ በኋላም እናቱ ከአረጋውያን መጦሪያ ስለአረፉ ለቀብር ተጠርቶ፣ ተመልሶም ከውቧ ሴት ጓደኛው ሜሪ፣ ህይወትን ሲያጣጥም ባልጠበቀዉ ወቅትና ስፍራ ሳያስብበት አንድ አረብ ገድሎ ይያዛል። በዚህ ክፍል የጐረቤቶቹ ገመና፥ እና የእለት በእለት ህይወቱን አንዳንዴ እያውጠነጠነ፥ በሌላ ወቅት በዝምታ እንደ ገለልተኛ እያጤነ ያወጋል። በክፍል ሁለት መርሶ ሰው መግደሉን እንደ ቀላል ጉዳይ እየቆጠረ፣ ከወህኒ ቤት ለአስራ አንድ ወራት ያህል የፍርድ ቤት ውሳኔ እየጠበቀ ብቻውን ይታሰራል። የአደባባይ ኑሮ እየናፈቀው፥ ኢ-አማኝ በመሆኑም ምንም የመንፈስ የፈጣሪ እርዳታ ሳይለማመጥ ትናንቶቹን፥ ትዝታውን፥ የቤቱን ዕቃ ጭምር በእእምሮው እያመላለሰ የእስር ቤቱን የተንዛዛ ጊዜን ለመገድብ ይተጋል። *“ቀጥሎ የተረዳሁት ነገር ቢኖር አንድ ቀን እንኳ በህይወት የኖረ ሰው እስር ቤት ቢገባ ከድብርት የሚያድኑት በቂ ትዝታዎች ስለሚኖሩት መቶ አመታትን በእስር መኖር እንደሚችል ነዉ”* [ገፅ 81] ቀስ በቀስ የግሉን ውስጣዊ ህይወት ይበረብራል። በሁለቱም ክፍሎች በየገፁ የሚመስጡ ሁነቶች፥ እንግዳ ድርጊቶች፥ ከተቀበልነው አመለካከት ያፈነገጡ እሳቦቶች ይርመሰመሳሉ። ዝርዝር ሤራዉንና የሌሎች ገፀባህርያት ውጣውረዱን ለአንባቢ በማስተረፍ በደምሳሳው ስለ ባይተዋሩ ነጥቦች መቀስቀስ ይበቃል።

ገና ከመነሻው መርሶ እውነትም ባይተዋር ይሆንብናል። እናቱን ለመቅበር ወደ አረጋውያን መጦሪያ ሲሄድ የሚያስተዛዝኑት እድሜዋን ቢጠይቁት አለማወቁን ይገልፃል፤ ማዘኑን አያሳውቅም። በማግስቱ ከሴት ጓደኛው ጋር አስቂኝ ፊልም አይቶ፥ ዋኝቶ ይዳራታል።

*“ስንለባብስ ጥቁር ከራቫት መልበሴን በማየቷ የተገረመች መሰለችና ለቅሶ ሰንብቼ እንደሆን ጠየቀችኝ። እማዬ እንዳረፈች ነገርኳት። መች እንደሆነ ለማወቅ ፈለገች።*

*“ትላንት” አልኳት።*

*ትንሽ ደንገጥ ብትልም ምንም አልተናገረችም። የእኔ ጥፋት እንዳልሆነ ልነግራት ፈለግኩና ተውኩት። … ባወራውም ምንም ትርጉም የለውም።”* [ገፅ 21]

ማህበረሰቡ ከሱ የሚጠብቀውን ጉዳይ ለይሉኝታ እንኳን ማስመሰል አልፈቀደም። የተለያዩ ገፅታዎች በመለዋወጥ ታርቆ ማደር፣ ልክ አዳም ረታ በ “ይወስዳል መንገድ …” እንደቀረፃቸዉ ወይዘሮ አስካለ መኖር አይችልም። ወይዘሮ አስካለ የሟች ባላቸዉ የጡረታ ገንዘብ ለእለት ጉርስ ስለማይበቃቸው ወንድና ሴት በማገናኘት ይተዳደራሉ። ታድያ በየአፍታ ገፃቸውን ይለዋውጣሉ። *“ገፃቸዉ የፈገግታ ማስክ ለብሷል። ጓዳ ሲመለሱ ያወልቁታል። ወደ ሳሉን ሲመጡ ይለብሱታል። ሲለብሱ ሲያወልቁ ሊውሉ ነዉ ”* መርሶ ያለ ማስኮች ሌጣ ግልፅ ገፁን እየወለወለ በመኖሩ ነዉ ከማህበረሰቡ በባይተዋርነት የተነጠለው። እድገቱም፥ ውድቀቱም ሆነ።

*“ሜሪ … የኔን የሴሊት ልብስ እጅጌውን ጠቅልላ ለብሳለች። ስትስቅ እንደገና አማረችኝ። ከአፍታ በኋላ አፈቅራት እንደሆነ ጠየቀችኝ። ማፍቀር ምንም ማለት እንዳልሆነና እማፈቅራት እንደማይመስለኝ ነገርኳት። ያዘነች መሰለኝ። … የዛን ቀን ምሽት ሜሪ ልታየኝ መጥታ ላገባት ፍላጐት ያለኝ እንደሆነ ጠየቀችኝ። በእኔ በኩል ምንም ልዩነት እንደማያመጣና እሷ ከፈለገች እንደምንጋባ ነገርኳት። አፈቅራት እንደሆን ማወቅም ፈለገች። የቀድሞውን መልሴን ደገምኩላት። ፍቅር ምንም ማለት አይደለም። … “ታድያ ለምን ታገባኛለህ?” ስትል በእውነቱ እሷ ከፈለገች እንደምንጋባ ነገር ግን ለውጥ እንደሌለው ደገምኩላት። … ጋብቻ የዋዛ ፈዛዛ ሳይሆን ታላቅ ቁም ነገር መሆኑን ጠቀመችኝ። “አይደለም” አልኳት። … ራሷ ታፈቅረኝ እንደሆነ ለማወቅ በመቸገሯ ተገረመች። እኔም ይህንን ላውቅ ምችልበት መንገድ የለኝም። ከሌላ ዝምታ በኋላ ግራ አጋቢ መሆኔን አጉረመረመች። ምናልባትም ለዚህ ይሆናል ያፈቀረችኝ።”* [ገፅ 37፥ 43-44]

መርሶ በጣም ለሚቀርቡት እንኳን እንዳይቀየሙኝ ብሎ የማስመሰል ባህርይ የለውም፤ እውነቱን እስከተናገረ ድረስ ሌላው ለሚጨነቅበት ጉዳይ ደንታ የለውም። የመሰለውን ከማድረግ አያፈገፍግም፤ የማህበረሰቡን መርህ ባለመከተሉ እንደ እንግዳ - እንደ ባይተዋር ይታዘቡታል። ጓደኛው የሚንከባከባትን ፍቅረኛውን ስለተቀያየሙ ክፉኛ ይደበድባታል፤ ወንድሟ ለበቀል ከጓዳኛው ሲጣሉ በአረቡ ላይ እንዳይተኩስ መርሶ ሽጉጡን ቀምቶት ከኪሱ ይሸሽገዋል። ነገር ከረገበ በኋላ ሙቀቱና ፀሀዩ ወብቆት ለመናፈስ፣ መርሶ ብቻውን ከባህር ዳርቻ ሲሄድ ከአረቡ ጋር ይገጣጠማል።

*“አረቡ ከተቀመጠበት ሳይነሳ ጩቤውን ወደ እኔ አስተካከለ። ጩቤው ላይ ያረፈው የብርሃን ብልጭታ ልክ ግንባሬን የሚዘነትል ረዥም ሰይፍ አይነት ነበር። በዚያች ቅፅበት ከቅንድቤ ወደ አይኑ-ርግቤ ጠብ ያለው ላብ አይታዬን በአንዴ በሙቀትና በብዥታ ሸፈነው። … የታወቀኝ ቢኖር ግንባሬን እንደሚደፈጥጠዉ ሹል የፀሀይ ጨረር እና በቅጡ የማይታየኝ የሚያበራው የጩቤው ጫፍ ከፊት ለፊቴ እየበረረ ወደ እኔ መምጣቱ ነበር። …ሁሉመናዬ ተቆጥቶ በእጄ ሽጉጡን ጠበቅ አደረግኩ። ቃታዉ ሲላቀቅ እጄታው ነቀነቀኝ። … በተጨማሪ አራቴ ተኮስኩ። ጥይቶች ምልክት ሣይተው በማይንቀሳቀሰው ሰዉ አካል ስር ተቀበሩ። የሀዘንን በር አራቴ በፍጥነት እንደማንኳኳት አይነት ነበር።”* [ገፅ 59-60]

የማያውቀዉን ግለሰብ በብዥታ ምክንያት ከገደለ በኋላ ለእስር ቤትና ለፍርድ ውሳኔ ሲጋለጥ ይህ ከማህበረሰቡ መርህ አለመግጠሙ - አለመዋሸቱ፥ ኢ-አማኒ መሆኑ፥ የአስተሳሰብ ባይተዋርነቱ - ፈተና ይሆንበታል። በመለወጥ እና በመጐምራት ላይ እያለ ነው ልቦለዱ የሚያበቃው። አንብበነዉ መርሶ ስለሚመስሉና ስለማይመስሉ ግለሰቦች እንድናጤን ይገፋፉናል፤ ራሳችንም “ባይተዋር ነን ወይ?” በማለት እንጠይቃለን። ያው በዕዉቀቱ ስዩም በ *ስብስብ ግጥሞቹ”* ገፅ 72፣ *የባይተዋር ገድል* ብሎ እንደተቀኘዉ ነዉ።

*በቁም መስተዋት ፊት መቆምህ ሲጨንቅህ*
*የቁም መስተዋቱ፥ ”ሰውነትህ የታል?” ብሎ ሲጠይቅህ*

……….

*“መንሳፈፉስ ይቅር፥ መስጠም ያቅተዋል ሰው?”*
*ሲያሰኝህ እድልህ*
*ያኔ ይጀምራል፥ የባይተዋር ገድልህ።*

የአልበርት ካሙ “ባይተዋሩ”፣ በአማርኛ ተገርቶ የሚያጣጥመዉ ተደራሲ መነፈጉ፥ ለንባብም አንድ የዘበትነት -absurdity- ጠገጉ ነዉ።

## ኪነጥበባዊ ዜና

### “በሕይወት መስኮት” ዛሬ በሀዋሳ ከተማ ይመረቃል

በጋዜጠኛና ደራሲ አሰግድ ሀምዛ ተፅፎ የታተመው “በህይወት መስኮት” የተሰኘ መፅሃፍ ዛሬ በሀዋሳ ከተማ ይመረቃል፡፡ መፅሃፉ፤ ወጎችና የፍቅር ደብዳቤዎችን ያካተተ ሲሆን ደራሲው በመምህርነት ባገለገለበት ሙርሲ ብሔረሰብ ውስጥ የታዘበውንና የኖረውን እውነታ በሚጥም ቋንቋና ውበት ፅፎታል፡፡

141 ገፆች ያሉት መፅሀፉ ዛሬ ሲመረቅ፣ የዘርፉ ምሁራን አስተያየት የሚሰጡ ሲሆን በስነ ስርዓቱ ላይ የጥበብ አፍቃሪዎችና ቤተሰቦች እንደሚታደሙ ታውቋል፡፡ መፅሃፉ አገር ውስጥ በ40 ብር፣ በውጭ አገር በ8 ዶላር እንደሚሸጥ ተገልጿል፡፡

# ፑቲን ለሚኒስትሮቻቸው የአዲስ ዓመት እረፍት የለም አሉ



የሩሲያ ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን በተከሰተው የኢኮኖሚ ቀውስ ምክንያት ሚኒስትሮቻቸው የአዲስ ዓመት እረፍት እንደማይወስዱ ሰሞኑን አስታወቁ፡፡ በሩሲያ ትልቁ በዓል እንደሆነ በሚነገርለት የፈረንጆች አዲስ ዓመት፤ በመላ አገሪቱ የሚገኙ የሩሲያ ኩባንያ ሰራተኞች ለበዓሉ የ12 ቀናት እረፍት ይወስዳሉ፤ ከጃንዋሪ 1 እስከ 12፡፡

ፑቲን ባለፈው ሐሙስ በቴሌቪዥን በተሰራጨ የመንግስት ኃላፊዎች ስብሰባ ላይ፣ በዚህ ዓመት የካቢኔ ሚኒስትሮቻቸው እረፍት መውሰድ እንደማይገባቸው ተናግረዋል፡፡ “ቢያንስ ለዚህ ዓመት መንግስት ይሄን ረዥም የበዓል ዕረፍት መስጠት አይችልም - መቼም የምለው ይገባችኋል” ብለዋል - ፕሬዚዳንቱ፡፡

የአገሪቱ ጠ/ሚኒስትር ዲሚትሪ ሜድቬዴቭ በበኩላቸው፤ በበዓሉ ወቅትም ጭምር (ከዓመቱ የመጀመሪያ ቀናት አንስቶ) የኢኮኖሚውን ሁኔታ እንዲከታተሉላቸው እንደሚፈልጉ ለሚኒስትሮቹ ነግረዋቸዋል፡፡

በነዳጅ ዋጋ መቀነስና በምዕራብ አገራት ማዕቀብ ክፉኛ የተጎዳው የሩሲያ ኢኮኖሚ፤ ከስድስት ዓመታት ወዲህ ለመጀመሪ ጊዜ በቀጣዩ ዓመት “ድቀት” ውስጥ የሚገባ ሲሆን፣ የአገሪቱ ገንዘብ ሩብልም በአሁኑ ሰዓት ከዋጋው ግማሽ በታች ወርዷል፡፡ ከያዝነው ወር መጀመሪያ አንስቶ አንድ ዶላር በ80 ሩብል ሲመነዘር የቆየ ሲሆን፣ ባለፈው ሐሙስ የ2 በመቶ መጠነኛ መሻሻል አሳይቶ አንድ ዶላር በ52 ሩብል መመንዘሩ ታውቋል፡፡

የሩሲያ ማዕከላዊ ባንክ የአገሪቱ መጠባበቂያ ገንዘብ ከ2009 ዓ.ም ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ ከ400 ቢሊዮን ዶላር በታች መውረዱን አስታውቋል፡፡ ዋጋው እጅግ ያሽቆለቆለውን የአገሪቱን መገበያያ ሩብል ማረጋጋት፣ የሩሲያ የገንዘብ ኃላፊዎች ተቀዳሚ ስራ ይሆናል ተብሏል፡፡ ከዩክሬን ጋር በተያያዘ በአገሪቱ ላይ የተጣለው ማዕቀብ፣ በርካታ የሩሲያ ኩባንያዎችን ከምዕራብ አገራት የፋይናንስ ገበያ እንዳስወጣቸው ተዘግቧል፡፡

# መኪና ሲያሽከረክሩ የተያዙ የሳኡዲ ሴቶች በሽብርተኝነት ሊከሰሱ ነው



መኪና ሲያሽከረክሩ የተያዙ ሁለት የሳኡዲ ሴቶች ለአንድ ወር ገደማ ከታሰሩ በኋላ ባለፈው ሳምንት ጉዳያቸው ሽብርተኝነትን ለሚመለከት ልዩ ፍ/ቤት እንደተላለፈ ተገለፀ፡፡

የ25 ዓመቷ ሎዩጂይን አል ሃትሎል እና የ33 ዓመቷ ማይላ ይሳ አል - አሙዲ ጉዳይ ወደ ልዩ ፍ/ቤት የተላለፈው በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በሰጡት አስተያየት ነው ብለዋል - የመብት ተሟጋቾች፡፡ ሳኡዲ በዓለም ላይ ሴቶች መኪና እንዳያሽከረክሩ የምትከለክል ብቸኛ አገር ናት፡፡

ሴቶች መኪና እንዳያሽከረክሩ በፅሁፍ የተቀመጠ ህግ ባይኖርም የመንጃ ፈቃድ የሚሰጠው ግን ለወንዶች ብቻ ነው፡፡ ሴቶች በአደባባይ ሲያሽከረክሩ ከተገኙም በፖሊስ ተይዘው ከመታሰርም ባሻገር ይቀጣሉ፡፡


የሳኡዲ ሴቶች መኪና እንዳያሽከረክሩ የተጣለባቸው እገዳ እንዲነሳላቸው ማህበራዊ ሚዲያን ጨምሮ የተለያዩ ተከታታይ እንቅስቃሴዎች ሲያካሂዱ ቆይተዋል፡፡

አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ የዜና ወኪል እንደዘገበው፤ ሚስ ሃትሎል የተያዘችው ከጐረቤት አገር፣ ዩናይትድ አረብ ኢምሬትስ እያሽከረከረች ወደ ሳኡዲ ለመግባት ስትሞክር ነው፡፡

ነዋሪነቷን በዩናይትድ አረብ ኢምሬትስ ያደረገችው የሳኡዲ ጋዜጠኛ ሚስ አላሙዲም የተያዘችው ሚስ ሃትሎልን ለመርዳት ድንበር ላይ ስትደርስ ነው ብሏል - የዜና ወኪሉ፡፡

ሁለቱም ሴቶች በትዊተር እጅግ በርካታ ተከታይ ያሏቸው ሲሆን ሚስት ሃትሎል ወደ አገሪቱ ለመግባት አንድ ቀን ሙሉ ያቸውን ውጣ ውረድ በትዊተር ገጿ ላይ እንዳሰፈረች ተዘግቧል፡፡ ባለፈው ሐሙስ በአገሪቱ ምስራቃዊ ክፍል የሚገኘው አል - አህሳ ፍ/ቤት፤ የሁለቱ ሴቶች ጉዳይ በሪያድ የሽብርተኝነት ክሶችን ለመከታተል በተቋቋመው ልዩ ፍ/ቤት እንዲዳኙ በይኗል፡፡ የሴቶቹ ጠበቆች ግን ይግባኝ ለመጠየቅ ማሰባቸውን የመብት ተሟጋቾች ለአዣንስ ፍራንስ ፕሬስ ጠቁመዋል፡፡

# ጆርጅ ቡሽ ገናን በሆስፒታል አሳለፉ



የትንፋሽ ማጠር ገጥሟቸው ባለፈው ማክሰኞ ሂዩስተን ሜቶዲስት ሆስፒታል የገቡት የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ኤች ደብሊው ቡሽ፤ ከትላንት በስቲያ የተከበረውን የፈረንጆች የገና በዓል በሆስፒታል አሳለፉ፡፡

የፕሬዚዳንቱ ቃል አቀባይ ጂም ማክግራዝ፤ ቡሽ በጥሩ ጤንነት ላይ እንደሚገኙና የገና በዓልን በሆስፒታል ያሳለፉት በሽታው ከፍቶባቸው ሳይሆን ለጥንቃቄ ሲባል እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ የዛሬ ሁለት ዓመት በተመሳሳይ ጊዜ ብሮንካይትና በሃይለኛ ሳል ይዟቸው ሆስፒታል ከገቡ በኋላ የገና በዓልን ጨምሮ ለሁለት ወራት እዚያው መቆየታቸውን ያስታወሱት ቃል አቀባዩ፤ የአሁኑ ግን ከቀድሞው በጣም ይለያል ብለዋል - የፕሬዚዳንቱን ጤናማነት ሲገልፁ፡፡

የፕሬዚዳንቱ ሆስፒታል መግባት ላሳሰባቸው በርካታ ወዳጆችና አድናቂዎቻቸው የቡሽ ዋና ኃላፊ በሰጡት መግለጫ፤ “የቡሽ ቤተሰብ፤ ለጭንቀታችሁ፣ ለፍቅራችሁና፣ ለፀሎታችሁ በእጅጉ ያመሰግናል፡፡ ይሄ የዛሬ ሁለት ዓመት እንደሆነው ዓይነት አይደለም፡፡ የትንፋሽ ማጠር ነው፡፡ በጥቂት ቀናት ውስጥ ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ” ብለዋል፡፡ ቡሽ ሆስፒታል መግባታቸውን የሰሙት ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ እና ባለቤታቸውም ለቀድሞው ፕሬዚዳንትና ለመላው የቡሽ ቤተሰብ የመልካም ጤንነት ምኞታቸውን ልከዋል፡፡

ሪፐብሊካኑ የ90 ዓመቱ ቡሽ፤ 41ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በመሆን አገራቸውን ያገለገሉ ሲሆን የ43ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ደብሊው ቡሽም አባት ናቸው፡፡ የዊልቸር እስረኛ ባደረጋቸው ከፍተኛ የነርቭ ህመም ሲሰቃዩ የቆዩት ቡሽ፤ በቅርቡ ግን ነቃ ነቃ ማለት ጀምረው ነበር ተብሏል፡፡ ባለፈው ሰኔ ለ90ኛ ዓመት የልደት በዓላቸው ከሄሊኮፕተር ላይ በፓራሹት የዘለሉ ሲሆን የዛሬ ወር “41፡ A Portrait of My Father” የተሰኘ አዲስ መፅሃፋቸው የምረቃ ስነስርዓት ላይ ከልጃቸው ጋር ተገኝተው ነበር፡፡

ፕሬዚዳንት ሆነው የተመረጡበትን 25ኛ ዓመት በዓል በቅርቡ ያከበሩት ጆርጅ ቡሽ፤ በፕሬዚዳንት ሮናልድ ሬገን ዘመን ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው አገልግለዋል፡፡

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በባህር ኃይል አብራሪነት የተሳተፉ ሲሆን ወደ ፖለቲካው ዓለም ከመግባታቸው በፊት በቴክሳስ የነዳጅ ኢንዱስትሪ ውስጥ እንደሰሩ የህይወት ታሪካቸው ያወሳል፡፡

# የተባበሩት ብሔራዊ ፔትሮሊየም ባለ 11 ፎቅ ህንፃ ሊገነባ ነው

ናፍቆት ዮሴፍ

በ21 ኢትዮጵያዊያን የተመሰረተውና ነዳጅ በማከፋፈል የመጀመሪያው አገር በቀል ድርጅት የሆነው የተባበሩት ብሔራዊ ፔትሮሊየም አክሲዮን ማህበር ለዋና መስሪያቤትነት ባለ 11 ፎቅ ህንፃ ሊገነባ ነው፡፡ ድርጅቱ ከትናንትና በስቲያ ሲኤምሲ በሚገኘው ማደያ ግቢ ውስጥ የተመሠረተበትን 10ኛ ዓመት በዓል ከባለ አክሲዮኖቹ ጋር በድምቀት ያከበረ ሲሆን የመስኖ፣ የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር አቶ አለማየሁ ተገኑ የህንፃውን የመሰረት ድንጋይ አኑረዋል፡፡ 50 ሚሊዮን ብር እንደሚፈጅ የተገመተው ህንፃ፤ ከዋና መስሪያ ቤትነት በተጨማሪ ለተለያዩ አገልግሎቶችም ይውላል ተብሏል፡፡ 261 ባለአክሲዮኖችና የተከፈለ 135 ሚሊዮን ብር ካፒታል ያለው የተባበሩት ብሔራዊ ፔትሮሊየም፤ በመላ አገሪቱ መቶ ያህል ማደያዎች ያሉት ሲሆን ከአንድ ሺህ በላይ ለሆኑ ቋሚና ጊዚያዊ ሰራተኞች የስራ እድል መፍጠሩን የድርጅቱ ዋና የስራ አስኪያጅ አቶ ተስፋዬ መኮንን በእለቱ ባደረጉት ንግግር ገልፀዋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ጥራት ያለው ነዳጅ ከማከፋፈሉም በላይ ጥራት ያላቸው የብሪቲሽ ፔትሮሊየምን የሞተር ዘይቶች በብቃት እንደሚያከፋፍል የተናገሩት ሥራ አስኪያጁ፤ የነዳጅ ማደያ ምልክቱንም ቢሆን በአንድ ወጣት ኢትዮጵያዊ አሰርተው ማስገጠማቸውን ተናግረዋል፡፡ የውሃ የመስኖና ኢነርጂ ሚኒስትሩ አቶ አለማየሁ ተገኑ ባደረጉት ንግግር፤ አገር በቀል ድርጅቶች ነዳጅ ቢያከፋፍሉ ለአገር ጠቀሜታ ያለውን ፋይዳ ግምት ውስጥ በማስገባት በጥቅምት ወር 1996 ዓ.ም በሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ ብሔራዊ ፔትሮሊየም ወደ ዘርፉ በመግባት ከፍተኛ እድገት እንዳመጣ ገልፀው ለመስራቾቹ፣ ለባለአክሲዮኖችና ለድርጅቱ ሰራተኞች ለዚህ በመብቃታችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ ብለዋል፡፡ ድርጅቱ የ10ኛ ዓመት ምስረታውን አስመልክቶ ባዘጋጀው በዓል የተለያዩ አስተዋፅኦዎች ላበረከቱ ወገኖችና ሠራተኞች ሽልማት አበርክቷል፡፡ ለዋና መስሪያ ቤትነት የሚገነባው ህንፃም በሁለት ዓመት ተጠናቅቆ ስራ እንደሚጀምር ሥራ አስኪያጁ ገልፀዋል፡፡

# "ህፃናትና ገና" የመዝናኛ ፕሮግራም የገና ዕለት ይካሄዳል

ናፍቆት ዮሴፍ

ኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ሰርቪስ (ኢቢኤስ) ቴሌቪዥንና አብርሃም ግዛው ኢንተርቴይንመንትና የፕሬስ ስራዎች ኃ/የተ/የግል ማህበር በመተባበር "ህፃናትና ገና" የተሰኘ የህፃናት መዝናኛ ፕሮግራም በገና በዓል እለት እንደሚያቀርቡ ገለፁ፡፡ በዛሬው እለት "በኤስ ኦ ኤስ" ህፃናት መንደር ቀረፃው እንደሚካሄድ የገለፁት አዘጋጆቹ፤ ባህላዊ ስፖርቶቻችንን በሚያስታውሱት የገና ጨዋታና የገበጣ ጨዋታ ህፃናት እንደሚሳተፉ ጠቁመዋል፡፡ በህፃናት አስተዳደግና እንክብካቤ ዙሪያ መልካም ተሞክሮና ልምድ ያላቸው ወላጅና አሳዳጊዎችም ልምዳቸውን ለታዳሚው እንደሚያካፍሉ ተገልጿል፡፡

የማንበብ ልምድን ለማሳደግ ታስቦ የተዘጋጀ የህፃናት የንባብና የልዩ ተሰጥኦ ውድድር እንዲሁም ልዩ ልዩ ገናን የሚዘክሩ ወጐች የመዝናኛ ፕሮግራሙ አካል እንደሆኑ የተገለፀ ሲሆን፤ ለአሸናፊዎችም ሽልማት ይበረከታል ተብሏል፡፡ በተለያዩ ትልልቅ ሃይማኖታዊና ብሔራዊ በዓላት ላይ ህፃናት ትኩረት ተሰጥቷቸው የራሳቸው ፕሮግራም ሲዘጋጅላቸው አይስተዋልም ያለው ጋዜጠኛ አብርሃም ግዛው፤ "ህፃናትና ገና" የመዝናኛ ፕሮግራም ግን ህፃናት ላይ አተኩሮ የተዘጋጀና ህፃናት የገና በዓል አከባበርን ጠንቅቀው እንዲያውቁና የራሳቸው የበዓል መዝናኛ እንዲሆንላቸው ታስቦ መዘጋጀቱን ገልጿል፡፡

በእለቱ የሴቶች ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰን ጨምሮ ሌሎች የመንግስት ሃላፊዎች፣ የፕሮግራሙ ተሳታፊ ህፃናት ወላጆች፣ የኪነጥበብ ሰዎችና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በበዓሉ ላይ ይታደማሉ ተብሎ እንደሚጠበቅ አዘጋጆቹ ለአዲስ አድማስ ገልፀዋል፡፡

# ቢጂአይ ኢትዮጵያ የወይንና የቢራ ፋብሪካዎችን አስጎበኘ

## "ቢራ ሃንግኦቨር የሚፈጥረው ፈርሜንቴሽኑን ካልጨረሰ ነው"

መንግሥቱ አበበ

ባለፈው ሳምንት ቅዳሜ ከየሚዲያው የተውጣጡ ጋዜጠኞች፣ የአዲስ አበባ የጤና ቡድን አመራሮችና ሌሎች እንግዶች ቢጂአይ ኢትዮጵያ ባደረገላቸው ግብዣ መሰረት፣ የዝዋይን የወይን ጠጅ እርሻና ፋብሪካ እንዲሁም የሀዋሳን የቢራ ፋብሪካ ጎብኝተው ነበር፡፡ እኔም ከጐብኚዎቹ አንዱ ነበርኩ፡፡በመጀመሪያ የጎበኘነው ዝዋይ የወይን እርሻና ፋብሪካ ነው፡፡ ወይን የሚመረተው በዓመት አንዴ ስለሆነ ጠመቃውም አንድ ጊዜ ነው፡፡ የዕለት ተዕለት የሥራ ሂደት ያለው ቢራው ስለሆነ በዚያ ላይ አተኩራለሁ፡፡ እናንተ! ይኼ በየመጠጥ ቤቱ የምንጠጣው ድራፍትና ቢራ በርካታ ሂደቶች አልፎ ነው ለካ የሚቀርብልን፡፡ ውሃው በተለያዩ ኬሚካላዊ ሂደት ውስጥ አልፎና ተጣርቶ፣ መጥመቂያ ጋኖቹም በኬሚካሎች ታጥበው፣ ንፁህ መሆናቸው በላብራቶሪ ፍተሻ ተረጋግጦ ነው ቢራ ጠመቃው የሚጀመረው፡፡

ለቢራ ምርት የሚያስፈልጉት አራት ነገሮች ውሃ፣ የቢራ ገብስ (ብቅል) ጌሾና እርሾ ናቸው፡፡ የትኛውም የቢራ ፋብሪካ የሚያስፈልጉት ዋነኛ ንጥረ ነገሮች እነዚህ ናቸው፡፡ ልዩነት የሚፈጠረው በአቀማመም ሂደት ነው፡፡ የቢራ ጠመቃ የሚጀመረው ገብሱን (ብቅሉን) በመፍጨት ነው፡፡

የሃዋሳው ቢጂአይ ቢራ ፋብሪካ ለአንድ ጊዜ ጠመቃ 5,950 ኪሎ የገብስ ብቅል እንደሚፈጭ የፋብሪካው የፕሮዳክሽን ቺፍ ሊደር አቶ ደገፋው ማዘንጊያ ገልፀዋል፡፡ ወፍጮው አውቶማቲክ ስለሆነ ገብሱን ራሱ በማበጠር ጠጣር ነገሮችን (አፈር፣ ብረት...) እንዲሁም ገለባ ይለያል፡፡ ከዚያም ዱቄቱ በ13.500 ሊትር ይቦካና በተለያዩ የሙቀት ደረጃዎች እንዲቆይ ይደረጋል፡፡ የቢራ ጥራት የሚወሰነው፤ በገብሱ ሽርክትና መጠን እንደሆነ አቶ ደገፋው ይናገራሉ፡፡ ፋብሪካው 12 ጋኖች ሲኖሩት እያንዳንዱ ታንክ 200ሺ ሊትር ሃይ ግራቪቲ ቢራ እንደሚይዝ፣ ፈርሜንቴሽን (ማብላያ) ጋን ውስጥ ከ15-20 ቀን እየተብላላ እንደሚቆይ፣ በመጀመሪያው ፈርሜንቴሽን ለ7 ቀናት በ12 ዲግሪ ሙቀት፣ በሁለተኛው በ16 ዲግሪ ሙቀት ለ72 ሰዓታት እንደሚቆይና ከሦስት ቀናት በኋላ ተጣርቶ ለገበያ እንደሚቀርብ ሃላፊው አስረድተዋል፡፡

የድራፍትና ቢራ የአመራረት ሂደት አንድ ነው ያሉት ኃላፊው፤ ልዩነት የሚመጣው በፓስቸራይዜሽን ሲስተሙ፣ በመያዣ ዕቃ (ፓኬጂንግ) በርሜልና ጠርሙስ መሆንና በካርቦንዳይ አክሳይድ ይዘት እንደሆነ ገልጿል፡፡ ድራፍት የሚቀቀለው (ፓስቸራይዝ የሚደረገው) በ94 ዲግሪ ሴንቲግሬድ ሲሆን ቢራ ደግሞ በ62 ዲግሪ ረዘም ላለ ጊዜ ነው፡፡ ድራፍትም ሆነ ቢራ የሚቀቀሉት (ፓስቸራይዝድ የሚደረጉት) ሳይበላሹ የመቆያ ጊዜያቸውን ለማራዘም እንደሆነ የጠቀሱት ሺፍ ኃላፊው፤ ፓስቸራይዝድ የተደረገ ቢራ ሳይበላሽ ለአንድ ዓመት፣ ድራፍት ደግሞ ለአንድ ወር ይቆያሉ ብለዋል፡፡

የቢራ ሃንግኦቨር (በማግስቱ ራስ ምታት) የሚፈጠረው በፈርሜንቴሽን ጊዜ ቆይታ ማነስ ወይም መብዛት እንደሆነና ጊዜውን በመቆጣጠር ማስቀረት እንደሚቻል አቶ ደገፋው አስረድተዋል፡፡ ለምሳሌ ቢራው ውስጥ ብዙ ጉሉኮስ (ስኳር) እያለ የፈርሜንቴሽኑ ጊዜ አጭር ከሆነ (በደንብ ካልተብላላ) ከፍተኛ አልኮሎች ይመረቱና ቢራው ሲጠጣ ራስ ምታት ያመጣል፡፡ ፈርሜንቴሽን በጣም እንዲዘገይም ሆነ እንዲፈጥን አይደረግም፡፡ ከገበያ አኳያ እንዲዘገይ፣ ከጥራት አኳያ እንዲፈጥን ማድረግ ጥሩ አይደለም፡፡ ሲዘገይም ሆነ ሲፈጥን የሚፈጠር ነገር (ያልተፈለገ ምርት) አለ፡፡ ያ ነው ራስ ምታት የሚፈጥረው በማለት አስረድተዋል፡፡

ሴላር የሚባለው ፈርሜንቴሽኑን ያልጨረሰና የሚፈለገውን የጥራት ደረጃ ያልያዘ በጣም ወፍራም ቢራ ነው ይላሉ - አቶ ደገፋው፡፡ የአልኮል መጠኑ ከፍተኛ፣ እንዲሁም በጣም ወፍራምና ያልተጣራ ስለሆነ ገበያ ላይ ቢወጣ ብዙ ሰው አይጠጣውም፡፡ ስለዚህ አልኮሉ እንዲቀንስ (ዳሊዩት) ይደረጋል፤ ይጣራና ተገቢውን የውፍረት መጠን ይዞ ወደ ገበያ ይወጣል ብለዋል፡፡

ሴላር መጠጣት ወይም አለመጠጣት የደንበኛው ፍላጎት ነው፡፡ ነገር ግን ሴላር ገበያ ሲወጣ ከቢራ እኩል አይሸጥም፤ ዋጋው ወደድ ይላል፡፡ ፓስቸራይዝድ ስላልሆነ ለጤናማም ጥሩ አይደለም፡፡ ሴላር ወዲያው ካልተጠጣና ሁለት ሦስት ቀን ከቆየ ይበላሻል፡፡ ስለዚህ ሴላር መጠጣት ካለበት ፋብሪካው አካባቢ፣ የሚጓጓዝበትም መኪና ማቀዝቀዣ ያለው መሆን አለበት በማለት አቶ ደገፋው ማዘንጊያ አብራርተዋል፡፡


# የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ

## ለትሩዌይ ካፒታል ሰርቪስ አ.ማ ባለአክሲዮኖች በሙሉ

የትሩዋይ ካፒታል ሰርቪስ አ.ማ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ታህሳስ 12 ቀን 2007 ዓ.ም ሲኤምሲ መንገድ በማገኘው የወረዳ 8 ወጣቶች ማዕከል ከጧቱ 2፡30 ጀምሮ እንደሚካሄድ ጥሪ ማስተላለፉ ይታወቃል፡፡

ሁኖም በመላ ሀገሪቱ የምርጫ አስፈጻሚዎች ምርጫ በዕለቱ እንደሚካሄድና የስብሰባ አዳራሾች በዚሁ ምክንያት እንደሚያዙ በስብሰባው ዋዜማ ስለገለጽን፤ የስብሰባ ቀኑን መለወጥ አስፈላጊ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ከላይ በተጠቀሰው ቦታና ሰዓት ታህሳስ 26 ቀን 2007 ዓ.ም ባለክሲዮኖች እንዲገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

**የዳይሬክተሮች ቦርድ**

# አቶ ተስፋዬ ተሾመ አዳል

**የአንደኛ ሙት ዓመት መታሰቢያ**



*ተሰፍሽ፤*
*ከተለየሽን ዓመት ሞላው፤*
*ጊዜው ይሄዳል፤ ፈገግታህ ብቻ ነው*
*ትዝታ ሆኖ የቀረው፡፡*

ፀጋዬ ከምሲና
ቤተሰቡ


ሸንጎ ከገፅ 14 የዞረ

አስመሰለው። እብዷ ወዲያው ወደ ቀልቧ ተሰብስባ፣ ግቷን ለጨቅላው ስታቀብልና ጩኸቱ ሲረግብ አንድ ሆነ።

ምሁሩ እብድ የሴትየዋን ተሳልቆ በጥሞና ተከታትሎታል።

“We need to revolutionize our thinking behavior” አለ በሚታወቅበት የእንግሊዘኛ ችሎታው። እብዶቹ በሙሉ የተናገረውን ወደ ሀበሻ አፍ እንዲለውጥላቸው በአንድ ላይ ተንጫጩበት፤ ግድ አልሰጠውም.....ጉራማይሌ እያደረገ ንግግሩን ቀጠለ፤

“ቆይ እናንተን ከእብድ ማህበረሰብ ጋር እንድትቀላቀሉ የፈቀዳለችሁ ማን ነው? የእኛ ትውልድ እብድ መለመላውን ሆኖ በእንግሊዝ አፍ እየተቀኘ የሚንጎራደድ...ወደል ነበር፤ ትንሽ እንደተጓዘ በጤነኞች አጀብ ይደረግለታል። It was so majestic............፡፡

የእናንተ አጀብ የገዛ ጥላችሁ ነው። ቆይ እኔ የምለው ወይ በእንግሊዝ አፍ አትቀኙ፣ ወይ በሀበሻ አፍ አትቀኙ። ሁለመናችሁ የተሸበበ ልጉም ፍጡሮች! እኔ የማዝነው ያ ወርቃማ የእብድ ማህበረሰብ አልቆ እኔ ብቻ በመቅረቴ ነው። ትውልዳችንን ከመጥፋት የሚታደገው ማን ነው? በቃ የእብድ ማህበረሰብ ማለት ይህ ነው?” ስቅስቅ እያለ ማንባት ጀመረ፡፡ የእርሱን ሀዘን የተጋሩ ሌሎች እብዶች አብረውት ተነፋረቁ፡፡

አፈጉባኤው ጸጥታ ለማስጠበቅ የጫት ገረወይናውን አንስቶ ሊደበድብ እጁን ሰደደ። ገረወይናው የለም። ዞር ሲል ወይጦ ከሚባለው እብድ ጋር አይን ለአይን ተላተመ፡፡ ገረወይናው የወይጦ ካራ ሲሳይ ሆኗል። ብሽቀቱን ለመሸሸግ እየሞከረ ካጠገቡ ተንጋላ በተቀመጠችው ቁራጭ የሀይላንድ እቃ ጉብታውን መሬት ልቡ እስኪጠፋ እየደጋገመ ደበደበው።

“ጸጥታ! ጸጥታ! ለመነፋረቅ አይደለም የተሰበሰብነው። መላ ልናወጣ ልናወርድ እንጂ። ጸጥታ.......ጸጥታ!” ሀይላንዱ እስከትነደል ድረስ ጉብታውን መቀጥቀጡን አላቆመም። እብዶቹ አፈጉባኤውን ብዙ ሳይንገራግሩት ቀና ምላሽ ሰጡት።

ቃለጉባኤ እንዲይዝ የታዘዘው እብድ የጨበጠው ብዕር አልፅፍ ስላለው ቅዝዝ እንዳለ በቀፎው መሬቱን ይቆረቁራል። ድንገት መሬት መቁርቆርን ገታ አደረገና እምር ብሎ ተነሳ። ሽቅብ ወደ ሰማይ አንጋጠጠ። ሁሉም እብድ በአይኑ ተከተለው። እብዱ አይኑን ከአንድ ነገር ጋር እየተከተለ ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ ያንከራትታል። አይኑ የሚንከራተተው በአካባቢው ቅኝት በሚያደርግ አሞራ ላይ ነው። አሞራው ያንዣብባል። አንዴ ቁልቁል እንደ ሚግ አውሮፕላን ክንፉን ጨምቆ ይወረወርና ይመለሳል፤ በድጋሚ ክንፉን ጨምቆ ይወረወራል። ምንም የለም። ይመለሳል። መወርወር መመለስ። መወርወር መመለስ። ለሀምሳ ጊዜ ተመላለሰ። በሀምሳኛው ላይ አንዲት ግልገል አይጠ መጎጥ በጥፍሩ ጨምድዶ፣ በአሸናፊነት አየሩን እየገመሰ ከአይን ተሰወረ።

ሁሉም እብድ ትእይንቱን ከጅምሩ አንስቶ ነፍዞ እየተከታተለው ነበር።

“አሁን ከእዚህ ትዕይንት ለእብድ ማህበረሰብ ምን የሚፈይድ ነገር ተማርን?” አለ ቃለጉባኤ ፀሐፊው፡፡“እብድና ብኩን አሞራ አንድ ናቸው። አሞራውስ ሀምሳ ጊዜ ተንከራቶ አንድ አግኝቷል፤ እብድ ግን ለእዚህ አልታደለም። ሀምሳ ጊዜ ተመኝቶ ሀምሳውንም የሚያጣ፤ ሀምሳ ጊዜ ጠይቆ ሀምሳ ጊዜ የሚነፈግ፤ ሀምሳ ጊዜ አንብቶ አንድ ጊዜም የማይፈግግ ብኩን አሞራ ነው፤ ስለዚህ ቢያንስ ከእዚህ አሞራ እንማር፤ ሀምሳ ጊዜ ለፍተን አንድ እንቃርም፤”

“ምንድን ነው የምንቃርመው?” አለ አፈጉባኤው ድንገት አቋርጦት

“እብደታችንን ነዋ፤ እውነተኛ እብድ እንሁን፤ እስካሁን እብድ ለመሆን ተንከራተናል፤ በእርግጥ ቆሽሸናል፤ አዳፋ ተከናንበናል፤ ከገንዳ ውስጥ ፍርፋሪ እየለቀምን እድሜያችንን ቀጥለናል፤ ግን አሁንም ከትክክለኛው እብደታችን ጋር በአይነ ስጋ አልተያየንም። እውነተኛው እብደታችን ከእቅፋችን ውስጥ የሚገባው እንዲህ በረባው ባልረባው ብርክ የሚይዘው ልባችን መጀገን ሲጀምር ነው።።

እስቲ የትኛው እብድ ነው ጤነኞች የሚወረውሩበትን ፍላጻ ለመመከት ደረቱን በጀግንነት ገልብጦ የሚሰጠው፤ የትኛው እብድ ነው እጁን ወደ የሚንቀለቀል እሳት የሚልከው፤ የትኛው እብድ ነው አንድዬ ብርቅዬ ህይወቱን እየሳቀ የሚሸኘው ፤ አያችሁ እኛ እብዶች አይደለንም፤ ምስኪን ጤነኞች እንጂ፤ ምስኪን ጤነኛ ደግሞ ከእብድ እግር ጋር አይተካከልም? እንዴት ይተካከላል...” ጠየቀ ተሰብሳቢውን፡፡የጉባኤውን መንፈስ ለማረጋጋት ሌላ እብድ ከተቀመጠበት ተነሳ። በመስተፋቅር ካበደው የፓርላማው ወገን ነው። አናቱ ላይ ብጭቅጫቂ ዳንቴል አጥልቋል፤ አንገቱ ላይ ሻሽ ጠምጥሟል፤ የደረቱን እኩሌታ በእሳት በተበላ ጡት መያዣ ሸፍኖታል፤ ሚጢጢዬ ጠጠር ድንጋይን እንደ ከሬን እየተጎተተ ከመሬት በማንሳት በጩኸት መናገሩን ቀጠለ፤ “ለምንድን ነው ግን ወደ ራሳችን የማንመለከተው፤ ድሮ ድሮ እብድ ሲባል የጠገበ ዱላ ይዞ የሚንጎራደድ ወጠምሻ ነበር፤ የእብድ ስም ሲነሳ የማይሸበር ጤነኛ አልነበረም፤ እንደውም እስከነተረቱ....“እብድ የተናገረው መሬት አያርፍም” ይባላል፡፡

ፍልስፍናው ዝብርቅርቅ፣ ወሬው የጤነኞችን የማሰብ አቅም የሚፈታተን ነበር፤ ዛሬስ? ዛሬማ ተንቀናል፤ እስቲ ተመልከቱን .....ለአይን የሚያጠግብ እብድ ከእዚህ ውስጥ ይፈለግ ቢባል አይገኝም፤ በአካልም በመንፈስም ደቀናል። አንደበታችን ዲዳ፤ አካላችን ለንቋሳ ሆኗል። እጃችን በዱላ ፋንታ የተጣለ ሀይላንድ መለቃቀም ከጀመረ ሰነባብቷል።

ፍልስፍናችን በዝምታ ተቀይሯል። የድሮ እብደታችንን ማምጣት ለነገ የምንለው ስራ መሆን የለበትም።”ቀኝ እጁን ወደ ላይ እየሰቀለ መፈክር ማሰማት ጀመረ፤ “እብደታችን እንደ ድሮ ይሆናል! እብደታችን እንደ ድሮ ይሆናል!” አስደንጋጭ መፈክር ከሞቀ ጭብጨባ ጋር አጀበው። ጭብጨባውን ሰምቶ ይሁን ድንገት... ስጋ የጠገበ መለዮ ለባሽ ዱላውን አክሮባት እያሰራ ከርቀት ወደ ስብሰባው ሲመጣ ታየ፡፡ ሁሉም ተሰብሳቢ በፍርሀት ልቡ ይርድ ጀመረ።

አፈጉባኤው በእዚህ ጊዜ፤

“አንድ ጊዜ ......አንድ ጊዜ፤ አሁን ጤነኛውን ከእብድ፣ ፍሬውን ከገለባ መለየት ቻለናል፡፡ በአንድ መለዮ ለባሽ እንዲህ የሚርድ ልብ ካለን፣ ጤነኛ የመሆናችን ፋይዳው ምኑ ላይ ነው። ...ኸረ.. እብደት በስንት ጣዕሙ..... በሉ ወደ የሚያዋጣን እብደታችን እንመለስ” ብሎ በንዴት ስብሰባውን በተነው።

ግጥሞች ከገፅ 8 የዞረ

“የማንነት ጥያቄ” ቀውስ ቀላል አልነበረም፡፡ ያም ሆኖ ግን በአንድ በኩል በልቶ ህይወቱን ለማቆየት ከነበረው ተስፋና ጉጉት፣ በሌላም በኩል በመንግስት ተፅእኖ የኖረበትን መሬት ለቅቆ ወደተባለው ቦታ ሄዶ ሠፍሮአል፡፡ ሠፈራው ያሳደረበትንም ከቀዬው የመነጠል መሪር ስሜት በቃል ግጥሞች ገልጾአል፡፡ እንዲህ እያለ:-

*የኮምሽን ስንዴ ጣዕሙ ጥሩ ነበር*
*ውለው እያደሩ ስፈሩ ባልነበር!*

ግጥሙ ምንም እንኳን በወቅቱ በመንግስት ለማህበረሰቡ ይታደል ስለነበረው “የኮሚሽን ስንዴ” የሚናገር ቢመስልም ጉዳዩ ሠፈራው ነው፡፡ ማህበረሰቡ በየጊዜው ያላችሁበትን ለቅቃችሁ ወደ ሌላ ቦታ *“ሥፈሩ”* በመባሉ የነበረውን ተቃውሞ ግጥሙ በሚገባ ያሳያል፡፡ ሆኖም በወቅቱ ይህንን ተቃውሞውን በግልጽ ለመናገር የማይችል በመሆኑ (አሁን ይችላል አላልኩም!) ቃላዊ ሀብቱን ተጠቅሞ፣ ስለ ስንዴ ያወራ በመምሰል በሠፈራው ላይ ያለውን ተቃውሞ ገልጾአል፡፡

*ምንድን ነው ሠፈራ ዶሮ ይመስል*
*ላከኝ ከጦር ሜዳ ከወንዶች ሰፈር*

ይህ ደግሞ ከቀደመው ቃል ግጥም በከረረ መልኩ ማህበረሰቡ ለሠፈራው የነበረውን ተቃውሞ የገለጸበት ነው፡፡

በግጥሙ የመጀመሪያ መስመር ላይ “ሠፈራ” ለዶሮ እንጂ ለሰው እንዳልሆነ/ እንደማይሆን ያስረግጣል፡፡ ይህም “እኛ ሰዎች ሆነን ሳለ የዶሮ ያህል አሳንሰው እያሠፈሩን ነው” ወደሚል ትርጉም ያደርሰናል፡፡ ይህንን ልብ ብለን ወደ ሁለተኛው የግጥሙ መስመር ስናልፍ ግን የምናገኘው መልዕክት ከዚህም የመረረና የጠነከረ ነው፡፡ ማህበረሰቡ በግጥሙ መንግስትን “ከሰው አሳንሰህ እንደ ዶሮ ከምታሠፍረኝ ወደ ጦር ሜዳ ላከኝ” ብሎአል፡፡ በጦር ሜዳ ሞት አለ፡፡ ሆኖም እንደ ዶሮ ከመኖር ጦር ሜዳ ሄዶ መሞትን መርጦአል፡፡... ይህንን እዚህ ላይ ገተን በዘመኑ በነበረው የማያቋርጥ ጦርነት ላይ ወደተነገረው እንለፍ፡፡

የደርግ ዘመን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ጊዜያት ከጦርነት የፀዳ ነበር ማለት ማበል ነው፡፡ በቀዳሚዎቹ የአገዛዙ ዓመታት ከሶማሊያ መንግስት ጋር ከባድና ብዙ ጉዳት ያደረሰ ጦርነትን አድርጎአል፡፡ እንዲሁም ከኤርትራ ነጻ አውጪ ግንባሮችና ከወያኔ ሠራዊት ጋር የስልጣን ዘመኑ እስከሚያበቃበት የመጨረሻዎቹ ወቅቶች ድረስ ተዋግቶአል፡፡

በእነዚህ ጦርነቶችም በርካታ ዜጎች ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡ ጦርነቱ በርካታ ዓመታትን ያስቆጠረ በመሆኑም የደርግ መንግስት በተለይ በመጨረሻዎቹ ዓመታት “ብሔራዊ ውትድርና” በሚል ብዙ ወጣቶችን “አፍሶ” ወደ ጦር ግንባሮች ልኳል፡፡

ይህ ሁኔታ ልጁን ለተነጠቀው ማህበረሰብ እጅግ መራር ሀዘንን የፈጠረ በመሆኑ ሌላ ጊዜ እንደሚያደርገው ሁሉ ስሜቱን በቃል ግጥም አውስቷል፡፡ ጦርነቱ ላይ የተነገረን አንድ ቃል ግጥም እንጥራ፡፡*እንዴት ያል ዘመን ነው የዘመን ቆረንጮ*

*ወልዶ ለጦርነት ሰርቶ ለመዋጮ*

በግጥሙ የመጀመሪያ መስመር ላይ ማህበረሰቡ ሆኖና ተደርጎ የማያውቅ ነገር በዘመኑ በመፈጸሙ ይህንን ሲወቅስ እንመለከታለን፡፡ በሁለተኛው መስመር ላይ በሚገኙት ሁለት ሐረጎች የምናገኘው መልዕክት ግን ሁለት ነው፡፡

ማህበረሰቡ የወለደውን ልጅ ጦርነቱ እየነጠቀው በመሆኑ ተስፋ ቆርጦአል፡፡ ሰው የሚወልደው ለጦርነት አይደለም፡፡ ለብዙ ሰዋዊ ዓላማዎች ነው፡፡

ሆኖም ግን በወቅቱ ለነበረው ማህበረሰብ መውለድ ለጦርነት ሆኖ ተሰምቶታል፡፡ በመሆኑም “ምናባቱ ባልወልድስ” እስከማለት አድርሶታል፡፡

ሁለተኛው ሐረግ ደግሞ ማህበረሰቡ ለመስራትም ልቡ እንደሰነፈና ተስፋ እንደቆረጠ ያሳያል፡፡ በዘመኑ ማህበረሰቡ “ለእናት ሀገር” በሚል መዋጮ እንዲያዋጣ ይደረግ ነበር፡፡ በመሆኑም “ባልሰራስ፣ ቢቀርስ” በሚል ተስፋ ቆርጦአል፡፡

በሀገራችን በዘመነ ደርግ ስርዓቱ ላይ የተነገሩትን የተቃውሞ ቃል ግጥሞች አነሳሁ እንጂ በየዘመናቱና ስርዓቱ በተለያዩ ቋንቋዎች ሥፍር ቁጥር የሌላቸው ቃል ግጥሞች ተነግረዋል፡፡ አሁንም ይነገራሉ! እነዚህ ቃል ግጥሞች ማህበረሰቡ ለየዘመኑና በዘመኑ ለነበረው ስርዓት የነበረውን ሁሉን አቀፍ ስሜትና ምላሽ የያዙ በመሆናቸው ዘመኑንና የወቅቱን ማህበረሰብ ስነልቡና የሚያሳዩ ህያው ምስክር ናቸው፡፡

ይህንን እየከተብኩ እንዲህ አሰብኩ፡፡ በዘመነ ኢህአዴግ እየተነገሩ ያሉ ቃል ግጥሞችስ ምን ይመስሉ ይሆን? በዘመናችን ቃል ግጥምን ሊያስነግሩ የሚችሉ በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡

በርካታ! ስራ አጥነት፣ መልሶ ግንባታ፣ ውሃ ማቆር፣ የኑሮ ውድነት፣ ስደት፣ ምርጫና የፖለቲካ ውዝግብ... ሌሎችም ብዙ! ታዲያ ማህበረሰቡ ለእነዚህ ጉዳዮችና በአጠቃላይ ለአገዛዙ ያለውን ምላሽ በቃል ግጥሙ እንዴት ገልጾ ይሆን? ጊዜና አጋጣሚ ቢፈቅድ ሌላ ጊዜ እመለስባቸዋለሁ፡፡

መልካም ሰንበት!!

www.
addisadmassnews.com
ይጎብኙን

# እንኳን ለብርሃነ ልደቱ በጤና እና በሰላም አደረስዎ

ከውጭ ሀገራት የሚላክልዎትን ገንዘብ ወዲያውኑ ለመቀበል አሁን በርካታ አማራጮች አሉልዎት። ከ20 በላይ ከሆኑ ታዋቂ ዓለም አቀፍ የገንዘብ አስተላላፊ ድርጅቶች ጋር እንሠራለን። በመላ ሀገሪቱ ካሉን 900 ቅርንጫፎች ከቀረብዎት ቅርንጫፍ ገንዘበዎን ያላንዳች ውጣውረድ በቀላሉ መውሰድ ይችላሉ።

ሌላም አስተማማኝና ፈጣን አማራጭ አለልዎ:- በባንካችን የስዊፍት አድራሻ (SWIFT CODE):CBETETAA በኩል ገንዘብ ቢላክልዎ ወደተላከልዎ ቅርንጫፍ በመሄድ ያላንዳች የአገልግሎት ክፍያ ገንዘብዎን በፍጥነት ይቀበላሉ።

## መልካም የገና በዓል ይሁንልዎ!

**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ**

**ሁሌም የሚተማመኑበት ባንክ!**

ደርባ ሲሚንቶ
DERBA CEMENT



# ክቡራትና ክቡራን ደንበኞቻችን!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ላለፉት ጥቂት ወራት በጥገናና እድሳት ላይ ቆይቶ ሥራውን በማጠናቀቅ ወደ ሙሉ ምርታማነቱ ተመልሷል፡፡

የሲሚንቶን ዋጋ በማረጋጋት የሚታወቀው ፋብሪካችሁ እንደተለመደው ከፍ ያለ ጥራት ያላቸውን OPC እና PPC ሲሚንቶ በተለየ አደረጃጀት እደጃፋችሁ ድረስ ማድረሱን ከህዳር 29 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ የተለመደውን አገልግሎት በመስጠት ይጀምራል፡፡

በዚህ አጋጣሚ በእድሳትና ጥገና ወቅት አብራችሁን ለቆያችሁት ደንበኞቻችን ወደር ለሌለው ትዕግሥታችሁ የደርባ ማኔጅመንትና ሠራተኞቹ ከፍ ያለና የከበረ ምስጋናቸውን ለእናንተ ለደንበኞቻቸው ያቀርባሉ!!

"ለሁሉም ሥራ በሁሉም ሥፍራ ነገን ዛሬ እንስራ"
"ደርባ ሲሚንቶ"

## ላንቺና ላንተ

# "...ልጆችን በተገቢው መንገድ ማስተማር..."

ፀሐይ ተፈረደኝ ከኢሶግ

"...በሴቶች ላይ የሚፈጸመው የአስገድዶ መድፈር ጥቃት በአብዛኛው ቅርብ በሆኑ ወይንም በሚታወቁና እምነት በተጣለባቸው ወንዶች አማካኝነት ነው፡፡ ይህም በስነተዋልዶ ጤና በኩል በከፍተኛ ሁኔታ የጤናን ችግር ከሚያስከትሉና የሴቶችን የሰብአዊ መብት ከሚገፉ ድርጊቶች የተመደበ ነው፡፡" - WHO

ከላይ ያነበባችሁት እውነታ በመላው አለም ከግምት ውስጥ የገባና ሀገራት ችግሩን ለመቅረፍ ያላሰለሰ ጥረት ሲያደርጉ የሚስተዋልበት ነው፡፡ የአለም የጤና ድርጅት መረጃውን በማከልም የሚከተሉትን ነጥቦች ለንባብ ብሎአል፡፡

በቅርብ በአለም ላይ የተገኘው መረጃ እንደሚገልጸው፡-

በአለም አቀፍ ደረጃ 35% የሚሆኑ ሴቶች በሕይወት ዘመናቸው በሚያውቁትም ይሁን በማያውቁት ሰው የወሲብ ጥቃት ተፈጽሞባቸዋል፡፡

- ከእነዚህም ውስጥ በአማካኝ 30% የሚሆኑት ሴቶች በቅርባቸው ካለ ወይንም አብሮአቸው በሚኖር ሰው ድርጊቱ እንደተፈጸመባቸው መስክረዋል፡፡
- በአለም 38% የሚሆኑ ሴቶች ሕይወት የጠፋውም በሚያውቁዋቸው ወይንም በኑሮ ተጋሪዎቻቸው መሆኑን የአለም የጤና ድርጅት ይመሰክራል፡፡
- በሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት በአካል፣ በአእምሮ፣ በወሲብ የሚፈጸም ሲሆን ይህም ለስነተዋልዶ ጤና ወይንም ሌላ ተያያዥ ለሆኑ የጤና እክሎች (ኤችአይቪ) ሊያጋልጥ ይችላል፡፡
- በሴቶች ላይ የወሲብ ጥቃቱን የሚፈጽሙት ወንዶች ምናልባትም ዝቅተኛ ትምህርት ያላቸው ወይንም በቤተሰቦቻቸው ዘንድ ለሕጻናት በቂ ትኩረት ወይንም እንክብካቤ ሲደረግ ማየት ያልቻሉ ወይንም በቤተሰብ ዘንድ ጥቃት ሲፈጸም፣ ጎጂ የሆኑ አልኮሆል የመውሰድ ልምድ፣ የስርአተ ጾታ ክፍፍል ሲደረግ መመልከት፣ የሴቶች እኩልነት ዝቅ ማለትን እያዩ ያደጉ ሊሆኑ እንደሚችሉ ዘገባው ያስረዳል፡፡

ባለፈው ሳምንት እትም የኢትዮጵያ የጽንስና ማህጸን ሐኪሞች ማህበር በመቀሌ ከተማ ሐይደር ሆስፒታል ያቋቋመውን ተገደው የተደፈሩ ሴቶች የሚታከሙበትን ሞዴል ክሊኒክ በንባብ ማስጎብኘታችን ይታወሳል፡፡ በዚያም ያገኘናቸውን ባለጉዳዮች ማብራሪያ አቅርበን ለዚህ እትም ቀጣይ እንደሚኖረው ገልጸናል፡፡ በመግቢያው ላይ "...መምህርማ አባት ወይንም እናት..." የሚለውን ርእስ የተጠቀምነውም ምክንያት ስላለው ነው፡፡ ለዚህ እትም ማብራሪያ ያገኘነው በሞዴል ክሊኒኩ ከምትሰራው ከሲ/ር አበባ ከበደ ነው፡፡

በመቀሌ የተከሰተ አንድ ታሪክ እናስነብባችሁ፡-

ሰውየው በመቀሌ ከተማ በሚገኝ አንድ ትምህርት ቤት አስተማሪ ነው፡፡ ከሚያስተምራቸው ተማሪዎች መካከል የተወሰኑትን ጥናት አስጠናችሁዋለሁ በማለት በየቀኑ በተራ በተራ ከእርሱ ጋር እንዲቆዩ ያደርጋል፡፡ የመምህሩ አላማም ሕጻናቱን ማስተማር ሳይሆን አስገድዶ መድፈር ነበር፡፡ ድርጊቱን ከፈጸመ በሁዋላም ልጆቹ ለማንም ይህንን ታሪክ እንዳይ ናገሩ ...ከተናገሩም ጉዳት እንደሚያደርስባቸው እያስጠነቀቀ ነበር የሚለቃቸው፡፡ በስተመጨረሻውም ከእርሱ ጋር ለመቆየት ተረኛ የነበረች በእድሜዋ ወደ አስራ ሁለት አመት የሚሆናትን ሕጻን በፊንጢጣዋ ጭምር ስለደፈራት ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ ይሆናል፡፡ ሕጻኑዋ እንደተለመደውም በማስጠንቀቂያ ቢለቃትም ...እርስዋ ልትደብቀው የማትችለው በመሆኑ ሰውየው ይጋለጣል፡፡ የህጻኑዋ ቤተሰቦች ልጅቱን ወደሐኪምቤት በማድረስ ወደህግ ቦታም ሄደው ጉዳዩን በመከታተል ላይ ናቸው፡፡

"...እዚህ ላይ አንድ የሚያሳዝን ክስተት ተፈጽሞአል፡፡ ሰውየው ሕጻኑዋን ከጥቅም ውጭ አድርጎ በመድፈሩ ምክንያት የልጅቱ ገላ እንዳይሆን ሆኖአል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ...መምህሩ ኤችአይቪ ቫይረስ በደሙ ውስጥ የሚገኝ በመሆኑ ህጻኑዋንም በቫይረሱ እንድትያዝ አድርጎአታል፡፡ መምህሩ ዛሬ በህግ የተያዘ ቢሆንም የህጻኑዋ የወደፊት የህይወት እጣ ፈንታ ግን ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም፡፡ እጅግ ...ያሳዝናል፡፡ መምህርማ በእናትና አባት የሚመሰል አይደለምን? ይህንን ድርጊት ይፈጽማል ብሎ መገመት እጅግ ያስቸግራል፡፡ እንደዚህ ያለው መምህር የሌሎች መልካም ስነምግባር ያላቸውን መምህራን በጎ ተግባር የሚያጠፋ ስለሆነ ተገቢው እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡"ሲስተር አበባ እንደገለጸችው ...ይህች ልጅ ጉዳትዋ ስለከፋ ወደህግና ሕክምና ቀረበች እንጂ ይህ መምህር ጥቃት ያደረሰባቸው ሌሎች ህጻናትም አሉ፡፡ ማንኛውም ቤተሰብ ልጆቹን ግልጽ ውይይት ማስተማር እንዳለበትንና ልጆች ከማንኛውም ሰው የሚሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ ወደጎን በመተው እውነቱን ለወላጆቻቸው መንገር እንዳለባቸው ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሲስተር ሳራ በአይደር ሆስፒታል ያነጋገርናት ባለሙያ ናት፡፡ እሱዋም እንደምትመሰክረው ወላጆችም ይሁኑ ትምህርትቤቶች እንደዚህ ያለውን አስጸያፊ ተግባር ህጻናቱ አስቀድሞውኑ እንዲያውቁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

"...በተለይም ወላጆች በግልጽ ልጆቻቸውን ተገዶ በመደፈር ሁኔታ ላይ የሚያስተምሩ አይመስለኝም፡፡ እንዲሁ በደፈናው ሴት ልጆቻቸውን ለምን በሰአቱ ከትምህርት ቤት አትመጪም ወይንም ለምን ከወንድ ጋር ትሄጃለሽ የመሳሰሉትን ተግባራዊ የማይደረጉትን ቁጣዎች ሊሰነዝሩ ይችላሉ፡፡ ይህ ግን ትክክለኛው የማስተማሪያ መንገድ አይደለም፡፡

ልጆቹ ከትምህርት ቤት መውጫ መግቢያ ሰአታቸውን መጠበቅ የሚገባቸው ለምን ድነው? ምን ችግር እንዳይገጥማቸው ነው?

ሕጻናቱ ከወንድ ጋር አትሂጂ የሚለውን ቁጣ በደፈናው ሊቀበሉት የማይችሉትን መሰንዘር ትክክለኛው መንገድም ስላልሆነ... ከሱ ይልቅ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በተሳሳተ መንገድ በልጆ ላይ ምን ጉዳት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ እና ይህ ግን የሁሉም ወንዶች እና ሴቶች ተግባር እንዳ ልሆነም ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በተለይም ተገዶ መደፈር ምን ማለት እንደሆነና በልጆቹ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት እና የመብታቸውን ሁኔታ በትክክል እንዲያውቁ ማድረግ ከወላጆች፣ ከትምህርት ቤቶች እንዲሁም ከመላው ሕብረተሰብ የሚጠበቅ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡"

ሴቶች የወሲብ ጥቃት ወይንም ትንኮሳ ደርሶባቸዋል ሲባል የግድ የወሲብ ግንኙነት ተደርጎአል ማለት ብቻ አይደለም፡፡ ነገር ግን ወሲብ ለመፈጸም ሙከራ ማድረግ፣ በእጅ ወይንም በአይን በመሳሰሉት ሁሉ የተለያዩ ትንኮሳዎችን ማድረግ፣ በንግግር በመሳሰሉት ሁሉ ሴቶችን መተንኮስ፣ መብትን መጋፋት መሆኑን ከግምት የማያስገቡ አሰራሮች ሴት ልጆችን እየጎዱ መሆኑን ሲ/ር አበባ ገልጻለች፡፡

"...ታካሚዋ የመጣችው መስከረም ወር ላይ ነው፡፡ እድሜዋ አስራ ሁለት አመት ይሆናል፡፡ ልጅቱዋ በአሳዳጊዋ አራት ጊዜ የወሲብ ጥቃት ተፈጽሞባታል፡፡ ያች ልጅ ወደሐኪም ቤት መጥታ ሕክምና ከተደረገላት በሁዋላ የተሰጣት ምስክርነት ክብረ ንጽህናዋ እንዳልተነካ እና የመደፈር ምልክት እንዳልታየባት ነው፡፡ ይህንን ይዛ ወደህግ ቦታ ስትሄድ ግን ልጅትዋ የምትናገረውን ምስክርነት ከምንም ሳይቆጠር ክብረ ንጽህናዋ ስላልተወሰደ ለክስ መሰረት የሚሆን ነገር የለም ከሚል ፋይሉም ተዘግቶአል... ሰውየውም በነጻተለቅቆአል፡፡"

ልጅትዋ በአሳዳጊዋ አራት ጊዜ የወሲብ ጥቃት ከተፈጸመባት እንዴት ክብረንጽህናዋ አልተወሰደም የሚል ጥያቄ በአንባቢዎች ዘንድ የሚጭር ነው፡፡ ሲ/ር አበባ እንደገለጸችው፡-



ሲ/ር አበባ ከበደ

"...የድንግልና ቀለበቱ በተፈጥሮ የተለያየ አፈጣጠር አለው፡፡ አይነቱ አራት አይነት ሲሆን ከዚያ ውስጥ አንደኛው ቅርጽ በራሱ ጊዜ የመለጠጥ ባህርይ ያለው ነው፡፡ ይሄ አይነቱ ሲሆን ከግንኙነት በሁዋላ ተመልሶ ወደቦታው የሚገጥም ነው፡፡ እንደዚህ አይነት ተፈጥሮ ከሆነ የመድማት ወይንም የመቁሰል ምልክት ስለማያሳይ ክብረንጽህና አልተነካም ሊባል ይችላል፡፡ ነገር ግን ልጅትዋ በሰውየው ተደጋጋሚ የወሲብ ጥቃት እንደደረሰባት ከገለጸች እና ሌሎች መረጃዎች ከተሰባሰቡ ሐኪም የክብረንጽህና መወሰድ ምልክት በገላዋ ላይ አይታይም በማለቱ ብቻ መረጃው በሐኪም ካልተረጋገጠ ክስ ለመመስረት አያበቃም በሚል ጥፋተኛውን መልቀቅ በልጅትዋ ሞራልና የወደፊት ሕይወት ላይ ጠባሳ እንደሚጥል መገመት አያዳግትም፡፡"

የኢትዮጵያ የጽንስና ማህጸን ሐኪሞች ማህበር በመቀሌ ሐይደር ሆስፒታል ባቋቋመው ሞዴል ክሊኒክ የሚመጡ ታካሚዎች ከሌሎች ታካሚዎች ጋር በመደባለቅ ወረፋ ሳይጠብቁ በቀላልና በፍጥነት አስፈላጊው ምርመራና ሕክምና እየተደረገላቸው መሆኑን ከተጠቃሚዎች ለመረዳት ተችሎአል፡፡ ተገዶ መደፈር የደረሰባቸው ሴቶች እርግዝና መኖር ያለመኖሩ፣ ከኤችአይቪ ቫይረስ ነጻ መሆን ያለመሆናቸው እና የመሳሰሉትን ሕክምናዎች በነጻ ከማግኘታቸውም በላይ ጉዳያቸው በህግ እንዲታይላቸው አስፈላጊው ሕክምናና መረጃ ካለምንም ክፍያ ይሰጣቸዋል፡፡ በመሆኑም በቅርብ ጊዜ ስራውን የጀመረው ክሊኒክ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ከ75/ያላነሱ ባለጉዳዮችን ማስተናገዱን ሲ/ር አበባ ገልጻለች፡፡

**ይህንን አምድ አዘጋጅቶ የሚያቀርብላችሁ ESOG-Ethiopian Society of Obstetricians and Gynecologists (የኢትዮጵያ የፅንስና የማህፀን ሀኪሞች ማኅበር) ነው፡፡**
**(በፖ.ሣ.ቁ 8731 ስልክ 011-5-506068/69 ልታገኙን ትችላላችሁ)**

ፊደል ከገፅ 14 የዞረ

የሴም ፊደሎች ሰሜን ሲናዊ እና ደቡብ ሲናዊ በመባል በሁለት ወገን ይከፈላሉ፡፡ እናም ለኢትዮጵያዊው ፊደል (ግዕዝ) መነሻ ሆኖአል የተባለው የሳባ ፊደል በደቡቡ ሴማዊ ክፍል የሚገኝና በደቡብ ዐረብ የነበረ ነው፡፡

ይህ በደቡብ ዐረብ ይሰራበት የነበረውና ኋላም ወደ ኢትዮጵያ ተሻግሮ የግዕዝን ፊደል ያስገኘው የሳባ ፊደል፣ ሃያ ዘጠኝ ሆሄያት እንደነበሩት ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ግዕዝ ይኸንን የአጻጻፍ ስልት በወረሰበት ጊዜ ሁሉንም አልተቀበላቸውም፡፡ ምክንያቱም በሁለቱ ቋንቋዎች ማለትም በሳባና በግዕዝ ድምፀ ልሳኖች ውስጥ አንዳንድ ድምፆች ልዩነት ስለነበራቸው ነው፡፡

ከዚህም የተነሣ ግዕዝ አምስቱን በመተው፣ ሃያ አራቱን የሳባ ፊደል ሆሄያት ሊወርስ ችሏል፡፡ በተጨማሪም ከንፈራዊ ደወል የለሽ (ፐ) እና አንድ ከንፈራዊ ፈንጂ (ጰ) የተባሉትን ሁለት ድምፀ ወካይ ምልክቶች በማከል የፊደል ሆሄያቱን ቁጥር ኻያ ስድስት አድርሶታል፡፡ እንዲሁም ኻያ ስድስቱ ሆሄያት ድምፅ ሰጪ እንዲኖራቸው በመደረጉ፣ በጠቅላላው (26x7) አንድ መቶ ሰማንያ ሁለት ሆኑ ማለት ነው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም፡፡ የግዕዝ ዲቃላ የሚባሉ ሌሎች አራት ሆሄያትም በመኖራቸውና እነሱም በበኩላቸው አምስት ድምፅ ሰጪዎች ስላሏቸው (4x5) ሃያ ዲቃላ ሆሄያት ስለሚሆኑ፣ የግዕዝ ፊደል በጠቅላላው 202 ሆሄያት ነበሩት፤ አሉትም፡፡

የግዕዝ ፊደል የሚባሉት 26ቱ ድምፆችና አራቱ ዲቃሎች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ፣ ለ፣ ሐ፣ መ፣ ሠ፣ ረ፣ ሰ፣ ቀ፣ በ፣ ተ፣ ኀ፣ ነ፣ አ፣ ከ፣ ወ፣ ዐ፣ ዘ፣ የ፣ ደ፣ ገ፣ ጠ፣ ጰ፣ ጸ፣ ፀ፣ ፈ፣ ፐ እንዲሁም ኰ፣ ጐ፣ ቈ፣ ኈ ናቸው፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት በተለይም 26ቱ የግዕዝ ፊደል ተነባቢ ድምፆች የየራሳቸው የሆነ ትርጉምና የአጠቃቀም ህግ አላቸው፡፡ የጋዜጣውን ዓምድ ላለማጣበብ ሲባል እንጂ ሁሉንም መዘርዘር በተቻለ ነበር፡፡

የግዕዝ ፊደል ለኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ በር ከፋች ሆኖ በስፋት ሥራ ላይ መዋል ከጀመረ በኋላ እጅግ በርካታ ድርሳናት ተደርሰውበታል፡፡ በግዕዝ ቋንቋና ፊደል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ቅዱሳት መጻሕፍትዋ ላይ የጻፏቸውን ጨምሮ የአያሌ መጣጥፎችና መጻሕፍት ደራሲ የሆኑት ምሁር ፕሮፌሰር ኤፍሬም ይስሐቅ በሐመር መጽሔት ሐምሌ/ነሐሴ ፲፱፻፺፯ ዓ.ም እትም፤ "...ኢትዮጵያ በጥንታዊው የሥነ ጽሑፍ ታሪክ በዓለም የመጀመሪያውን ረድፍ የምትይዝ አገር ናት፡፡ በእንግሊዝ፤ በፈረንሳይ፣ በጀርመን ዛሬ የሚፃፉት ሁሉ ከኢትዮጵያ ሥነ-ፅሁፍ በኋላ የመጡ ናቸው፡፡ ከኢትዮጵያ ሥነ ጽሑፍ ጋር የሚወዳደሩት ትልልቆቹ የግሪክ፣ የአራማይክ፣ የላቲን፣ የመሳሰሉቱ ናቸው፡፡ ..." በማለት ኢትዮጵያን ታላቅ ከሚያደርጓት ሀብቶቿ አንዱ ይኸው የግዕዝ ሥነ ፅሑፍ መሆኑን በዝርዝር መግለፃቸውን እናያለን፡፡

በጥቅሉ ስለ ግዕዝ ፊደል የትመጣነትና አገልግሎት በዝርዝር ለማስቀመጥ ሰፊ ቦታና ጊዜ ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም ለመግቢያ ያህል ይህችን ታህል ካልን የሚበቃ ይመስለኛል፡፡ እናም ዘመቻ ወደበዛበት ወደ አማርኛ ፊደል መለስ ብለን ማየት እንሞክር፡፡

የአማርኛ ፊደል ለአማርኛ ቋንቋ መጻፊያነት እንዲያገለግል ሆኖ ሥራ ላይ መዋል የጀመረው በ1270 ዓ.ም የዛጌ ሥርወ መንግስት ማብቂያ ዘመን አካባቢ መኾኑ ይነገራል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ፊደሉን የወረሰው በቀጥታ በግዕዙ ከሚገኙት ሆሄያት ነው፡፡ ከላይ የተዘረዘሩትን ሃያ ስድስቱንም የግዕዝ ሆሄያት አንድም ሳያስቀር ሁሉንም ተቀብሏቸዋል፡፡

ያደረገው አዲስ ነገር ቢኖር ለቋንቋው የሚያገለግሉ 7 ድምፃዊ ምልክቶችን (የድምፅ ወካዮችን) ጨምሮ የፊደሉን ቁጥር ወደ 33 ከፍ አድርጎ መጠቀም መቻሉ ነው፡፡

እነዚህም ተጨማሪ ያደረጋቸው ሆሄያት "ሸ"ን ከሰ፣ "ቸ"ን ከተ፣ "ኸ"ን ከከ፣ "ኘ"ን ከነ፣ "ዠ"ን ከዘ የፈጠራቸው ናቸው፡፡ በመጨረሻም ከ"በ" ሆሄ "ቨ" የሚለውን ወካይ ጨምሯል፡፡

በዚህ ሁኔታ ስንመለከተው፣ አማርኛ የራሱ የሆነ ፊደል አለውን? ለሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት ይከብዳል ተብሎ አይገመትም፡፡ አንድ ቋንቋ ወይም አገር የራሱ ፊደል አለው ብሎ መናገር የሚቻለው የቋንቋውን ድምፆች የሚወክሉ ሆሄያትን የያዘ ፊደል መፈልሰፍ ሲችል ነው፡፡ ስለሆነም አማርኛ የሚጠቀምበት ፊደል 78.8% የግዕዝ በመሆኑ ፊደሉ የአማርኛ ነው ማለት ይከብዳል፡፡ ከዚህም የተነሣ አማርኛ በግዕዝ ፊደል ላይ በጨመራቸው 7 ሆሄያት ብቻ የቋንቋውን ድምፆች በጽሑፍ መግለጽ ስለማይችል የራሱን ፊደል ይዟል አይባልም፡፡

ከዚህም ላይ አማርኛ ከግዕዝ የወረሰው ፊደሉን ብቻ አይደለም፡፡ ከቋንቋውም ቀላል የማይባሉ ቃላትን በመዋስ ሲጠቀምባቸው ቆይቷል፤ እየተጠቀመባቸውም ነው፡፡ ይህ ከሆነ ታድያ "የአማርኛ ፊደል ይሻሻል፤ ፊደላት በዝተዋልና ይቀነሱ" ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችና ዘመቻዎች ለምን ይነሳሉ? በቀጣይ የምንመለስበት ይሆናል፡፡ ቸር እንሰንብት፡፡

ጠባቂ ከገፅ 7 የዞረ

ጀምሮ አንድ ሺህ ብር ጨምረናል፡፡

ካልተስማማችሁ በሁለት ቀን ውስጥ ቤቱን ልቀቁልን፡፡" የምር ያበሳጫል፡፡ ስሙኝማ...የብስጭት ነገር ከተነሳ ... "እንትናዬው ምን ያህል ብታበሳጨው ነው ሴቶችን እንደዚህ ጠምዶ የያዛት!" የሚያሰኝ ንግግር ገጥሟችሁ አያውቅም!

ሰውየው ጓደኛውን... "ሬድዮ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠረው በገነት ውስጥ ነው ሲሉ ሰማኋቸው፡፡

ምን ማለታቸው ነው?" ሲል ይጠይቀዋል፡፡ ጓደኝዬውም ምን ብሎ መለሰ መሰላችሁ..."እሱን የነገሩህ ሰዎች ፈጣሪ አዳምን ፈጠረ፡፡ ከዚያም ከጎኑ የጎድን አጥንት አወጣና የመጀመሪያውን ድምጽ ማጉያ ፈጠረ ማለታቸው ነው፣" ብሎት አረፈ፡፡ 'ጉልቤነትን'... አለ አይደል... ሲሆን ያስወግድልን፣ ካልሆነም የምንሸከምበትን ትከሻ ያደንድንልን፡፡

"የበጎቹ ጠባቂ ሆይ፣ 'ወየት' ነህ!" የምንልበትን ጊዜ ያሳጥርልን፡፡

ደህና ሰንብቱልኝማ!

ፕሮግራም ከገፅ 7 የዞረ

አካባቢውን በጩኸት ደባለቁት፡፡ አጠገባቸው እንደደረሰች የመኪናው በር ተከፍቶላት በቄንጥ ወረደችና ወደ አዳራሹ ዘለቀች፡፡

(እኛስ?... እኛማ እንኳን በሚሊዮን ብር መኪና ታክሲም በግድ ነው፤ በሰልፍ እየተንገላታን፡፡ ባቡራችን ቢደርስልን እንኳ በገንዘብ መወዳደር ባንችል እንኳን በፍጥነት እንቀራረብ ነበር፡፡ ከዚህ ውጪ መቼም አማራጭ የለም፤ ያው እንደፈረደብን በአንበሳችን እንታጨቃለን እንጂ!)

አዳራሹ በእንግዶቿ ተሞልቷል፤ ወደ አዳራሹ እንደተገባ በስተቀኝ በኩል መጠነኛ መድረክ ተዘጋጅቷል፡፡

አጋፋሪም ተመድቦለታል፤ በፈረንጅ ቡዳ የተበላ ይመስል አንድም የአማርኛ ቃል ሳይተነፍስ ነው ፕሮግራሙን የመራው፡፡ ለነገሩ ማን ያውቃል? "አማርኛ ከተናገርክ ወዮልህ!" ተብሎም ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላው አስገራሚው ነገር ደግሞ አንድም የኢትዮጵያ ሙዚቃና ውዝዋዜ ሳይታይ ነው ዝግጅቱ የተጠናቀቀው፡፡

ከዚህ በኋላ "በዓይነቱ ልዩ የሆነ ኬክ" ቀርቦ ባለ ልደቷ ቆረሰች፤ ርችቶች ተለኮሱ፤ ጩኸት በረከተ፤ ኬክ ተወራወሩ፤ ፊታቸውን ተለቀለቁት፡፡ በመጨረሻም ባለ ልደቷ ወደ መድረኩ በመውጣት ጋብዛቸው ሳያሳፍሯት ለመጡ ጓደኞቿ ምስጋና አቅርባ፣ ቀሪው ጊዜ ያማረ እንዲሆን ተመኝታ ወረደች፡፡ የልደት በዓሉ እዚህ ጋ ይጠናቀቅና ከአንድ ጓደኛዋ ጋር በመሆን አረጋውያንን ስትጎበኝ ተመለከትን፡፡ (በኔ ዕይታ ከፕሮግራሙ ውስጥ ብቸኛ መልካም ተግባር ይሄ ነው፡፡)

እንግዲህ ይህ ነው "One's in a Life" ማለት፡፡ አንድም ኢትዮጵያዊ መልክ የሌለው (እኛን የማይመስል) ፕሮግራም እንዴት ለኢትዮጵያውያን አማራጭ ተብሎ በተመሰረተ የቴሌቪዥን ጣቢያ እንዲቀርብ ይደረጋል? በእኔ አስተያየት ፕሮግራሙ መልካምነቱ ለተመሰከረለት ጣቢያ የማይመጥን፣ የህብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ፣ ባህልና ወግም ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ነው፡፡

ከእኛ ይልቅ ለውጭዎቹ ይበልጥ የሚቀርብም ነው፡፡ (ምናልባት ለዳያስፖራ ኢትዮጵያውያን?) እንደሚመስለኝ ባህል ወግ ልማዴን ትቼ ካልጠፋሁ እያለ ያስቸገረውን ወጣት፤ ወደ ቀድሞ ክብሩ መመለስ ባይቻል እንኳ፣ ባለበት ተረጋግቶ እንዲቆም ማድረግ የሁላችንም ኃላፊነት ነው፡፡ መልካም ሳምንት!

# 2014ን ወደኋላ

ግሩም ሠይፉ















በ2014 በዓለም ዙሪያ ታላላቅ የስፖርት ውድድሮች ተካሂደዋል፡፡ ጎን ለጎን በርካታ አወዛጋቢ አጀንዳዎችም ተከስተዋል፡፡ በራሽያዋ ግዛት ሶቺ የተካሄደው የክረምት ኦሎምፒክ ያስወጣው ከፍተኛ በጀት ያስገረመ ነበር፡፡ ብራዚል ያስተናገደችው 20ኛው የዓለም ዋንጫ ደግሞ የምን ግዜም ምርጥ ቢባልም በውዝግቦች ታጅቧል፡፡ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ተራቅቋል በአነጋጋሪ ክስተቶች የደመቀ ዓለም ዋንጫ ነበር፡፡ በሌላ በኩል ግዙፎቹ የስፖርት አስተዳደር ተቋማት በተለያዩ የውዝግብ አጀንዳዎች የታመሱበትም ዓመት ነበር፡፡ ዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ማህበር ‹‹ፊፋ›› ምንም እንኳን ብራዚል ባዘጋጀችው 20ኛው ዓለም ዋንጫ እስከ 4.5 ቢሊዮን ዶላር ትርፍ ቢያጋብስም 2009 አባል አገራት ያሉት ፊፋ 9 ዓለም ዋንጫዎች አዘጋጆችን ምርጫ ሙስና በተንሰራፋበት አሰራር ማከናወኑ ከፍተኛ ትችት አስከትሎበታል፡፡ ዓለም አቀፉ የኦሎምፒክ ኮሚቴም በታላቁ የስፖርት መድረክ ኦሎምፒክ ዙሪያ አሳሰቢ አጀንዳዎች ተፈጥረውበታል፡፡ የኦሎምፒክ አዘጋጆች የሚጠይቀው ከፍተኛ የበጀት ወጪ የአገራትን የመስተንግዶ ፍላጎት እያሳጣበት ነው፡፡ በኦሎምፒክ ውድድርና መስተንግዶ ተሃድሶ ለማድረግ መነሳቱ አበይት መነጋገርያ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ 2015 እኤአ ዓለም ዋንጫና ኦሎምፒክ ባይኖሩበትም በተለያዩ አህጉሮች የሚደረጉ ትልልቅ የስፖርት ውድድሮች ይስተናገዱበታል፡፡ በ2015 የውድድር ካለንደር በርካታ ዓለም አቀፍ ውድድሮችን በማስተናገድ እድለኛ የሆነችው አውስትራሊያ ናት፡፡ የኤስያ ካፕ፤ የዓለም የሜዳ ቴኒስ ሻምፒዮና፤ የዓለም የክሪኬት ዋንጫን ታዘጋጃለች፡፡ ቻይና 15ኛውን የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና በጉዋጂንግ ቤጂንግ ስታስተናግድ፤ በአፍሪካ አህጉር ደግሞ ኢኳቶርያል ጊኒ የምታዘጋጀው 30ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ይሆናል፡፡ ካናዳ ደግሞ የሴቶች እግር ኳስ ዓለም ዋንጫን ታዘጋጃለች፡፡

ስፖርት አድማስ በ2014 እኤአ በስፖርቱ ዓለም ያጋጠሙ አበይት ክስተቶችና ሁኔታዎችን ከዚህ በታች ከልሷቸዋል፡፡

## የጀርመን የዓለም ዋንጫ ድል

የ2014 እኤአ ዋና የስፖርት መድረክ በነበረው የብራዚል 20ኛው ዓለም ዋንጫ የጀርመን የበላይነት የተረጋገጠበት ነበር ቢሆንም በዓመቱ በእግር ኳስ እንደ ጀርመን ስኬታማ የሆነ የለም፡፡ የጀርመን እግር ኳስ በፊፋ ወርሃዊ የእግር ኳስ ደረጃ በ1725 ነጥብ በመሪነት በክለብ እና በብሄራዊ ቡድን ደረጃ በየውድድሮቹ ቋሚ ተፎካካሪ የሆነበር ዕድገት የዓመቱ ትልቅ ስኬት ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ በ20ኛው ዓለም ዋንጫ ላይ የፍፃሜው ጨዋታ የጀርመን ብሄራዊ ቡድን አርጀንቲናን 1ለ0 በማሸነፍ ለአራተኛ ጊዜ የዓለም ሻምፒዮን ለመሆን በቅቷል፡፡ ይሄ የዓለም ዋንጫ ድል ከ24 ዓመታት በኋላ የተገኘ ነበር፤ አውሮፓዊ ቡድን ደቡብ አሜሪካ አህጉር ላይ ለመጀመርያ ጊዜ የዓለም ዋንጫን ክብር መቀዳጀቱም አዲስ ታሪክ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ የጀርመን እግር ኳስ ስኬት በዓለም ዋንጫ ድል ብቻ የተወሰነ አልነበረም፡፡ ባለፉት አምስት ዓመታት የአገሪቱ ክለቦች በአውሮፓ ትልልቅ ውድድሮች ቋሚ የዋንጫ ተፎካካሪ ሆነዋል፡፡ የቦንደስ ሊጋ ውድድር በስታድዬም ተመልካች ብዛት እና በአስተማማኝ የኢኮኖሚ ጥንካሬው ተምሳሌት ሆኖ ይገኛል፡፡ በፊፋ የ2014 የወርቅ ኳስ ፉክክር ውስጥ ጀርመናዊያን በዋና ዋና የሽልማት ዘርፎች የመጨረሻ እጩ ናቸው፡፡ የጀርመን እግር ኳስ ፌደሬሽን ይህን ስኬት በሚቀጥሉት 10 ዓመታት በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ እቅድ በ2024 እኤአ ላይ ደግሞ የአውሮፓ ዋንጫን በታላቅ ድምቀት ለማዘጋጀት ይፈልጋል፡፡ ኦሎምፒክንም ለማስተናገድ ፍላጎት አለ፡፡

## የሪያል ማድሪድ ኃያልነት

በአውሮፓ እግር ኳስ 2014ን የነገሰበት የስፔኑ ክለብ ሪያል ማድሪድ ነው፡፡ 4 ትልልቅ ዋንጫዎችን ሰብስቧል፡፡ አስረኛውን የሻምፒዮንስ ሊግ የዋንጫ ድል አትሌቲኮ ማድሪድን 4ለ1 በማሸነፍ መቀዳጀቱ የመጀመሪያው ነበር፡፡ በተጨማሪ የአውሮፓ ሱፐር ካፕ ፤ የስፔን ኮፓ ዴላ ሬይ እና የዓለም ክለቦች ሻምፒዮና ሶስት ዋንጫዎችን በሽልማት ያስገባው ገንዘብ ከ65 ሚሊዮን ዩሮ በላይ ነው፡፡ አሶስዬትድ ፕሬስ በ2014 የእግር ኳስ ገድላቸው ጎልቶ ለወጡ ክለቦች በሰራው ደረጃ በ137 ነጥብ በአንደኛነት የሚመራም ክለቡ በ2015 እኤአ ተጨማሪ 4 ዋንጫዎችን ለመሰብሰብ አቅዶ እየሰራ እንደሚገኝ ጣሊያናዊው አሰልጣኝ ካርሎ አንቾሎቲ ተናግረዋል፡፡

## የታላላቅ ተጨዋቾች ጡረታ

በ2014 የቀድሞ ታላላቅ ተጨዋቾች እግር ኳስን በጡረታ ተሰናብተዋል፡፡ በጡረታ ጫማቸውን ከሰቀሉት መካከል ቲዬሪ ሆንሪ፤ ሃቪዬር ዛኔቲ፤ ካርሎስ ፒዮል፤ ሪያን ጊልስ፤ ክላረንስ ሲዶርፍ፤ ቬሮንና ሪቫልዶ ይጠቀሳሉ፡፡ በተጫዋችነት ባሳለፉባቸው የውድድር ዘመናት በተለያዩ የአውሮፓ ሊጎች እና የውስጥ ውድድሮች 50 ዋንጫዎችን 15 የሻምፒዮንስ ሊግ የዋንጫ ድሎችንም አግኝተዋል፡፡ ለብሄራዊ ቡድኖቻቸው 857 ጨዋታዎችን ያደረጉም ናቸው፡፡ ሶስት የዓለም ዋንጫን ያሸነፉ ፤ ሁለት የኦሎምፒክ የወርቅ ሜዳልያ የተጎናጸፉ እንዲሁም የወርቅ ኳስ ተሸላሚ ብራዚላዊው ሪቫልዶ ይገኙበታል፡፡

## የኦስካር ፒስቶርዬስ ወንጀል

በ2014 እኤአ በስፖርቱ ዓለም አስደንጋጭ እና አነጋጋሪ ከነበሩ ክስተቶች መጠቀስ ያለበት ደቡብ አፍሪካዊው የፓራኦሎምፒክ ጀግና ኦስካር ፒስተርዬስ የትዳር አጋሩን ራሴን ለመከላከል በሚል ምክንያት በጥይት ተኩሶ ገድሏታል፡፡ ፍርድ ቤት የተመላለሰበት የክስ ሂደት ከፍተኛ ትኩረት የሳበ ነበር፡፡ ከሁለት ወራት በፊት 5 ዓመት ፅኑ እስራት ተፈርዶበት ወህኒ ወርዷል፡፡ የ36 ዓመቱ ኦስካር ፒስቴርዬስ በፓራኦሎምፒክ የአጭር ግዜ ተሳትፎው በጣም ስኬታማ ነበር በ100 ሜትር እና በ200 ሜትር ውድድሮች 6 የወርቅ፤ 1 የብር እና 1 የነሐስ ሜዳልያዎችን በፓራ ኦሎምፒክ ውድድሮች ተጎናፅፏል፡፡ በ100 የፓራኦሎምፒክ ሪከርድም አስመዝግቧል፡፡ ሰሞኑን በተፈረደበት የ5 ዓመት የወህኒ ቆይታ ላይ ይግባኝ ጠይቋል አልተሳካለትም፡፡ በመልካም ተመክሮ ለመፈታት ቢያንስ 10 ወራት ወህኒ እንዲቆይ ይጠበቅበታል፡፡

## ዶፒንግና አይ.ኤ.ኤ.ኤፍ

ዓለም አቀፉ የአትሌቲክስ ፌደሬሽኖች ማህበር ‹‹አይኤኤኤፍ›› በ2014 እ.ኤ.አ የዓለም የቤት ውስጥ ሻምፒዮና፣ ኢንተርኮንትኔንታል ካፕ፤ የዱላ ቅብብል የዓለም ሻምፒዮና የዓለም የግማሽ ማራቶን ሻምፒዮና፤ የዳይመንድ ሊግ እና ሌሎች ውድድሮችን በተሳካ ሁኔታ አካሂዷል፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት ከዶፒንግ በተያያዘ የሚነሱት አጀንዳዎች በዓመቱ መጨረሻ የተከሰቱ ነበር፡፡ ከ1999 እኤአ አንስቶ ዓለምን አቀፉን የአትሌቲክስ ፌደሬሽኖች ማህበር የመሩት ሴኔጋላዊው ለሚን ዲያክ ጫና ውስጥ ገብተዋል፡፡ 2014 የመጨረሻ የግልጋሎት ዘመናቸው እንደሚሆን እየተገለፀ ነው በዶፒንግ ዙርያ የተፈጠሩት አወዛጋቢ አጀንዳ በስልጣን የመቆየታቸውን ተስፋ አጠያያቂ አድርገዋል፡፡ ባለፈው ሰሞን የጀርመን ብሄራዊ የቴሌቭዥን ጣቢያ የሰራው ጥናታዊ ፊልምም በዶፒንግ ዙሪያ ያሉ የተድበሰበሱ ችግሮችን አጋልጧል፡፡ አይኤኤኤፍ በዶፒንግ ዙሪያ በከፍተኛ የአሠራር ችግር መውተብተቡን የረዳ ፊልም ሆኗል፡፡ በውድድር ወቅት አስፈላጊውን የህክምና ምርመራ ባለማድረግ፤ ብቃትን የሚጨምሩ መድሃኒቶችን ለመቆጣጠር ባለመቻል እና በለዘብታ በማለፍ ዓለም አቀፉ ማህበር እና ታላላቅ አትሌቶች መጠየቅ አለባቸው የሚል ዘመቻ ከፍቷል፡፡ በጀርመኑ የቴሌቭዥን ጣቢያ በዶፒንግ ችግር ተጠርጣሪ ናቸው ተብሎ በወጣው የ150 አትሌቶች ዝርዝር የብሪታኒያ፤ የራሽያና የኬንያ አትሌቶች ይገኙበታል፡፡

በተለይ የራሽያ ኦሎምፒያኖች 99 በመቶ ብቃት የሚጨምሩ መድሃኒቶች ይጠቀማሉ በሚል የተሰራው ዘገባ እያነጋገረ ነው፡፡ ከራሽያ ባሻገር በዶፒንግ ችግር የገዘፈ ክብር እና ዝናው አደጋ ውስጥ የወደቀው ደግሞ የኬንያ አትሌቲክስ ነው፡፡ ኬንያዊ እውቅ አትሌቶች ከመደበኛ የዶፒንግ ምርመራ በማፈንገጥና ከምርመራ በኋላ ብቃት የሚያሳድጉ መድሃኒቶች መጠቀማቸው በአንዳንዶቹ ላይ መረጋገጡ የአገሪቱ አትሌቲክስ እያቃወሰው ይገኛል፡፡ የኬንያ መንግስት በኬንያ አትሌቶች የዶፒንግ ችግር ዙርያ ዋና ተጠያቂ ያደረገው አትሌቲክስ ኬንያ ተብሎ የሚጠራው ፌደሬሽን ነው፡፡ አስፈላጊው ትኩረት እና ጥንቃቄ እንዲደረግ አልሰራም የሚል ምክንያት በማቅረብ አመራሮቹ ከስልጣናቸው እንዲለቁ ግፊት እያደረገባቸው ነው፡፡ የኬንያ አትሌቶች ኤጀንቶች እና ማናጀሮችም በኬንያ መንግስት ተወቅሰዋል፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት የቦስተን እና የቺካጎ ማራቶኖችን ያሸነፈችው ሪታ ጄፕቶከወር በፊት የተከለከለ መድሃኒት መጠቀሟ በዶፒንግ ምርመራ ተደርሶበታል፡፡ ብቃት ያሳድጋል የተባለውና እና እውቁ ብስክሌተኛ ላርንስ አርምስትሮንግ በመጠቀሙ አምኖ የተቀጣበትን "ኢፒኦ" የተባለ መድሃኒት መውሰዷ በመረጋገጡ ነው፡፡ በ2014 ብቻ ከዶፒንግ ምርመራ ጋር በተያያዘ የ32 የኬንያ አትሌቶች የክስ ፋይል መከፈቱ ቢነገርም በይፋ የተገለፀው የ16ቱ ብቻ መሆኑ የኬንያ አትሌቲክስ ፌደሬሽን አመራሮች ከ25 ዓመታት በላይ በሃላፊነት መቆየታቸው ጥያቄ ውስጥ ገብቷል፡፡ የፌደሬሽን አመራሮቹ በኬንያ ያለው የዶፒንግ ችግር ከራሽያና ከቻይና የባሰ አይደለም በሚል ይሟገታሉ፡፡ ለአትሌቶች ብቃት የሚያሳድጉ መድሃኒቶችን የሚያቀርቡ ህገወጥ ቡድኖች ታድነው ለፍርድ እንዲቀርቡም አይኤኤኤፍ ይፋ ባደረገው ሪፖርት በ2014 እኤአ በዓለም አትሌቲክስ በ39 አገራት የሚገኙ 225 አትሌቶች በዶፒንግ ዙርያ ክስ ቀርቦባቸው ምርመራ ተደርጐባቸዋል፡፡

## ኢቦላ ያመሰው የአፍሪካ እግር ኳስ

2014 የአፍሪካ እግር ኳስ በኢቦላ የታመሰበት ዓመት ነው፡፡ ከ5 ወራት በፊት የኢቦላ ወረረሽኝ በምዕራብ አፍሪካ ሲከሰት የአህጉሪቱ የእግር ኳስ ውድድሮች ተቃውሰዋል፡፡ በአፍሪካ እግር ኮንፌደሬሽን የሚካሄዱ የማጣርያ ውድድሮች ፕሮግራማቸው ተዛብቷል፡፡ የአፍሪካ ዋንጫ አዘጋጅ ተሰርዞ ለምትክ አስተናጋጅ ተላልፎ ተሰጥቷል፡፡ በአፍሪካውያን ስፖርተኞች ላይ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ውድድሮች የመገለል እና ከልክ ያለፈ ጥርጣሬ ተፈጥሯል፡፡ ዓለም አቀፍ ደረጃ ያላቸው የስፖርት ክለቦች እና የውድድር አመራሮች ወረርሽኙን በመፍራት ባወጧቸው የጥንቃቄ መመርያዎች የዘረኝነት አጀንዳዎች አከራክረዋል፡፡ በ2015 እኤአ ላይ 30ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ የምታዘጋጀው ሞሮኮ ነበረች፡፡ ከኢቦላ ወረረሽኝ በተያያዘ በተፈጠረ ስጋት ግን ውድድሩን በ2016 እንዳስተናግድ ይሸጋሽግልኝ ብላ ጥያቄ አቀረበች፡፡ ካፍ አልተቀበለውም፡፡ ስለሆነም ውድድሩ ለምትክ አዘጋጁ ኢኳቶርያል ጊኒ መሰጠቱ ግድ ሆኗል፡፡ ጊኒ፤ ላይቤርያ እና ሴራልዮን ዓለም አቀፍ የእግር ኳስ ውድድሮችን በአገራቸው መሬት እንዳያካሂዱም የኢቦላ ወረርሽኝ ምክንያት ነበር ታግደው ዓመቱን አሳልፈዋል፡፡

## የፊፋ ቅሌት

ዓለምአቀፉ የእግር ኳስ ማህበር ፊፋ በ2014 በበርካታ የአስተዳደር ቀውሶች ተበጥብጧል፡፡ በማህበሩ አመራሮች ላይ በተደጋጋሚ የቀረቡ ክሶች የተቋሙን ተዓማኒነት አደጋ ላይ ጥለውታል፡፡ በ2018 እ.ኤ.አ 21ኛውን ዓለም ዋንጫ ራሽያ፤ በ2022 እ.ኤ.አ 22ኛው የዓለም ዋንጫ ኳታር እንዲያዘጋጁ የተመረጡት በከፍተኛ የሙስና መረብ መሆኑ መጋለጡ አሁንም እያነናገርነው፡፡ ዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ማህበር በተለያዩ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች በተሰራጩ የምርመራ ሪፖርቶች የውስጥ ገበናው ተጋልጦበታል፡፡ ትልልቅ ባለስልጣናቱ እርስ በራስ እንዲወዛገቡ እና አንዳንዶቹም ከስልጣን እንዲለቁ ምክንያት የሆኑ ውዝግቦች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል በዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ማህበር ፕሬዝዳንትነት ለ16 ዓመታት ያገለገሉት ሴፕ ብላተር ግን ቅሌቱን ለማስተባበል መሟገታቸውን አልተውም፡፡ በ2014 በከፍተኛ ደረጃ ከተወቀሱና ከተተቹ የስፖርት አመራሮች ግንባር ቀደሙ ተደንቋል፡፡ በ2015 እ.ኤ.አ ሴፕ ብላተር ለፊፋ ፕሬዚዳንትነት ለአምስተኛ ጊዜ ለመመረጥ ፍላጐት እንዳላቸው አስታውቀዋል፡፡

## የኦሎምፒክ በጀት መጥፋት

በ2014 በከፍተኛ ድምቀት ለመካሄድ ከቻሉ የስፖርት መድረኮች በራሽያዋ ግዛት ሶቺ ለመካሄድ የበቃው የ2014 የክረምት ኦሎምፒክ ይጠቀሳል፡፡ በከፍተኛ የበጀት ወጭው እና በተሳካ መስተንግዶው ተደንቋል፡፡ የሶቺ የክረምት ኦሎምፒክ ለማዘጋጀት ራሽያ ከ50 ቢሊዮን ዶላር በላይ ወጭ አድርጋለች፡፡ የምንጊዜም ውድ የኦሎምፒክ መስተንግዶ ሆኖ በታሪክ መዝገብ ሰፍሯል፡፡ ይሁንና ከፍተኛ በጀት የሚጠይቀው የኦሎምፒክ መስተንግዶ ዓመቱን ሙሉ ሲያከራክር ነበር፡፡ የዓለም አቀፉ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ፕሬዝዳንት ቶማስ ባች የኦሎምፒክ ውድድር ተሃድሶ እንደሚያስፈልገው በማሳሰብ ከፍተኛ ዘመቻ እያደረጉ ናቸው፡፡ በ2022 እኤአ የክረምት ኦሎምፒክ ለማዘጋጀት አመልክተው በተለያዩ ምክንያቶች እቅዳቸውን የሰረዙት ሶስት ከተሞች ናቸው፡፡ ይህ ያሳሰባቸው ፕሬዝዳንቱ ታላቁ የስፖርት መድረክ ትኩረት እንዳያጣ ይፈልጋሉ፡፡ የስዊድኗ ስቶክሆልምና የዩክሬኗ ኪዬቭ ከተሞች የክረምት ኦሎምፒክ ለማስተናገድ የነበራቸውን ፍላጎት ሰርዘዋል፡፡ በጀቱን አንችልም በሚል ምክንያት ነው፡፡ የክረምት ኦሎምፒኩን ብቻ ሳይሆን ዋናውን የኦሎምፒክ ውድድር ከወጭው ክብደት አንፃር ቢሆኑም ማለት ነው፡፡ ማዘጋጀት የሚፈልጉ አገራት ጠፍተዋል፡፡ ዓለም አቀፉን የኦሎምፒክ ኮሚቴ ሁኔታው አሳስቦታል፡፡ አስቀድሞ ኦሎምፒክን ለማስተናገድ ለአንድ አዘጋጅ አገር ብቻ የሚሰጠውን እድል በመከለስ አገራት ለጣምራ አዘጋጅነት እንዲያመለክቱ ግፊት እያደረገ ነው፡፡ በ2016 እኤአ ብራዚል በሪዮ ዴጄኔሮ ከተማ 31ኛውን ኦሎምፒያድ እንዲሁም በ2020 ጃፓን በቶኪዮ ከተማ 32ኛውን ኦሎምፒያድ እንዲያስተናግዱ ተመርጠዋል፡፡ በ2024 እኤአ 33ኛውን ኦሎምፒያድ ማን እንደሚያስተናግድ ግን ከወዲሁ የታወቀ ነገር የለም፡፡ የመስተንግዶ ወጭዉ በየኦሎምፒኩ በከፍተኛ ደረጃ እያደገ መምጣቱ አዘጋጅ አገር የማግኘቱን እድል እያጠበበው መጥቷል፡፡ በ1996 እኤአ አትላንታ ኦሎምፒክ 1.8 ቢሊዮን፤ በ2000 እኤአ ሲድኒ ኦሎምፒክ 3.8 ቢሊዮን፤ በ2004 እኤአ አቴንስ ኦሎምፒክ 15 ቢሊዮን፤ በ2008 እኤአ ቤጂንግ ኦሎምፒክ 40 ቢሊዮን እንዲሁም በ2012 እኤአ ለንደን ኦሎምፒክ 49 ቢሊዮን ዶላር ወጥቷል፡፡

## የወርቅ ኳስ ፖለቲካ

በ2014 እኤአ በከፍተኛ ደረጃ መነጋገርያ ከሆኑ የእግር ኳሱ ዓለም አጀንዳዎች አንዱ የፊፋ የወርቅ ኳስ ሽልማት ነው፡፡ 3 የመጨረሻ እጩዎች ከታወቁባቸው የ2014 የመጨረሻ ወራት ወዲህ ክርክሩ በመጧጧፉም አሸናፊውን ለመገመት አዳጋች ሆኗል፡፡ የሽልማት ስነስርዓቱ ከ2 ሳምንታት በኋላ በዙሪክ እንደሚከናወን ይጠበቃል፡፡ በዓለም ኮከብ ተጨዋቾች ምርጫው የሻምፒዮንስ ሊግና የዓለም ዋንጫ ስኬቶች እንዲሁም አዳዲስ የእግር ኳስ ሪከርዶች የሚኖራቸው ተጽእኖ አከራካሪ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በአንዳንድ የስፖርት ሚዲያዎች የምርጫው ሂደት ፖለቲካዊ አጀንዳ እየተንፀባረቀበት መሆኑም ተገልጿል፡፡ የአውሮፓ እግር ኳስ ማህበር ፕሬዝዳንት ሚሸል ፕላቲኒ የወርቅ ኳሱን የዓለም ሻምፒዮን የሆነ ተጨዋች መሸለም አለበት ብሏል፡፡ ከዚህ አስተያየት በኋላ በስፖርቱ ዙርያ ያሉ አሰልጣኞች፤ ተጨዋቾች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የወርቅ ኳሱን ማን ይሸለም በሚለው አጀንዳ ሲሟገቱ ሰንብተዋል፡፡ የማንቸስተር ዩናይትድ አሰልጣኝ ሊውስ ቫን ሃል፤ እውቁ የሆላንድ የእግር ኳስ ሰው ዮሃን ክሮይፍ፤ ለባየር ሙኒክ የሚጫወተው ዣቪ አሎንሶ የሚሸል ፕላቲኒን ሃሳብ ይጋራሉ፡፡ ሽልማቱ ለግብ ጠባቂው ኑዌር ይገባል ይላሉ፡፡ የሪያል ማድሪድ አሰልጣኝ የሆኑት ካርሎ አንቾሎቲ በበኩላቸው ሽልማቱ የሚገባው በግሉ ምርጥ ብቃት ላሳየ ተጨዋች ይገባል በሚል አስተያየት ለሮናልዶ ድጋፍ ሲሰጡ፤ የክለቡ ፕሬዝዳንት ፍሎረንቲኖ ፔሬዝም በዓለም እግር ኳስ ሁሉን ያሟላ ተጨዋች ሮናልዶ በመሆኑ መሸለሙ ተገቢ ነው ብለዋል፡፡ የቼልሲው ጆሴ ሞውሪንሆ በበኩላቸው የወርቅ ኳሱ ፖለቲካ ለእግር ኳስ እንደማይበጅ በመናገር ማንም ቢያሸንፍ ግድ እንደሌላቸው ይገልፃሉ ከሰሞኑ ደግሞ አንጋፋው የባርሴሎና ተጨዋች ዣቪ ኸርናንዴዝ ሮናልዶ ከሶስቱ እጩዎች ተርታ መሰለፍ እንደሌለበት ተናግሯል፡፡ የወርቅ ኳስ ለመሸለም በዓለም ዋንጫ ስኬት ማሳየት ዋና መስፈርት ሊሆን ይገባል በማለትም ሜሲ ካልተሸለመ ማኑዌል ኑዌር ቢሸለም ይገባዋል ብሏል፡፡ ባለፈው ዓመት ከሶስቱ የመጨረሻ እጩዎች አንዱ የነበረው ፈረንሳዊው ፍራንክ ሪበሪ ደግሞ ሽልማቱን አርያን ሮበን ባይወስድ እንኳን ለማኑዌል ኑዌር እንደሚገባ አስታውቋል፡፡ በሌላ በኩል የባርሴሎናው ኔይማር ሆኖ የሰጠው ድምፅ ሰሞኑን ግሎቦ በተባለ የአገሩ ጋዜጣ ወጥቷል፡፡ የብራዚል ብሔራዊ ቡድን አምበል ለቡድን አጋሩ ሊዮኔል ሜሲ ድጋፍ እንደሰጠ ተጋልጧል፡፡

ዓለም አቀፉ የእግር ኳስ ማህበር እንዳስታወቀው የፊፋ አባል ከሆኑ 209 አገራት ዋና አሰልጣኞች እና አምበሎች 87.3 በመቶ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች 94 በመቶ ድምፅ ሰጥተዋል፡፡ በምርጫው ባለፈው ዓመት ከፊፋ 205 አባል አገራት 505 ድምፅ ተሰብስቧል፡፡ 170 አምበሎች፤ 170 አሰልጣኞች እንዲሁም 165 የዓለም አቀፍ ሚዲያ ባለሙያዎች ነበሩ፡፡

ታዋቂው ጎል ስፖርት የድረገፅ አንባቢዎቹን ድምፅ እንዲሰጡ በማድረግ በሰራው ስሌት የዘንድሮ የወርቅ ኳስ ሽልማትን ማን ሊወስድ እንደሚችል በመቶኛ ተንብዮታል፡፡ ባለፈው ዓመት ሁለተኛውን የወርቅ ኳስ የወሰደውና ዘንድሮ ሶስተኛውን ለመሸለም እድል ያለው ክርስትያኖ ሮናልዶ በ57.2 በመቶ ድምፅ ከፍተኛውን ግምት አግኝቷል፡፡ ሮናልዶ በመጨረሻ እጩነት ሲቀርብ በውድድር ዘመኑ ከክለቡ ሪያል ማድሪድ ጋር የአውሮፓ ሻምፒዮንስ ሊግ ዋንጫን መውሰዱና በ17 ጎሎች ኮከብ ግብ አግቢ ሆኖ መጨረሱ ይታወቃል፡፡ሊዮኔል ሜሲ በጎል ድረገፅ አንባቢዎች 22.6 በመቶ ግምት በመውሰድ ለወርቅ ኳሱ ሽልማት ባለው እድል ሁለተኛ ደረጃ ተሰጥቶታል፡፡ ሜሲ በ2014 የውድድር ዘመን ከክለቡ ባርሴሎና ጋር ምንም አይነት የዋንጫ ድል ባያስመዘግብም በስፔን ፕሪሚዬራ ሊጋና በአውሮፓ ሻምፒዮንስ ሊግ የከፍተኛ ግብ አግቢነት ክብረወሰኖችን መቆጣጠሩ ወደ ፉክክሩ አግብቶታል፡፡ ሁለቱን አጥቂዎች ክርስትያኖ ሮናልዶንና ሊዮኔል ሜሲን በመፎካከር ከሶስቱ የመጨረሻ እጩዎች አንዱ ለመሆን የበቃው ደግሞ የጀርመን ብሄራዊ ቡድንና የባየር ሙኒክ ግብ ጠባቂ የሆነው ማኑዌል ኑዌር ነው፡፡ ማኑዌል ኒዌር በ20ኛው የዓለም ዋንጫ ከጀርመን ብሄራዊ ቡድን ጋር የዓለም ሻምፒዮን ለመሆን መብቃቱ ከፍተኛ ድጋፍ ያስገኝለታል፡፡ ኑዌር ከክለቡ ባየር ሙኒክ ጋር ባለፈው የውድድር ዘመን አራት ትልልቅ የዋንጫ ድሎችን አስመዝግቧል፡፡ በጎል ድረገፅ አንባቢዎች ለወርቅ ኳሱ በ20.2 በመቶ ድምፅ የማሸነፍ እድል ሶስተኛ ደረጃ ወስዷል፡፡ በፊፋ የዓለም የኮከብ ተጨዋቾች ምርጫ ታሪክ ከመጨረሻዎቹ እጩዎች ተርታ ለመግባት የቻለው ብቸኛው ግብ ጠባቂ ከስምንት ዓመት በፊት የጁቬንትስ እና የጣሊያን ተጨዋች የሆነው ጂያንሉጂ ቡፎን ነበር፡፡ በሌላ በኩል የወርቅ ኳስ ተሸልሞ የሚያውቅ በረኛ በታሪክ አንድ ጊዜ ብቻ አጋጥሟል፡፡ በ1963 እኤአ ‹ጥቁሩ ሸረሪት› በሚል ስም የሚጠራው ራሽያዊው ግብ ጠባቂ ሌቭያሺን የተሸለመበት ነበር፡፡

## የማራቶን ሪከርድና ኃይሌ

2014 እኤአ የዓለም የማራቶን ሪከርድ በኬንያዊው አትሌት ዴኒስ ኬሜቶ በበርሊን ማራቶን መሰበሩ አበይት ክስተት ነበር፡፡ ዴኒስ ኬሚቶ ያስመዘገበው አዲስ የዓለም ማራቶን ሪከርድ 2፡02፡57 የተመዘገበ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሚነሳው በ2007 እና በ2008 እኤአ ላይ ለሁለት ጊዜያት የዓለም ማራቶን ክብረወሰኖችን ለማስመዝገብ የበቃው ኢትዮጵያዊ አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ራነርስዎርልድ መፅሄት ከወር በፊት ይፋ ባደረገው አንድ ዘገባ በማራቶን ከፍተኛ የገንዘብ ሽልማት ያገኙ አትሌቶችን ደረጃ እንደሚመራ ማስታወቁ ኃይሌ ገ/ስላሴን ያስነሣዋል፡፡ በ2015 እኤአ የመጨረሻ የማራቶን ውድድሩን ለመሮጥ እንደወሰነ ያስታወቀው ኃይሌ ገብረስላሴ፤ በሩጫ ዘመናቸው ከፍተኛ ገቢ ከሽልማት ገንዘብ ያገኙ አትሌቶች ደረጃን የሚመራው በሰፊ ልዩነት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ደረጃውን ሳይነጠቅ ለዓመታት እንደሚቆይ ያመለክታል፡፡ ራነርስዎርልድ መፅሄት በዓለም አቀፍ የማራቶን ውድድሮች የምንግዜም ከፍተኛ የገንዘብ ተሻላሚዎች ደረጃን ያገኘው ከዓለም አቀፉ የጎዳና ላይ ሩጫዎች ስታስቲክስ ማህበር መሆኑን የሚገልፀው መፅሄቱ በወንዶች ምድብ የምንግዜም ከፍተኛ ተሻላሚ ደረጃ ኃይሌ ገብረስላሴ በ3,548, 398 እንዲሁም በሴቶች ፓውላ ራድክሊፍ በ2,236,415 ዶላር ገቢያቸው ይመሩታል፡፡ በሯጭነት ከ23 ዓመታት በላይ ልምድ ያለውና 41ኛ ዓመቱን የያዘው አትሌት ኃይሌ ገብረስላሴ ከጡረታ በፊት አንድ የመጨረሻ ማራቶን የመሳተፍ ፍላጎት እንዳለው የተናገረው ሰሞኑን ነው፡፡ በማራቶን ተወዳዳሪነት 9 ውድድሮችን ያሸነፈው ኃይሌ ገብረስላሴ ለአራት ጊዜያት የበርሊን ማራቶንን፤ ለሶስት ጊዜያት የዱባይ ማራቶንን አሸንፏል፡፡ በማራቶን ሁለት የዓለም ክብረወሰኖችን ያስመዘገበው ኃይሌ ከ2 ሰዓት ከሰባት ደቂቃዎች በታች በ10 ማራቶኖች፤ ከ2 ሰዓት ከ06 ደቂቃ በታች በአምስት ማራቶኖች፤ ከ2 ሰዓት 05 ደቂቃ በታች በሶስት ማራቶኖች እንዲሁም ከ2 ሰዓት ከ04 ደቂቃ በታች በአንድ ማራቶን ርቀቱን በመሸፈን ስኬታማ ነበር፡፡

# ተክለሃይማኖት ጠቅላላ ሆስፒታል
Teklehaimanot General Hospital

## የ24 ሰዓት የእናቶችና የህጻናት ህክምና

### ለህፃናት

- የጨቅላ ህፃናት ጠቅላላ ህክምና
- ያለጊዜያቸው ለሚወለዱ ህፃናት በኢንኩቤተር የታገዘ ህክምና
- ከተወለዱ በኋላ ቢጫ ለሚሆኑ ህፃናት የፎቶቴራፒ ህክምና
- የጨቅላ ህፃናት አይሲዩ /NICU
- ለህፃናት ብቻ የተዘጋጁ ልዩ የምርመራና የመኝታ ክፍሎች
- የህፃናት ጤናማ ዕድገት ክትትል
- የክትባት አገልግሎት
- የግርዛት አገልግሎት
- መለስተኛና ከፍተኛ ቀዶ ህክምና በህጻናት ቀዶ ህክምና ስፔሻሊስቶች

### ለእናቶች

- የቅድመ ወሊድ ፅንስ ክትትል እና የድህረ ወሊድ ክትትል
- የማዋለድ አገልግሎት
- የተሟላ የማህፀን ህክምና እና ቀዶ ህክምና
- የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት
- የመሀንነት ምርመራ
- የቅድመ ካንሰር ምርመራ



ተክለሃይማኖት ጠቅላላ ሆስፒታል የእርስዎና የቤተሰብዎ፡፡
ሆስፒታለንዳ፣
ያሁ ... ያበሩሳሁ ... ይና ... ይንመንዳ!!




ዓ ሳ ማ ች ን ህ ሙ ማ ን ን መ ር ዳ ት ነ ው!!
A Center Where the Oath of Hippocrates Comes True !!

Tel:+251 111 561 287 / +251 111 561 114 Fax:+251 111 562 Email:tgh@ethionet.et www.tgh.com.et PoBox24078

አድራሻ : ሱማሌ ተራ



ካቤ CABEY
ኃ.የተ.የግ.ማ. Private Limited Company

BRIDGESTONE

Tel: 011-55-11-138 /Mob. 0911-20-60-44
Fax. 011-46-63-164 /P.o.box. 18192/
e-mail cabey@ethionet.et

